በፍቅር፤ በሰላም፤ በአንድነት፤
ተከባብሮ ለመኖር
መደማመጥ!
መቻቻል!

ኢትዮጵያዊ
የቤተሰብና የመዝናኛ መጽሔት
በአማርኛ

$2.75

# ላንድፍታ

ሚያዝያ/ግንቦት
፲፱፻፹፱
፭ኛ ዓመት
ቁጥር ፭

"... ኢትዮጵያ ላይ የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት የፈፀመውን በደልና ግፍ ለማተት የዚህ ወረቀት ቦታ አይበቃንም፤ ዝርዝሩ ብዙ ነው። ከዚህ ሁሉ ትልቁ ግፍ የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሀገር–በቀል ፊደልና ቋንቋ እንዲጠሉ በማድረግ ላቲንን እንዲቀበሉ እያደረገ ነው። ..."

ከአፍሪቃዊ–አሜሪካኖች ጥናትና ምርምር
ፕሮፌሰርና ሥራ አስኪያጅ፣

ገጽ 32

## የሲቪክ ማህበረሰቦች አስፈላጊነት

"... ዛሬ በኢትዮጵያ የተከሰተው የፖለቲካ ስርዓትና ሁኔታ ከምንጊዜውም የከፋና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ህልውና ያናጋ ክስተት ነው ብዬ አምናለሁ። እንዲሁም፣ የዚሁ ሁኔታ መለወጥ ደግሞ የአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ፍላጎት ነው ብዬም አምናለሁ። ነገር ግን፣ ይህ በውሁዳን በኢትዮጵያ ላይ የተጫነው የጨለማ ዘን ሊገፈፍ ያልቻለው፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች ውስጣዊ ድክመትና ከውጭ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ባሻገር፣ ጥያቄዎቻቸውን ከመሰረታዊው ፀረ የጎሳ ክፍፍልና አድልዎ ጋር በጥብቅ የሚያያይዙና ከስትራቴጂያዊው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና ጥያቄ ጋር የሚያስተሳስሩ የሲቪክ ማህበረሰቦች ማነስና አለማደግ ይመስለኛል።"

ጌታቸው በጋሻው (ገጽ 13)

# LANDAFTA

An Ethiopian Cultural Magazine In Amharic
(Amharic is the Official Language of Ethiopia)
April/May 1997 Vol. V - No.5

**Patrick A. Harton**
*Partner*

**Teketel Wegayehu**
*Legal Asst.*

# HARTON & HENRY

Attorneys At Law

**Samuel C. Henry**
*Partner*

**G. Angela Harton**
*Office Mgr.*

## "A Law Firm Proudly Serving the Ethiopian Community"

በየትም ቦታና ጊዜ ለሚያጋጥምዎ አጠቃላይ የሕግ ችግሮች
ምንም ነገር ከማድረግዎ በፊት በሕግ ምክርና የጥብቅና አገልግሎት
የታወቀውን የሐርትንና ሔነሪ የጥብቅና ድርጅት
በማነጋገር ለችግርዎችዎ በሙሉ አስቸኳይ መፍትሔ ያግኙ።

- Auto Accident
- Immigration Law
- Personal Injury
- Business Law
- Divorce
- Criminal Law

- Ethiopian National with extensive knowledge of Ethiopian history, laws, language and culture on staff.

## Free Consultation

**70 Fairlie Street, Suite 260, Atlanta, Georgia**

**404◆681◆1800**

# ኤክስፕሬስ

## የገበያ አዳራሽ መዝናኛና የባህል ምግብ ቤት

# EXPRESS FOOD MART

በቅርቡ ሥራውን የጀመረው ድርጅታችን የደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት በልዩ ዝግጅትና መስተንግዶ ተቀናብሮ ቀርቧል። የምግብ ማጣፈጫ ቅመማ ቅመም ከማቅረብ ሌላ ትዝታ ቀስቃሽ የባህል ምግቦችን ተወዳዳሪ በማይገኝላቸውና የረጅም ጊዜ ልምድ ባላቸው ባለሙያዎች እያዘጋጀ ያቀርባል። በተጨማሪም የመዝናኛ ክፍላችን ሌሎች አገልግሎቶችንም ለመስጠት በዝግጅት ላይ መሆኑን በደስታ እንገልጻለን።




For your Pleasure
we also carry:

- *Video sales & rentals*
- *Audeo cassettes*
- *Compact Discs*
- *Ethiopian Magazines*

**የአገራችንን ምግብ ለመሥራት
የሚያስፈልጉ ነገሮች ሁሉ ቀርበዋል፤**

1. በርበሬ
2. ምጥን ሽሮ
3. ሽሮ
4. አዋዜ
5. የቅቤ ቅመም
6. ጤፍ
7. መከለሻ
8. ምስር ክክ
9. አተር ክክ
10. ቅንጨ
11. የገንፎ ዱቄት
12. የአጥሚት ዱቄት
13. በሶ
14. እንጀራ
15. ጠላ
16. ጠጅ

በተጨማሪ ለክትፎ፤ ለጥብስና ለጥሬ
የሚሆን ወደር የማይገኝለት ሥጋ

Recreation Room Services Include:

- *Table Tennis*
- *Billiard*
- *Pin Balls*
- *Video Games*
- *Other Indoor Games*
- *Coffee & Tea*

**መጥተው ይጎብኙን!!
በመስተንግዶአችን ይኮራሉ።
ሰፊ የመኪና ማቆሚያ
ስላለን አይቸገሩም።**

**EXPRESS FOOD MART**

4959 - C Memorial Drive
Stone Mountain, GA 30083
Phone: (404)299-6800
Fax: (404)325-7344

# ማ ው ጫ CONTENTS


3 ከአዘጋጁ

4 ሰላምታ ከወደ አገር ቤት (ወርቃየሁ)

5 ሰላምታ ከባህር ማዶ (ገብርዬ)

13 የሲቪክ ማህበረ—ሰቦች አስፈላጊነት (ጌታቸው በጋሻው)

16 አዲሱ የኢምግሬሽን አዋጅ

21 ከአንባብያን

23 እንዲህ ሆነ (ከዜና ማህደር)

30 የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ሠራዊት መግለጫ

32 ከጥቁር አሜሪካውያን የትግላችን ደጋፊዎች . . .

37 "ጣጣቴ ገዳይ" (ሰይፉ መኩሪያ)

38 ከአበው (መጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

39 የግጥም ጉባኤ

41 "ለመታሰቢያ" (አገኘሁ እንግዳ)

43 ዜና ቤተ ክርስቲያናት

45 "እኔ የምለው!" ("ትርፍ ያለው ጓደኝነት)

46 የሰንጠረዥ ጨዋታ


ስለ የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ሠራዊት መግለጫ

ገጽ 30

. . . ኢትዮጵያ ላይ የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት የፈፀመውን በደልና ግፍ ለማተት የዚህ ወረቀት ቦታ አይበቃንም፡ ዝርዝሩ ብዙ ነው። ከዚህ ሁሉ ትልቁ ግፍ የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሀገር-በቀል ፊደልና ቋንቋ እንዲጠሉ በማድረግ ላቲንን እንዲቀበሉ እያደረገ ነው። . . .

የአፍሪቃዊ-አሜሪካኖች ጥናትና ምርምር ፕሮፌሰርና ሥራ አስኪያጅ፣

ገጽ 32

". . . ዛሬ በኢትዮጵያ የተከሰተው የፖለቲካ ስርዓትና ሁኔታ ከምንጊዜውም የከፋና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ህልውና ያናጋ ከስተት ነው ብዬ አምናለሁ። እንዲሁም፡ የዚሁ ሁኔታ መለወጥ ደግሞ የአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ፍላጎት ነው ብዬም አምናለሁ። ነገር ግን፡ ይህ በውሁዳን በኢትዮጵያ ላይ የተጫነው የጨለማ ዘን ሊገፈፍ ያልቻለው፡ ከፖለቲካ ድርጅቶች ውስጣዊ ድክመትና ከውጭ መንግሥት ጫልቃ ገብነት ባሻገር፡ ጥያቄዎቻቸውን ከመሰረታዊው ዐረ የጎላ ክፍፍልና አድልዎ ጋር በጥብቅ የሚያያይዙና ከስትራቴጂያዊው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና ጥያቄ ጋር የሚያስተሳስሩ የሲቪክ ማህበረሰቦች ማነስና አለማደግ ይመስለኛል።" ጌታቸው በጋሻው (ገጽ 13)

ላንዳፍታ የግል መፅሔት ናት። የሚወጡ ጽሑፎች በሙሉ የአዘጋጁን አመለካከት ወይም እምነት ያንጸባርቃሉ ማለት አይደለም። ጽሑፎቹን በሬዲዮ፤ በቴሌቪዥን ሆነ በተመሳሳይ መንገድ በከፊልም ሆነ በሙሉ አባዝቶ ለማሰራጨት የፀሐፊውንና የአዘጋጁን ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋል። በተለይ የፈጠራ ድርሰቶች መብታቸው በሕግ የተጠበቀ መሆኑን መግለጽ እንወዳለን።

© COPYRIGHT LANDAFTA 1997

**ላንዳፍታ**
ሚያዝያ/ግንቦት ፲፱፻፹፱
5ኛ ዓመት ቁጥር 5
LANDAFTA
April/May 1997 Vol. V - No.5



**አዘጋጅና አሳታሚ**
*መኮንን ገሠሠ*

**Publisher/Editor**
*Mekonnen Gessesse*

**Assistant Editor:**
*Genet Wolde*

**Contributors:**
*Workayehu (pen name)*
*Girma Zegeye*
*Seifu Mekuria*
*Seifu Bishaw*
*Gebrie (Pen Name)*
*Wuhib Tiruneh*
*Eyayu Belelgne (pen name)*
*Rev. Mekbib Atnaw*

**Editorial Advisors**
*Lisanu Simret*
*Dr. Abera Molla*
*Dr. Tilahun G. Hiwot*
*Solomon Melesse*
*Dawit Deres*

Distribution
Atlanta, GA
California Mart
Sweet Auburn Grocery
H & B Shop
Nazareth Restaurant
Express Food Mart
Chicago, IL
Ethio-Village Rest.
Dallas, TX
Maru Grocery
Abeba Grocery
Durham, NC
Blue Nile Ethiopian
Cusine
Houston
Queen Sheba Rest.
Maru Grocery
L.A., CA
Merkato
Damera
Oak Land, CA
Albo-African Shop
San Diego, CA
Emebet Worku
Axum Market
San Jose, CA
St. Claire news Stand
Seatle, WA
Arat Kilo Deli Grocery
St. Louis, MO
A & Z Liquor
St. Paul, MN
Merkato
Washington D.C. area
Addisu Gebeya
Nini Market (Alex.)
Tana (Silver Spring)
Windsor, Ontario
Tewodros Zewdu
London


# ከአዘጋጁ

እንደምን ከርማችኋል። በየጊዜው በአገራችን የሚከሰቱትን ሁኔታዎች በተመለከተ የምናቀርባቸው ዝግጅቶች ይኖሩናል። በዛሬው እትም ሰፋ ያለ የዜና ቅንብር አለን። ከፖለቲካ ፓርቲ ባሻገር በሲቪክ (ሕዝባዊ) ድርጅቶች አማካይነት ልናደርግ ስለምንችለው አስተዋጽኦ ገብርዬና ጌታቸው በጋሻው የሚያካፍሉን ሃሣብ ይኖራቸዋል። በአሜሪካን አገር የሚኖረውን ፍልሰ ስደተኛ (immigrants) ትልቅ ትርምስ ውስጥ የከተተውን የአሜሪካንን አዲሱን የፍልሰ ስደተኛ ሕግ በተመለከ አቀናብረን ያቀረብነው ዝግጅት አለ። የጥቁር አሜሪካውያን ምሁራን ወያኔ እያደረሰ ያለውን ችግር የአሜሪካን ኮንግሬስ ማወቅ የሚገባውን በተመለከተ ተቃውሞአቸውን ያሰሙበትን ደብዳቤ ከእነትርጉሙ አቅርበናል። ምን እንደታየው አናውቅም ሰይፉ መኩሪያ ከርሞ ከርሞ በዛ በምንናፍቀው ሽጋ ብዕሩ ስለ ክላሽንኮቭ ጠበንጃ የሚነግረን አለው። አገኘሁ እንግዳ ከአዲስ አበባ ጠቅላይ ቢሮ አሜሪካ ላለችው መታሰቢያ የጻፈላትን ደብዳቤ እንዳለ አውጥተነዋል።

ትምህርት አዘል የሆነው የወርቃየሁ ከአገር ቤትና ገብርዬ ደግሞ ከአሜሪካ የሚጻጻፉት የሰላምታ ልውውጥ አለን። የግጥም ጉባኤ አምዳችን በልሣኑ ስምረት፤ በካሣሁን በቀለና በዶ/ር ፍቅሬ ቶሎሣ ብዕር ተስተናግዷል። ከሚፃፉት የገጠመኝ ታሪኮች "እልፍ ሲሉ እልፍ ሊገኝ" የሚለውን የአትናትዮስን ተከታታይ ታሪክና የአብረኸትን "ዕጣዬ"ን በቦታ እጥረት ምክንያት ለሚቀጥለው እትም አስተላልፈናል።

ቋሚ ጸሐፊዎቻችንም ሆናችሁ ሌሎች በላንዳፍታ ላይ እንዲወጣ የምትፈልጉትን ጽሑፍ ቀደም ብላችሁ እንድትልኩልን አደራ እንላለን።


**ለኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተክርስቲያን ተከታዮች እንኳን ለብርሃነ ትንሣኤው አደረሳችሁ!!**



የላንዳፍታ መፅሔት ዝግጅት ክፍል
LANDAFTA
P.O.Box 49301, Atlanta, GA 30359
Phone: (404) 508-4657 Fax: (404) 508-2447
E-MAIL- mgessesse@aol.com
HOME PAGE:
http://www.ethiopic.com/landafta.htm



*Landafta is an independent magazine published bi-monthly in Amharic. Views expressed do not necessarily represent that of its editors and advisors.*

# ሰላምታ ከወደ አገር ቤት
## ከወርቃየሁ

እንደምን ከረማችሁልኝ ውድ የአገሬ ልጆች። በሰው አገር መባከኑ፣ ከውድ እናት ሀገር ተለይቶ መኖሩ፣ ዘመድና ወገን መናፈቁ እንዴት እያደረጋችሁ ይሆን? አንዳንዴ ስለእናንተ ሳስብ ጭንቅ ጭንቅ ይለኝና በቃ እነዚህ ልጆች በዛው እንደወጡ መቅረታቸው ነው እንዴ እላለሁ። አውሮፓውያንና አሜሪካኖች የአፍሪካን አዕምሮ በመሸርሸር ለሚያደርጉት ተግባር እናንተም ውድ ወገኖቼ ከጉናቸው የቆማችሁም ትመስሉኛላችሁ፤ አንዳንዴ ደግሞ እዚህ ያለውንና ቅጥአንባሩ የጠፋውን ሁኔታ ሳየውና በተማረው ኃይል ላይ የሚደርስበትን ስቃይ ስመለከት ደግሞ «ለካስ እነዚህ ልጆች እውነት አላቸው እላለሁ» ምኑን ትቼ ምኑን እንደምቀበል ግራ ግብት ብሎኛል።

ደግሞ እንደገናም ይግለጡ እንዳለው እዛ ያለው የተማረ የሚባለውና ጥሩ የንግድ እንቅስቃሴ ያደርጋል የሚባለውን ዜጋ ስለአገሩ ፍቅርና አንድነት ያለውን ደካማ ስሜት ሳስበው በመጠኑም ቢሆን ሳልከፋ የምቀር አይምሰልህ። በዚያን ሰሞን የአገራችሁ ፕሬዚዳንት ባለቤት ወይም በእናንተው አባባል ‹‹First Lady›› ከወደ ላይ «ጌቶቻችን» ሰፈር ደርሳ ሄደችን ስሰማ እነዚህ የአገሬ ሰዎች ይህ ሁሉ ሲደረግ እውን በህይወት አሉ ብዬ መጠየቁ አልቀረም! ግን እናንተስ ብትሆኑ ምን መብት አላችሁ? «ከአገሩ የወጣ አገሩ እስኪመለስ፣ ቢነዱት አህያ ቢጋልቡት ፈረስ!» ሆናችሁ ይሆን?

ወዳጄ ገብርዬ! ለመሆኑ አንተስ እንዴት ነህ? ባለፈው የፃፍክልኝ ስለብዙኃን ድርጅት ምንነትና ጠቃሚነት ያስተላለፍከው መልዕክት እጅግ ጥሩ ነው። እንዳልከውም በአገራችን ያልተለመደ ሆኖ ነው መሰል ከብዙ ሰዎች ጋር በዚሁ ጉዳይ ላይ ስንወያይበትና ስንከራከርበት ሰነበትን። ቃል በገባህልኝ መሰረት እስቲ በደንብ አብራራልንና የበለጠ እንረዳው።

ገብርዬ! ይኸው ለገበሬው የቆምኩ ነኝ ሲል የነበረው የአገራችን መንግሥት በገበሬው ከፍተኛ ተቃውሞ ደርሶበት ከረመ። ትዝ ይላችሁ እንደሁ ጥንት ያኔ በጃንሆይ ዘመን የፊውዳሉ የመሬት ስሪት ሳይቀየር የጐጃም፣ የሸዋ፣ የወሎ፣ የአርሲና የባሌ ገበሬ በገፍ እየመጣ ቤተመንግሥቱ ፊት ለፊት «አቤት አቤት» ሲል ነበር የሚከርመው። ዘንድሮ ደግሞ የጐጃም ገበሬ ነቅሎ፣ ማሳውን ትቶ ለአቤቱታ አዲስ አበባ በመምጣት «ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ» ቢሮ ፊት ለፊት እሱም በተራው «አቤት አቤት» ሲል ከረመ። ያ ሲታመሙ በወላንሳ ተሸክሞ፣ ሲራቡ አብልቶ፣ ሲደክሙ አሳርፎ እዚህ ያደረሳቸው ገበሬ ውለታው ሁሉ ተረሳና ዛሬ ማን ዞር ብሎ ይየው? ምንድነው ችግርህስ ማን ይበለው? እንዴ አልጋ ላይ ከተወጣ ወላ ገበሬ፣ ወላ ነጋዴ ቢንጫጫ ማን ከጉዳይ ሊጾለው? «ተልባ ቢንጫጫ በአንድ ሙቀጫ» አለ የአገሬ ሰው!

የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎችም እነዚህኑ ገበሬዎች ደግፈው ሰልፍ ወጡ፤ ግን ምን አገባችሁና ተብለው ዘብጥያ ወረዱ። ብንታሰርም፣ ብንረገጥም እኛው እንሻላለን መሰለኝ ትንሽ ቆይቶም የአዲስ አበባም ሕዝብ በነቂስ በሰልፍ ወጥቶ የገበሬዎቹን ጥያቄ በመደገፍ አለሁልህ አለ። ሰሚ ቢገኝ መልካም ነበር። ነገር ግን አዋጁን ያወጣው ራሱ የወያኔ መንግሥት ሆኖ ሳለ ይህ «የክልል ግዛትን የሚመለከት» እንጂ የፌዴራሉን መንግሥት አይመለከትም በማለት ጠ/ሚኒስትሩ ለውጪ ጋዜጠኞች መግለጻቸውን ስንሰማ ዓይን ባወጣው ውሸታቸው በጣም ነው የታዘብናቸው። እንግዲህ ጠቅላይ ሚኒስትር ተብዬው ስለሱዳኑ ጦርነት ሁኔታ ሲጠየቁ ስለ በቆሎ ምርት የሚያወሩ ከሆነና ለምን በመግለጫዎ ላይ የግል ጋዜጠኞችን አያነጋግሩም ሲባሉ ደግሞ ብፈልግ አነጋግራለሁ ባልፈልግ ደግሞ አላነጋግርም እያሉ የህፃን መልስ አይነት የሚሰጡ ከሆነ በየክልሉ ያለው አመራር ምን እንደሚመስል አንተው ራስህ በህሊናህ አስበው። ታዲያ ገብርዬ እውን ኢትዮጵያ በሰዎች እየተመራች ነው ማለት እንችላለን? ግን እኛስ ምን ዋጋ አለን? መታዘብ፣ መቆጨት፣...ብቻ! አንድ እንኳ አካኪ ዘራፍ ፣ እምቢ ለመብቴ፣ እምቢ ለአገሬ፣ እምቢ ለነፃነቴ፣ የማንል ትውልድ! እንዲሁ የወረቀት ላይ ነብር ብቻ!

ገብርዬ አንዴ በአንድ የሬዲዮ የቀልድ ፕሮግራም ላይ አንድ ኮመዲያን ያስተላለፈውን ቀልድ መሰል ትምህርት ላጫውትህ። ድሮ የእኛ ትውልድ አለ ልቡም ወኔውም ነበረን፣ የአሁኑ ትውልድ ደግሞ ጥሩ ምላስና አፍ አለው፣ የሚቀጥለው ትውልድ ደግሞ ሁሉም አይኖረውም ብሎን አሳረፈን። እኔ ግን በጣም አሳፈረኝ። ታዲያ እንዲች አይነቷ ንግግር ምንም ቢሆን ኤዲት አትደረግም። ለምን ብትል ስድብ ናታ! እውነትም እኛም ልብም የለንማ!

ገብርዬ! ሰሞኑን በርዕሰ ከተማችን በአዲስ አበባ በተከታታይ ፍንዳታዎች እየተሰማ ነው። የሞተውን ቤቱ ይቁጠረውና የተጐዳው ግን በቁጥር ብዙ ነው። ጠቅላይ ሚኒስትራችን መለስ የሰላም ተሸላሚ ለመሆን በሚሞሸሩበት ሰሞን ይህ ነገር መከሰቱ እንገት የሚያስደፋቸው ቢሆንም ትዝ ይልህ እንደሆን የድሮው ምክትል ጠ/ሚኒስትር አንዱ ሐረርጌ ሄደው «ብትፈልጉ መገንጠል ትችላላችሁ» በማለት ቅስቀሳ አካሂደው እንደነበር በደብዳቤዬ ላይ ማንሳቴ ትዝ ይለኛል። እንደሚወራው ቦንቡን ወርዋሪዎቹ የሶማሌ ተገንጣዮች ከሆኑ ቅስቀሳው ፍሬ አፍርቶአል ማለት ነው። "አዎን መገንጠል እንፈልጋለን!" ማለታቸው ነዋ! ታዲያ ይኼን ምን ትለዋለህ? አይ ፖለቲካ!!

በቸር እንሰንብት!

ወርቃየሁ ነኝ – ከሸገር

# ሠላምታ ከባህር ማዶ
# ከገብርዬ – ለወርቃየሁ

በጠፈር ርቀት ክናድ ፥ በአእጋራ ፀሐያት ተመን
በረቂቅ የሰማይ ገመድ ፥ በኢውሱን ዐመተ–ብርኃን
ዘርፉ በማይቋጨው ፥ በመዓቱ ሰበባችን
በምዝበራው በአፈና ጊዜ ፥ በልቅሶውም በሰቀቀን
ሠላምታ አሁንም ላንተ ፥ ባያሌው በጥብቅ እጅ ጉንዳ።
በወያኔ ሥረወ መንግሥት ፥ በዘር እባብ «ብልሁ»
ጊዜስ ምኑን ያልፍልሀል ፥ እንዴት አለህ
ወርቃየሁ!!
ምድረ የካድሬ መንጋ ፥ አበላ ባይ የከለለው
የዘር አንካሴ ችካሉ ፥ ምንድነው ውዝዋዜው
የኔ ብጤውን ባይሰማው ፥ ተሜን እንኳ ያላነቃው
ወይስ ነቅቶ አብቅቶ ነው ፥ አረ ነገሩ ምንድነው?
እስቲ ሸገርገር ብለህ ፥ ከሸገር ባሻገር አብራው
ትግል አደራ ነውና ፥ ለይግለጡም ንገረው።
እንደጥንቱ ተራምደህ
እንደልማድህ ተክዘህ
እንደወትሮህ መዝነህ፤
አንድም ነገር ሳታስቀር ፥ በጎዳግህ አስፍረው
የተሰማህን ነገር ሁሉ ፥ ባበራኸው አብራራው
እንደውኃ ሙላት ደርሰህ ፥
ቀለምህን አሾጉድጉደው፥
ተያይተን ብንፈራራ
ተገቢውን ባናፈራ
ሠግተን እንኳ ባንመለስ ፥
አንተው መልስህ መላልሰው
ገረን እንኳ ባይብስብን ፥ የእኛ ነገር እኮ ልዩ ነው
ኧረ ነገሩ ምንድነው፥
በባሰ ጉዳይ ላይ ያልባስነው።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

የአገራችን ነገር ግራ የሚያጋባ ነው። ዛሬ በአጫጭርና ግልፅ አረፍተ ነገሮች ሁሉም በአሜሪካ የሚኖር ኢትዮጵያዊ ዜጋ ውይይት እንዲከፍት እነሆ ይህን ደብዳቤ ከልቤ ጽፌአለሁ። ከልቤ በመሆኑም እንዳንተው ለሀገር ወዳድ ኢትዮጵያውያን ሁሉ በፍቅር የቀረበ ነው።

የጐሳ መስተዳደር ታሪክን ከላሽ፣ ሥልጣኔን አውዳሚ፥ ሕዝብን እርስ በእርሱ የሚያናክስ ብሎም ሕዝባችን ለዘላቂው የኢኮኖሚና የፖለቲካ መፍትሔዎች እንዳይታገል የሚበታትን እንደሆነ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ነኝ የሚለው (ከአፍራሾች በስተቀር) የተረዳው ይመስላል። ታዲያ ምንድነው እንደ ግመል ሽንት ወደኋላ የሚያስኬደን? አያ ወርቃየሁ – እዚህ ያለውን ሁኔታ በተለያዩ ጊዜያት እኔም ሆንኩ ይግለጡ ነካክተነዋል፤ የመሰለንን ከዚህ በፊት ፅፈናል። እስቲ ባንተ በኩል ያለውን በተለይም ተማርኩ የሚለውን ክፍል አስተሳሰብ መዝግብልን።

ባለፈው ደብዳቤዬ ስለብዙኃን ድርጅቶች (ማኅበራት) አስፈላጊነትና እነዚህም ለትግላችን፥ ለጋራ ግምባር አመቺ ሁኔታን ለመፍጠር የሚያደርጉትን አስተዋጽኦ፥ ለዕድገታችንና እንደዚሁም በአሜሪካ መጫወት ስለሚችሉት ሰብዐዊና ፖለቲካዊ ሚናዎች አትቼአለሁ። ዛሬም ይህን አስታከኬ እርስ በእርስ ያለመስማማትንና የመናናቅን ባሕል ለመምታት ብሎም መፍትሔውን ለመፈለግ እንዲያስችለን በአጭሩ አንዳንድ ቁምነገሮችን ለመግለፅ እወዳለሁ። መፍትሔ ካላገኘን ትልቅ አስተዋፅዖ ሊያደርግ የሚችለው በምዕራቡ ዓለም የእኛ መደራጀት ግቡን ሊመታ አይችልም።

ወዳጄ ወርቃየሁ!

አገር ማለት ጓደኛ፣ ሕዝብ፣ ወገን፣ ዓለማው፣ ወንዙ፣ ተራራው፣ ምድሩና አራዊቱ ነው። በተጨማሪም አገር ማለት ትሥሥሩ፣ ባሕላችን፣ ክብራችንና ባንዲራችን ነው። አገር ማለት ለበጐ ተግባርና ለሕዝብ ጥቅም የሚደራጅ ኮሚኒቲ፣ ስብስብና ድርጅት ማለት ነው። አገር ማለት ለጋራ ዓላማ ሕዝባችንን ከአስከፊ የዘር ጥላቻ ለማላቀቅና ብሎም አብሮ ለፍትሕ ለመታገል የጋራ መድረክ መመሥረት ነው። ሀገር ሁሉ ይህን ይይዛል። ባንዲራ መኪና ላይ እየለጠፉና የቱሪስት መሳቢያ ስዕሎችን ግርግዳ ላይ እየሰቀሉ ኢትዮጵያዊ ነኝ ማለት ነገር ግን በድርጅትና በኮሚኒቲ ምስረታ አለመሳተፍ ከደንቆሮነትም አልፎ በድንነት ነው። የሀገር ፍቅር ማለት ሀገርንና ባሕልን እንዲሁም ታሪክን ማፍቀር ነው። ኢትዮጵያዊ የሆነውንና ለአንድነት የሚታገለውን ሁሉ ማፍቀር ነው። ለመቻቻል፣ ለመደማመጥና ለመግባባት በር መክፈት ነው። ኢትዮጵያ ላይ በደረሰው አደጋ ከቀኝም ከግራም ያለ ወገንና ለአንድነት የሚታገል ሕዝብ በአይዲዮሎጂ መራኮትና ማዶ ለማዶ መታየት የለበትም። ልዩነቱን አቻችሎ አብሮ መታገል አለበት። መጀመሪያ ሃገሪቷን ከዚህ ከከፋ ሥርዓት ካላቀቅን በኋላ እንጣላለን። በቀላሉ ጥሉንና ንትርኩን ለሌላ አመቺ ጊዜ እናስተላልፈው (Postpone እናድርገው) ማለት ነው። ቻይንጋቼክና ማውዜዱንግ እንኳ ለተወሰነ ጊዜ አብረው ሰርተዋል። ይህ በቀላሉ ለተወሰነ ዓላማ እስከተወሰነ ጊዜ ድረስ የሚዋቀር ስብስብ ነው።

ስለኮሚኒቲ (የመረዳጃ ማኅበር) ስናነሳ ግልፅ መሆን ያለባቸው ጉዳዮች አሉ። የእርስ በእርስ መረዳጃ ማኅበራት ከአባላትና በጐ አድራጊዎች በሚገኙ መዋጮዎችና በመንግሥት መደጐሚያ ለኅብረተሰብ አገልግሎት ስለሚሰጡ

ከፖለቲካ ነፃ መሆን አለባቸው። ብዙውን ጊዜ እነዚህ ማኅበራት በቀረጥ ነፃ መዋሞዎች [(501) (C)(3)] ይደገፋሉ። ለባሕል ልውውጥ፣ ለትምህርታዊ ቁምነገሮችና ለኅብረተሰብ አገልግሎት የሚመሰረቱ ናቸው። ምንም እንኳ በፖለቲካ ጉዳዮች ባይሳተፉም በምዕራቡ ዓለም ባለው ሕግ ተጠቅመው ለሰው ልጆች መብት መከበር በሀገራቸውና በሌላው የዓለም ክፍል ላለው ሕዝብ ይታገላሉ። እዚህ ላይ ሕጉን በመጠቀም እነዚህ ሰብዓዊ ድርጅቶች በተራቀቀ ስሌት እንደሌሎች የአሜሪካ ሰብዓዊ ድርጅቶች ለሕዝባቸው ሊቆሙ ይችላሉ።

ሌላው ደግሞ በሰብዓዊ መብት ዓላማ፣ በፆታ ስብስብ፣ በኢኮኖሚ ዕድገት መድረክና በሌሎችም የሚዋቀሩ የብዙኃን ማኅበራት ለተወሰነ የዴሞክራሲ ጥያቄ፥ ለመሰብሰብና ለመፃፍ ሊታገሉ ይችላሉ። የብዙኃን ድርጅቶች የአረማመድና የመፈክር ስልቶች ከሀገሪቷ ባሕል፣ ድንጋጌዎችና መመሪያዎች ጋር አብረው መሔድ አለባቸው። ልህቀ ስልቱን፣ አገባቡን፣ ክርክሩንና አካሄዱን ከሀገሪቱ ሕግጋት ጋር ማጣመር ይኖርብናል። ለምሳሌ ካቶሊክ ቻሪቲና ኢንተርናሽናል ሬስኪዩ ኮሚቴ የዓለም ስደተኞችን የሚረዱ ድርጅቶች ናቸው። እነዚህ ድርጅቶች በሶቪየት ኅብረገነን መንግሥት ጊዜ ስለሰው ልጆች መብት መከበር ብዙ ሚና ተጫውተዋል። ሕጉ የሚለው «እነዚህ ከፖለቲካ ነፃ የሆኑ ሰብዓዊ ድርጅቶች ናቸው» ነው። በእርግጥ እነዚህ ከፖለቲካ የነፁ (Santized የሆኑ) ናቸውን? እያንዳንዱ አንባቢ የራሱን ግምጋሜ እንዲወስድ አስገነዝባለሁ። ስለሆነም እኛም እንደነርሱ መርቀቅ ይኖርብናል። በአንድ ሀገር ሁለት ዓይነት ሕግ አይወጣም። በተለይም በዚህ ዴሞክራሲያዊ ኅብረተሰብ ሕጉ ሁሉንም ያቅፋል። እኛም እንደነርሱ ለሰው ልጆች መብት መከበር (ሀገራችንንም ይጨምራል) መታገል እንችላለን። አንዳንድ የሚቃረኑንና አድሎአዊ አመለካከቶች ካሉ ይህን ክልተ–ስፍር (Double Standard) እና ቅጥፈት (hypocracy) ማጋለጥ ይኖርብናል። በተለይ ለዚህ ተሳትፎ ለአንዳንዶቻችን የአሜሪካ ዜግነት ይፈቅድልናል። ሐሳብንም የመስጠት መብት አለን።

ሌላው እኔ መመለስ የማልችለው ጥያቄ አለ። አንዳንድ ግለሰቦች በኢትዮጵያ ማኅበራት ውስጥ አፍራሽና የታወቁ የወያኔ ግልገሎች መግባት አለባቸው በማለት የሚከራከሩና አውቀውም ሆነ ሳያውቁ የሞኝ ፈለግ የሚከተሉ ግለሰቦች አሉ። ይህን የሚሉት ለተንኮል ሳይሆን «ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎን» ለማሳደግ ነው። እዚህ ላይ አንድ መመለስ ያለበት ጥያቄ አለ። ለምሳሌ አይአርሲ(IRC) ራሱን የሚያፈርሱ ግለሰቦችን በውስጡ ያሳትፋልን? በአንፃሩ የወያኔ አባላት ደግሞ ኢትዮጵያዊ የሚለውን ስም ስለማይፈልጉና በአሜሪካ በ«አፍሪቃዊነት» ስም መደራጀትን ስለሚደግፉ ኢትዮጵያዊ የእርስ በእርስ መረዳጃ ማኅበራት አፍራሽነታቸውን እያወቁ እነዚህን ግለሰቦች ማቀፍ አለባቸው ወይ? ይህ አሳሳቢ ጥያቄ ስለሆነ ሁሉም የመሰለውን እንዲተች አስገነዝባለሁ። እዚህ ላይ አንድ አስቸጋሪ ጉዳይ አለ። ይህም አሳሳቢ ጉዳይ ለአሜሪካ መንግሥት ግልፅ አይደለም። እነዚህን ግልገሎች አናስገባም ከተባለ የፖለቲካ መስመር ሊመስል ነው። ከገቡ ደግሞ በሳምንት ውስጥ እንደለመዱት ማኅበራትን ሊያፈራርሱና ሊያናክሱ ነው። ከዚህ አንፃር ሁሉን አቀፍ የኮሚኒቲ ማኅበር እንዴት መመሥረት ይቻላል? የዚህስ መፍትሔ ምንድነው?

ሌላ የሚያሳስብም ሁኔታ አለ። አንዳንድ የወያኔ ደጋፊዎች ደግሞ ኢትዮጵያ የሚል ማኅበር በመመሥረት ኢትዮጵያዊነትን ለማጥፋት የሚታገሉ አሉ። እነዚህ እጅግ የተራቀቁ ምሑራን ናቸው። ተለጣፊ ስማቸው «ኢትዮጵያዊ» ስለሚል ያንን ይዘው ኤርትራውያንና አፍሪቃውያንን በአፍሪቃዊነት የሚያደራጁ አሉ። ግባቸው ፖለቲካዊ ነው። በአፍሪቃዊነታቸውና በአንድነት ተቆርቁረው አይደለም ይህን የሚያደርጉት፤ ኢትዮጵያዊነትን ለመምታት እንጂ። አንዳንዱም በመብት ስም «ሁሉም በብዙኃን ድርጅትና በኮሚኒቲ ያስፈለገውን መናገር ይችላል» በሚል ስም አፍራሽ አስተሳሰቦችንና ጉጂ አመለካከቶችን በማሰረግ ድርጅቶችን ለቦርባሪ ግለሰቦች አጋልጠው የሚሰጡ አሉ። በእነርሱ አባባል «ኢትዮጵያዊ የሚለውን ስም ስለማልፈልግ ስሙ ተሰርዞ አፍሪቃዊ ይባልልኝ» ብሎ አንዱ ቢጠይቅ አይ ይኸማ መብቱ ነው በሚል በሞኝነት ማኅበራችንን ልናፈርሰው ነው ማለት ነው። ለግል ድጋፍና ተቀባይነት ይህን የሚያደርጉ ካሉና ከስህተታቸው ካልተማሩ ወደፊት ታሪክ እንደሚጠይቃቸው ርግጠኛ ነኝ። የዚህስ መፍትሔ ምንድነው?

ወንድሜ ወርቃየሁ!

አዲሱ አስተሳሰባችን ጠላትን ለመምታት የወገን መቻቻል መልማት አለበት የሚለው ነው። ውድቀታችንን መመርመር አለብን። እንደቻይናውያን አባባል «ስምንት ጊዜ ወድቀን አንድ ጊዜ መነሳት» መቻል አለብን። አዲሱ መፈክራችን መቻቻልና ፍቅር ይሁን። ለሀገርና ለወገን ሲል የተቀያየመ ይታረቅ፣ የሚናናቅ ይከባበር፣ የሚገላመጥ በፈገግታ ይተቃቀፍ፣ ወንድሞቹን (እህቶቹን)ና ኮሚኒቲን የሚያንቋሽሽ ካለም ለብሩህ ዓላማ ከእንግዲህ ወዲህ ራሱን ወቅሶ ይተባበር ... እኛ በተራራቅን ቁጥር ጠላት ይቀራረባል፤ እኛ ባለቀስን ቁጥር ጠላት ይስቃል።

አንድ ሊቅ ለባልንጀራቸው ሲፅፉ እንዲህ

ብለው ነበር፦ «በምንም ዓይነት ሁኔታ መቻቻልና መተባበር አለብን። የኅብረተሰብን የዕድገት ሕግ መፈለግ ያስችለን ዘንድና ይህንንም ለመመርመር እንደዚሁም ያለንን ቀኖናዊ አስተሳሰብ ድምጥማጡን ለማጥፋት እባካችሁ እናስተውል፤ ይህንን የምናደርገው በሌላ መመሪያ የሕዝብን ጭንቅላት ለማጠብ አይደለም። ሁሉንም ለመወያየትና መብራት ለማብራት የምታስቡትን ሁሉ እቀበላለሁ። ውይይታችን ልባዊና አስተማሪ ይሁን። ለዓለም የቱን ያህል ተመራማሪዎችና አዋቂዎች እንደሆንን እናስረዳ፤ በመቻቻል እንዴት የወደፊቱን ድልድይ እንደምንመሰርት እንግለፅ። የተሻለ አስተሳሰብ አፍላቂ ስለሆንን ብቻ መቻቻልን አሽቀንጥረን አንጣለው። እንደ አዲስ «ኃይማኖት» ደቀመዝሙር ጉረኛ አንሁን፤ ምንም እንኳ አዲሱ «ኃይማኖት» ሐቀኛና እውነተኛ ቢሆንም እንኳ! ማንኛውንም ተቃውሞና ልዩ አስተሳሰብ በመድረካችን እንቀበል። ነገር ግን ነጣዮችን እንዋጋ፤ ወደ ፍልስፍና ቅዠት አንግባ፣ ለጥያቄዎች በር አንዝጋ። የመጨረሻ ክርክራችንን ብንጨርስ እንኳ እንደገናም በእውነት ምሶሶ ላይ በቆመ ውይይት ንግግራችንን እንጀምር። በዚህ ሁኔታ ብቻ ነው በመድረካችሁ ልሳተፍ የምችለው። አለበለዚያ እኔም አልገኝም»። ይህ ምክር ትልቅ ቁምነገር አለው። እኛም ለዓለም ሕዝብ ብልኃታችንን እናሳይ!

አንጀቴ ወርቃየሁ!

ጊዜ እስኪያልፍ ያለፋል። ለማይረባ ጥቅም ታሪክን መሸጥ አሳፋሪ እንደሆነ የምትረዳው ነው። ከወያኔ የበለጠ የምጠላቸው ታሪካቸውን የሸጡ ሬሳ ሲላክ ብቻ ተኳኩለው ወደ መርዶ ቤት የሚሄዱና ኮሚኒቲዎችንና አብያተ ክርስቲያናትን የሚያሽሟጥጡና የሚንቁትን የእኛን ኔግሮዎችን ነው። ሁላችንም ኔግሮ ነን። እነዚህን ስልጡን መሰልና ሞልቃቃ ቺቹና ቶኒን ስልጣኑ ኖሮኝ በአለንጋ ትንሽ በሀገር ፍቅር ስሜት ብገርፋቸው ምንኛ በተደሰትኩ!! በተለይም የወያኔ የመከፋፈል ስልት እጅግ ተራቆ የከተማ (ያዲሳባ) ልጅና የገጠር ልጅ ብሎ በአሜሪካ በሚከፋፈልበት ወቅት የእነርሱን ተንኮል ባለመረዳት ክፍፍልን የሚያራምዱትን መርካቶ ቀመስ ወገን አድሚ ወንድሞቻችንና እህቶቻችንን ማስተማር አለብን።

ልጅ ወርቃየሁ!!

ጊዜ በገፋ ቁጥር ጥርሱን እያገጠጠ እርቃኑን ስጋውን የቀረው የወያኔና የሻዕቢያ ጥምር አምባገነን መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ አዋርዶ መቀመቅ የመክተት ተግባሩን ግልፅ እያደረገው ነው። ከዚህ በፊት የሚያካሂደውን ድብቅ ግድያ ዛሬ በአደባባይ በማውጣት ባሕታዊ ፈቃደ ሥላሴን ረሸኗቸዋል። የጦቢያ ፀሐፊዎችና አሳታሚዎች በግፍ ወደ ወህኒ ቤት ተጥለዋል። ይህንን ስንሰማ ብዙዎቻችን ከዚህ በፊት ከትጥቅ ትግሉ በፊት የሰላም ትግሉን ማካሄድ ይኖርብናል በማለት የምንወያየው ሁሉ ከእንግዲህ በኋላ መለሳለሱ እንደማያዋጣ የተረዳን ይመስላል። እንግዲህ ጉበዝ «አልዲነክ እኔ እኮ ኤርትራዊ ነኝ» እያለ በእግሩ እየረገጠ የሚያዋርደንን ጠላት በሚያውቃት ቋንቋ ካላነጋገርነው የኢትዮጵያ ሕዝብ በአሳፋሪ ባርነት ውስጥ እየገባ ነው። በሰላም ክርክር፣ በንግግርና በጽሑፍ ብዙ ኢትዮጵያውያን ያላሰለሰ ተቃውሞ ቢያደርጉም ይህ የጉሳ መንግሥት የሰላሙን በር ሊከፍት አልቻለም። እንዲያውም በምዕራቡ ዓለም በሚመራው ፕሮፓጋንዳው «እኛ የምንፈልገው ጠንካራ ተፋላሚን ነው» በማለት ተቃዋሚ ኃይሎች በመለስ ዜናዊ የክልልና የጉሳ አስተዳደር ውስጥ ገብተው በእርሱ ማነቆ እንዲታነቁ ብዙ አሹፏል። ይህንንም በተመለከተ በቅርቡ በኢትዮጵያ የአሜሪካ አምባሳደር የሆኑት ዶክተር ዴቪድ ሺን በወያኔ ልሳን «አብዮታዊ ዴሞክራሲ» የተናገሩት ብዙ ኢትዮጵያዊ የአሜሪካ ዜጎችን አሳዝኗል። በእርግጥም የዚህ ዓይነቱ ንቀትና አነጋገር የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር (State Department) በሚደግፈው ሀገር በጣም የሚደጋገምና የተለመደ ነገር ነው። የአሜሪካ መንግሥት ወያኔን ደገፈ ማለት ወያኔ የሞራል የበላይነቱን ያዘ ማለት አይደለም። «እኛን የሰለጠነው ዓለም ሲደግፈን እናንተ ብቻችሁን ቀራችሁ» በማለት ራሳቸውን የሚያሞካሹ የዘር ካድሬዎች ሊያውቁት የሚገባ ትልቅ ነገር አለ። የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ የተሳሳተባቸው ወቅቶች ብዙ ናቸው (በተለይም በሰው ልጆች መብት መረገጥ)። እንዲያውም በየጊዜው ታግሎ የሚለውጠውና የሚያቃናው ሕዝቡና ኮንግሬሱ ነው። አንዳንድ ምሳሌዎችን እንጥቀስ፤ የአሜሪካ የቀኝ አክራሪ ፖለቲከኞች በብራዚል ጉዳናዎች ለሕፃናት ገዳይ ፖሊሶች የሚሰጡት የሕሊና ፍርድ፣ በጓታማላ በሲአይኤ ቅልብ የጓታማላ ፖሊሶች በአሜሪካን ዜጋ ባል ላይ ለተደረገው አፈናና የነፍስ ማጥፋት የሚሰጡት ክብደት፤ በአሜሪካ ግብር ከፋይና በንግድ ግኑኝነቱ (NAFTA) የደለበው የሜክሲኮ መንግሥት የቺያፓስን ባላገሮች (Indigeneous people of Chiapas) ሲረግጥ የተወሰደው ዲፕሎማሳዊ እርምጃ ያልረባና እንዲያውም አሺፌ መሆኑን ስናይ ዛሬም በኢትዮጵያ ሕዝብ መብት የሚቀልደውን የወያኔና የሻዕቢያ ጥምር መንግሥትን አምባሳደር ሺን ቢያሞግሱ የሚያስደንቅ አይሆንም። የአሜሪካ መንግሥት ዲክቴተሮችን ብዙ ጊዜ ደግፏል። እነሞቡቱን ደግፏል። የሞቡቱ ኬሌፕቶ ክራሲ የብዙ ቢሊዮን ብር ብድር ከአይኤምኤፍና ዎርልድ ባንክ እንዲያገኝ ረድቷል። የአምባሳደሩ የወያኔን

መንግሥት ማድነቅ አያስገርምም። ዱባ ወደ ትርንጐነት እንደማይለወጥ ሁሉ በእርሳቸው ሙገሳ ብቻ የወያኔ መንግሥት ሞራላዊ ሊሆን አይችልም።

የኢትዮጵያ ሕዝብ የውጭ ኃይሎች ፍላጐት ምን እንደሆነ ገና ፓርቱጋሎች ሲገቡ፣ ገና ድሮ የካቶሊክ ቄሶች ምፅዋን ሲቆጣጠሩና ገና በጥንት ጊዜ መጽሐፍ ቅዱስ ይዘው በሰላማዊ መንገድ ሲገቡ ነው ሁኔታቸውን የተረዳው። የአምባሳደሩም ንግግር ሊያስደንቀን አይገባም። አየህ አምባሳደሩ ለአገራቸው ገናናነትና ለራሳቸው ጥቅም የቆሙ ናቸው። የኢትዮጵያን ሕዝብ ለመርዳት ከዮርዳኖስ ባሕር በእግዚአብሔር ተቀብተው ሰባቱን ዓሣ ለሰባ ሺህ ሕዝብ ሊመግቡ አይደለም የመጡት። በጥቁር ሕዝብ፥ «በውጭ እርዳታ»፥ በጥቁር ባሕልና ታሪክ ፥ በዓለም ሰላም፥ በሦስተኛው ዓለምና በብሔራዊ እንቅስቃሴ ላይ የሀገራቸውና የራሳቸው የአስተሳሰብ ሥነልቦናዊ ግንዛቤና ይህንንም የሚያራምዱበት የዴፕሎማሲያዊ የሥራ ድርሻ ሊኖራቸው እንደሚችልና ይህም ከእኛ የተለየ መሆኑን መረዳቱ እጅግ ይጠቅማል። ትናንት የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ በአደሌ ሲተሸንሰንና ዲን አችንሰን የኃይለሥላሴን አስተዳደር በረቀቀ መንገድ በመደገፍ ያደረጉት የፖለቲካ ጫወታ ለዚህ በቅቶ የዓለም ኀብረገነን መንግሥት (Totalitarianism) ከተመታ በኋላ ዛሬ የአሜሪካ ፖሊሲ ከጥቁር የጐሳ ፖለቲካ ጋር ማበሩ እጅግ የሚገርም ነው። የኃያላን መንግሥታት ዲፕሎማሲ በሰው ልጆች መብት ላይ ብቻ ያተኮረ አይደለም። የነሞሎቶቭ፥ የነሪቢንትሮቭ፥ የነዲን ራስክ አሁንም የነኮሐን፥ ዋረን ክሪስቶፎርና ከጥቂት ጊዜ በፊት የተሾሙት እሜቴ ማድሊን አልብራይት ሥራቸውን የሚሰሩት ከሀገራቸው የአጭርና የረዥም ጊዜ ጠቀሜታ አንፃር ነው። በዚህ ሊነቀፉ አይገባም። ማንም ዜጋ ለሀገሩ ክብር መቆም አለበት። እንዲያውም በእነርሱ ልንቀና ይገባናል።

በጣም የሚገርም ነገር ላጫውትህ። በቅርቡ ፕሬዚዳንት የልሲን (የራሽያው) ልቡን በጠና ታሞ ኖሮ ቀዶ ጥገና ተደረገለት። በአንድ ስብሰባ ላይ ሰውነቱ ገርጥቶ እጁ ሲንቀጠቀጥ ያዩት ከፍተኛ የአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ባለሥልጣናት ወዲያውኑ «እኛ ቀጥሎ በሥልጣን ላይ ሊወጣ የሚችለውን ነው መደገፍ ያለብን፥ ሕዝቡን እንደግፋለን፥ ፖሊሲያችን ቀጣይ ነው» ሲሉ ተገረምኩ። ፋሽሽቱ ዥርኖቪስኪም ሥልጣን ቢይዝ የተለመደ ጨዋታቸውን ሊጫወቱ ነው።

«ፖለቲካ ቆሻሻ ጨዋታ» እንደሆነ ሁሉ ዲፕሎማሲም የእርሱ ቅርንጫፍ ነው። በእኔ አመለካከት ሦስተኛው ዓለም የሚካሄድበት ዲፕሎማሲ ጥሩ ልብስ በለበሱና አደብ ገዝተው መልካም ነገር በሚናገሩ ምስለኔዎች በአክብሮትና በፈገግታ በሚያደራድር የገያጅ ግኑኝነት ነው። እንዲያው ስለዲፕሎማሲ ጉዳይ አለፍ አለፍ ብዬ ለማንሳት እንጂ የዛሬው ጉዳዩ አሁንም የሚያተኩረው በብዙኃን ድርጅቶች ምሥረታና ዕድገት ላይ ነው።

ውድ ወንድሜ! የዛሬው ደብዳቤ ትንሽ ደረቅ ሊልብህ ይችላል። ግን ቁምነገር ነው። በብዙኃን ድርጅት በንቃትና በባህል ያልታቀበ ሕዝብ (በተለይም በአሜሪካ) የበታችነት የሚሰማውና ግዴለሽ ሕዝብ ነው። በአሜሪካ ሕዝብ ማንነቱን (identity) የሚያሳውቀውና በሥርዓተ ማኅበሩም ውስጥ በሕጋዊ መንገድ ለመብቱ፣ ለጥቅሙና ለባሕሉ የሚታገለው ዓላማ ባላቸው ማኅበሮች ነው። እንደነዚህ ዓይነት ማኅበራት በምርጫም ስለሚሳተፉ ከፍተኛ ተደማጭነት አላቸው። ከመንግሥት ኮንትራት፣ ብድርና የገንዘብ መደጐሚያንም በማግኘት ተደማጭነታቸውን ያሳድጋሉ፤ ለስደተኞች መብት ይከራከራሉ፤ በቀድሞ ሀገራቸው ለሰው ልጆች መብት ይታገላሉ፤ ጐጂ የመንግሥት አዋጆችንና ፖሊሲዎችን ይፋለማሉ።

ምሳሌዎች፦

1) Anti-Defamation League (ADL) - ለእሥራኤል ሕልውና፥ ለእሥራኤል ሕዝብ ባሕል፣ ደህንነትና የኢኮኖሚ ዕድገት የሚታገል ድርጅት።

2) National Association For The Advancement of Colored People (NAACP) -ለጥቁር አሜሪካውያን መብት፣ ባሕላዊና ኢኮኖሚያዊ ዕድገት የሚታገል

3) Native American Rights Fund - ለባለጉልቱ ነባር የአሜሪካ ሕንዳውያን ጥቅም ጥብቅና በመቆም የሚታገልና የሚያታግል የብዙኃን ስብስብ ነው። ከአሜሪካ ሕንዳውያን በመለስ ይህ ድርጅት ሌሎች በዓላማው ሊተባበሩ የሚችሉትን «ዴሞክራቶችና» ለሕዝብ የሚቆረቆሩ ወገኖችን ያቅፋል።

4) Movements Estudiantil Chicano De Aztlan - በጌቶና ባሪዮ (እሪ በከንቱ) ላሉ ለሜክሲኮአዊ አሜሪካውያን ወጣቶች የትምህርት ዕድል የሚታገል የብዙኃን መድብለ ድርጅት (Umbrella Group) ነው።

5) National Mexican American Anti-Defamation Committee - ይህ ድርጅት በነጩ ቁጥጥር ስር ያሉ የመገናኛ መሣሪያዎች የጥላቻና የንቀት መልዕክት ሲያስተላልፉ ይመክታል፤ ይታገላል። ለባሕል መግባባትና ለመልካም ግኑኝነት ትምህርት ይሰጣል፤ ዘረኞችን ይፋለማል።

6) International League For The Rights of Man - የትም የዓለም ሥፍራ ሕዝብ ሲጨቆን ይሟገታል፤ ለታሰሩ የፖለቲካ ስደተኞች ይከራከራል።

7) Japanese Americans Citizens League - ይህ ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት የጃፓኖች የእሥር

ካምፕ (Concentration Camp) የተወለደ ድርጅት ሲሆን ለኢኮኖሚ ዕድገት፣ ለመግባባትና ጥላቻን ለማስወገድ ይታገላል። ለጃፓን–አሜሪካውያን ዕድገት ይሚገታል።

እነዚህን እንደምሳሌ ጠቀስን እንጂ በአሜሪካ የተመሠረቱት ድርጅቶች ዝርዝራቸው ትላልቅ መጽሐፍት እንኳ አይበቃቸውም። ብዙዎቹ ጠንካራ ድርጅቶች ከመሆናቸው የተነሳ በፖሊሲም ደረጃ ተደማጭነት አላቸው። ሕዝባቸውን ይመክታሉ። ለመብታቸው ይከራከራሉ። ለምሳሌ ሳዳም ሁሴን ላይ በተደረገው ጦርነት ጊዜ አንዳንድ የጠገቡ ዘረኞችና ፖሊሶች ጠጉረ ልውጡን ዐረብ መስል ሲያጉላሉትና ሕፃናቶቻቸውም በየትምህርት ቤት ሲሳቀባቸው ገትሮ የመከተው The Arab American Institute የተባለው ነው። ይህ ድርጅት በእስራኤልና በፍልስጥኤማውያን ግኑኝነትና የፖለቲካ ድርድርም ሳይቀር ሚና ተጫውቷል።

ብዙዎቹ እነዚህ ድርጅቶች ከመንግሥትና ከሐብታም ደጓሚ ድርጅቶች (Foundations) እርዳታ ያገኛሉ። አባሎቻቸውም ሳያሰልሱ መዋጮ ስለሚያዋጡ እንዲያውም ከመንግሥት ከሚያገኙት ገንዘብ የእነርሱ ድርሻ ይበልጣል። እኛ ግን በእውነቱ ደንጊያ ራሶች ስለሆንን ይህ አይገባንም። እነዚህ ድርጅቶች በከፍተኛ ተቋሞችም የራሳቸው የጥናትና የምርምር ክፍል በተለይም የሀገራቸውን የመብት አፈና በሚመለከት ያቋቁማሉ። ጉጂ ፖሊሲዎችንና አዋጆችን በማጋለጥ ለፍትሕ ይታገላሉ። የተጠቀሱት የሙያና የብዙኃን ድርጅቶች ለንዑሳን ዜጎች ዕድገት በአሜሪካ ይህ ነው የማይባል አስተዋፅኦ አድርገዋል። በንግድ መልክ የሀገራቸውን ሕዝብ አሳድገዋል። ብዙዎቹ የቀረጥ ነፃ መዋጮ ስለሚሰበስቡና ተጨባጭ ለውጥም ስለሚያመጡ በሕብረተሰቡ ውስጥ ይከበራሉ። ከሌሎችም ጋር በመጣመር (Alliance, Coalitions) የበለጠ ተደማጭነትን ያገኛሉ።

ወንድሜ ወርቃየሁ!

ዛሬ የወያኔ ትግሬዎችና የኤርትራውያን ማኅበራት በየቦታው እንደአሸን እየፈሉ ነው። አፍሪቃዊ በሚል ስምም ሚና የሚጫወቱት እነርሱ ናቸው። እኛም ከእነርሱ ልቀን የፖለቲካ ትግል ማድረግ አለብን። ለኅብረተሰብ ዕድገት፣ ለሀገራችን ሕዝብ መብት መከበር፣ የኢኮኖሚና የፖለቲካ በደልን ማጋለጥ ፖለቲከኛ መሆን አይደለም፤ ሰብዓዊነት ነው። ለኃይማኖት እኩልነትና በቀሳውስት ላይ የሚደርሰውን በደል መታገል ፖለቲከኛነት አይደለም ሰብዓዊነት እንጂ። የብዙኃን ድርጅት አተጋገል የራሱ የሆነ ሥልትና ጥበብ አለው። ከወርልድ ካውንስል አፍ ቸርችስና ከክርስቺያን ሳይንስ ሞኒተር ይበልጥ የተራቀቀ የብዙኃን ድርጅት ወይም ማኅበር የት ይገኛል? እኛም እንደነርሱ መብሰል አለብን።

የአሜሪካንን የፖሊሲ የውይይት አዝማሚያዊ ማዕከል (Policy concensus) ለኤርትራ መገንጠል በምዕራቡ ዓለም ትልቁን አስተዋጽኦ ያደረጉት ስደተኛን አስመጪና ተንከባካቢ ድርጅቶች ናቸው። ሥራቸውን ግን በግልፅ አይሰሩም። ተደማጭነት ስላላቸው ኩሉኔል መንግሥቱን በመምታት በዕርዳታ ስም በሞራልና በቁሳቁስ ለተገንጣዮች ከፍተኛ ድጐማ አድርገዋል። ግን የሚታወቁት በብዙኃን ድርጅትና በሰብዓዊነት ስም ነው።

ስለሆነም በስደት ላይ ያሉ ታጋይ ወገኖች እስካሁን ያላጤኑት ይህ «የሰብዓዊ» «ፖለቲከኝነትን» ነው። እዚህ ሀገር ቄሱ ሳይቀር ፖለቲከኛ ነው። ከአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ጋርም የተወሳሰበ ነው። በጦርነት ጊዜ ጦርነትን ለመደገፍ ቄሱ መጽሐፍ ቅዱስ ይዞ ጦርነትን ይባርካል። በግልፅ አብያተ ክርስትያናት «ሰብዓዊ ድርጅቶች» ናቸው ይባላል። በውስጥ ለጥቅማቸው ይታገላሉ። ሁሉ ነገር ንግድና ፖለቲካ ነው። ይህንን እነርሱም በረቀቀ መንገድ ስለሚጫወቱ ብልጥ ሰው እንደነርሱ ብልጥ ቢሆንና የእነርሱን ሕግ ቢጠቀም አይቃወሙም። በአሜሪካ የአንድ ኅብረተሰብ (Community) «በሕይወት» መኖር (Survival) ከዚህ ጋር የተያያዘ ነው።

ወገኔ ወርቃየሁ!

እኛ ኢትዮጵያውያን አንጐላችን ልዩ ነው ልበል? በቀላሉ ዋሽንግተን ዲሲ የሚኖር 10,000 ኢትዮጵያዊ እንኳ $200 በአንድ ጊዜ ቢያዋጣ በ$2 ሚሊዮን እንዴት ዓይነት ኢትዮጵያዊ አዳራሽና መሰብሰቢያ ይሠራል መሰለህ። ልጆቻችንን ፊደልና ሥነ–ሥርዓት ለማስተማር፣ ባሕላችንን ለዓለም ሕዝብ ለማሳወቅና የሥራ መስክም ለመክፈት እንዴት የሚያድል መሰለህ። ግን እኛ አይገባንም!! ለዚህ ምን መላ አለህ? በእርግጥም አንዳንድ ሥፍራዎች ሕዝባችን ይሉኝታውና ሁኔታው ስላሳዘነው አብያተ ክርስትያናትን መገንባት ጀምሯል። ነገር ግን ይህ በቂ አይደለም። የአጠቃላይ የብዙኃን ድርጅት በሀገር አቀፍ ደረጃ መመሥረት በሀገራችንና እዚህ ላለው ችግራችን መፍትሔ ይሆናል። ለሚያብሰለስሉን የአንድነት ጥያቄዎች በሩን ወለል አድርጐ ያሳያል፤ ሕዝባችንን ያቀራርባል፤ ለማንባር ምሥረታም አመቺነትን ያመጣል።

የውስጥ የሕዝቦችን ችግርና የፍልሳውያን ዕድገት በመግለፅ የኅብረተሰብ ጥናት ምሑር ሚስስ ፓትሪሽያ ስፒግል እንዲህ ሲሉ ተናግረዋል። «አብዛኛውን ጊዜ ፍልሳውያን (Immigrants) ሕዝቦችን ድርጅት ለመመስረት የሚያስቸግራቸው የገንዘብ እጦት ነው። አንዱ ምክንያት ገንዘቡ ያለው ከነባር ዜጎች ካዝና ነው።

ስለሆነም ለመጀመሪያ ጊዜ በፈቃደኞችና በትንሽ መዋጮ ድርጅትን መመሥረት አስፈላጊ ይሆናል። ሌላው <u>ትልቁ</u> ችግር እነዚህ ፍልሳውያን በሀገሩ እንዴት የብዙኃን ድርጅት እንደሚመሰረት ዕውቀት የላቸውም። የተወሳሰበው ሁኔታ አይገባቸውም። ፍላጐቱ ቢኖራቸውም ወደ ግቡ የሚያደርሰውን መንገድ ላያገኙት ይችላሉ። በሌላም በኩል ደግሞ በከፍተኛ ዕቅዶች ላይ ሊውል የሚገባ ጉልበትና ጊዜ ባልረባና በረባ ጭቅጭቅ ይባክናል። በዓላማ ብቻ መቃጠልና መብሰል አንድ እርምጃ እንኳ በአሜሪካ ወደፊት አያስኬድም። መንገዱን እንደ ንግድ (Business) መረዳት ያስፈልጋል። የብዙኃን ድርጅቶችን መመሥረት ራሱን የቻለ ትልቅ ትግል ነው» ብለዋል። ስለሆነም የእኛ ምሑራንና የኮሚኒቲ መሪዎች ይህን ጠንቅቀው መረዳት ይኖርባቸዋል።

አንጀቴ ወርቃየሁ!

ራሱንና ባሕሉን ሳይወድ የሌሎችን ሥልጣኔ አደንቃለሁ ማለት «እኔ ማንነቴ ጠፍቷል፣ እንደመጋጃ ነኝና ጋልበኝ» እንደማለት ነው። የሌሎች ሀገሮች ልብስ ከእኛ የተሻለ ነው ማለት አይደለም፤ የሀገራችን ፍልስፍና ከአውሮጳውያን ፀሐፊዎች ያነሰ ነው ማለት አይደለም። እኛም ሔገልን፥ ሞዛርትን፥ ዴስካርቴን፥ እንደነግራኞ ማርክስ ያሉ ኮሚዲያንን (ብልሆዎችን)፥ ናፖሊዮንን፥ ሼክስፒርን የሚመስሉ ሊቃውንት አሉን። የመድኃኒት መፅሐፍ (ዕፀ ደብዳቤ)፥ አውደ ነገሥት (Astrology)፥ ሥዕል (Art)፥ የሀገር ባሕል የሕክምና ዘዴዎች፥ የምግብ አሠራር፥ የእርሻ ዘዴ፥ የዲፕሎማሲ ዕውቀት፥ ስነጽሑፍ፥ ኪነት፥ የመጠጥ ዓይነቶች፥ ... ሁሉም ዓለም ያለው አለን። አዲሱ ትውልድ ግን ይህን እያንቋሸሸ ንቆታል። ዛሬ ወጣቱ ትውልድ ፋሽን አድርጐ የሚላጨው ክምክሞ፥ ጋሜ፥ ተረሬ፥ ጉትያና ጉቶ እንኳ ከብዙ ሺህ ዓመታት ጀምሮ በሀገራችን ያሉ ናቸው። በእርግጥም ኢትዮጵያ ውብ ናት። ሎቲ ማንጠልጠሉም ቢሆን ከግዳይ በኋላ ጀግኖች አንበሳ ሰብረው፣ ዝሆን ጥለው የሚያደርጉት ነው፥ የዛሬውን አያድርገውና። ሹሩባ፣ ቆንደላ፣ ጐፈሬ ገና የአሜሪካ አዲሱ አንፃረ—ባሕል (Counter Culture) በ1960ዎቹ ዓመታት ከመፈንዳቱ በፊት ነበር በሀገራችን የነበረው። እነራስ ተፈሪዎች የሚሰሩት የባሕታዊ ዓይነት ፀጉር አሠራር አመጣጡ ከእኛው ነው። ይህንን ማስተማርና ማሳየት መቻል አለብን። የሀገር ፍቅርም የሚጐለብተው ይህንኑ የፎእሕሕልሕ አስዋጽኦ በመረዳት ነው። የምዕራቡን ቆርቆሮ፣ ፕላስቲክና ፍቅር የሌለው በድን የቴሌፎን የመልስ ድምፅ (Answering machine) ስናደንቅ የእኛንም መለስ ብለን በረጋ አእምሮ ማስታወስ አለብን። ጐረቤት ቡና በማይጠጣበት፥ በበር ቀዳዳ በማየት ብቻ ጐረቤትን ማን እንደሆነ ሳንለይ ተሳቅቀንና ፈራ ተባ እያልን በምንኖርበት ሀገር አንዳንዴ ለትዝታም ቢሆን ባሕላችንን ማስታወስ ይኖርብናል። ለራሳችን ማንነትና ክብር እንኳ ብለን ለኮሚኒቲ ግንባታ ብንነሳ ያምርብናል። እኔ ከየት መጣሁ? አባቴ ማነው? እናቴ ማናት? ምንድነኝ ... ይህ ሁሉ ሁሉም የአሜሪካ ዜጋ የሚጠይቀው ጥያቄ ነው። በርግጥም አሜሪካ በዴሞክራሲ ዕድገት ከሁሉም ሀገሮች የተሻለ በመሆኑ የእኛ ድክመት ካልሆነ በስተቀር ባሕላችንን ለማስተዋወቅ፣ ኮሚኒቲ ለመገንባትና ብሎም ከሌሎች የሕዝብ ክፍሎች ትምህርት ለመውሰድና ለመርዳት መንግሥት ራሱም በገንዘብ ሳይቀር ይረዳል። በዚህ በዴሞክራሲያዊና በመብት ሀገር ባሕላችንን፣ እምነታችንና ማኅበራችንን ካላሳደግን የትም ሊሳካልን አይችልም። የአሜሪካንንም የዜግነትና የነዋሪነት ተሳትፎ ማክበር አለብን። ልባችን ከውዲቷ ኢትዮጵያ ጋር ቢሆንም ሕገ መንግሥቱ በሰጠን መብት ተጠቅመን ለዴሞክራሲ መታገል ይኖርብናል። በዚህ አጋጣሚም የዚህን ትልቅ ሀገር ስጦታ በቀላሉ ማየት የለብንም። በሀገራችን የማናገኘው መብት እዚህ እንዳለ መረዳት ይኖርብናል። ምስጋናችንን በዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ መግለፅ አለብን። በኢትዮጵያና በአፍሪቃ ላይ የተዛባ አቋም የሚወስዱትን አሜሪካኖች በምርጫ ወቅት አንምረጥ። እንዳይመረጡም እናስተባብር። ይህ መብታችን ነው።

ውድ ወንድሜ!

ካለመታከት ብዙዎቻችን የኮሚኒቲን መደራጀት ወረቀትና ጊዜን በማባከን የምንፅፈው ልዩ ጥቅም ስላለን ወይም ጠላቶቻችን እንደሚሉት በፖለቲካ ብቻ ሕዝባችንን ለማሰለፍ አይደለም። አንድ ታሪክ ያለው ሕዝብ በአሜሪካ የራሱን ማንነት (identity) ማሳወቅና ችግሮቹንም እንደሌሎች የኅብረተሰብ ክፍሎች አብሮ በጋራ መወጣት አለበት። ሌላ አሚሽ (Amesh) መሰል የተገነጠለ ኅብረተሰብ መመሥረት አለብን ማለት አይደለም። እንደሀገሬው ነዋሪ ሕዝብ መብታችን በሚፈቅደው መሠረት እኛም ጠቃሚ ባሕል እየወሰድን የእኛንም በመስጠት እርስ በእርሳችን እንማማራለን ከሚል ነው። በተለይም እንደሌሎች ንዑሳን ዜጐች የቀኝ አክራሪ የፖለቲካ አዋጆች እኛንና ቤተሰቦቻችንን በሚጐዱበት ወቅት አብረን በአንድ ላይ ድምፃችንን ማሰማት ይኖርብናል ከሚል ነው። በሀገራችንም ላለው የመብት አፈና፣ የጋዜጠኞች መታሠር፣ የመምህራን ማኅበር መሪዎች መንገላታት በአንድነት የተቃውሞ ድምፅ ማሰማት እንችላለን። ማንኛውንም በአሜሪካ ያለ የኮሚኒቲ ማኅበር የሚያደርገውን ሁሉ ማድረግ እንችላለን። ከሌሎች ጋር የጋራ መድረክ በመፍጠር

(Coalitions) ለንዑሳን ዜጎች ጉጂ የሆኑ ፖሊሲዎችን ማስቀየር እንችላለን። ኤሽያኖች፣ ሒስፓኒኮች፣ የአይሁድ ዜጎች፣ የአሜሪካ ጥቁር ነዋሪዎች፣ የአሜሪካ ሕንዶች(Chicanos, American Indians)፣ ሴቶች፣ የሕፃናት ተከራካሪ ድርጅቶች፣ የሽማግሌና አረጋዊ ተቋሞች፣ የተፈጥሮ ተንከባካቢ ጠበቃዎች (Environmentalists)፣ የእንስሳት መብት ተከራካሪ ግለሰቦች(Animal Right Activists)፣ የአካለ ስንኩላን ማኅበራት፣ የኤይድስ በሽተኞች ማኅበር ... ሌላው ቀርቶ የወፋፍራም (ቦርጫም) ግለሰቦች ጥቅም አስጠባቂ ድርጅቶች ... ወዘተ ... የሚታገሉት ለመብታቸው ነው። ለዚህም የሀገሪቷ ዴሞክራሲያዊ ተሳትፎ ለሕገመንግሥቱ (constitution) ተገቢውን አክብሮትና ምስጋና እሰጣለሁ።

በእርግጥም ደቦን፥ አፈርሳታን፥ የፅዋ ማኅበርን፥ ዕቁቡን፥ በጎብረት አዝመራ መከወንን፥ ጋዳን፥ ኃዘን(ልቅሶን) መካፈልን፥ ሰንበቴን፥ እድርን የመሳሰሉና ከሀገር ባሕላችንና ኃይማኖታችን ጋር የተቆላለፉ የብዙኃን ስብስቦች በታሪካችንና አሁንም በሀገራችን ቢኖሩም እዚህ ያለው ስደተኛ እነርሱን እንኳ በማሳደግ በማንነቱ (identity) የተፈለገውን ያህል ሊደራጅ አልቻለም። እየቆየ ማንነቱ እየጠፋው ሲሄድ ብቻ ነው ታሪኩን እንደገና በአእምሮው የሚከልሰው። ስለዚህም ነው ለኮሚኒቲ ግንባታ ሌት ተቀን የሚለፉት አብዛኞቹ ከ5 ዓመት በፊት የመጡ ኢትዮጵያውያን ናቸው የምለው። ኮሚኒቲን ለመገንባት የማያስችሉን ድክመቶቻችን ምንድናቸው?

1) በዘመኑ ስልጣኔና ረጋ ሠራሽ ባሕል ውስጥ የገቡ ወጣት ኢትዮጵያውያን የሀገራቸውን መልካም ባሕልና ታሪክ የሚያስተምራቸው የተጠናከረና የተደራጀ የኢትዮጵያውያን ማዕከል ባለመኖሩ ባሕላቸውን ኋላ ቀርና አሮጌ ወይም ያልሰለጠነ አድርገው ስለሚመለከቱና የእነርሱም ተሳትፎ ባለመኖሩ፤

2) መብትን ተጠቅሞ የራስን ሰብዓዊ ድርጅት አቋቁሞ ስደተኞችን በማስመጣት፣ ግልጋሎትና ሥራ በመክፈት ግፉዓንን ከመርዳት ይልቅ በትላልቅ አስመጪ ድርጅቶች መመካትና የራስን መናቅ፣ በነጭ ድርጅቶች ማመንና የአሜሪካ የዜግኝነት ግዴታን አለመወጣት፤

3) አንድ ግለሰብ ከአንዱ የኮሚኒቲ አባል ከተጣላ በእርሱ የተነሳ ማኅበሩን ለማናጋት መሞከር፣ ለማፍረስ መጣር፣ አሉባልታ ማስራጨትና ኮሚኒቲ እንዳይኖርና ሕዝብ እንዳይስማማ ማድረግ። እንደዚህ ዓይነቱ ሁኔታ በሁሉም የስደተኛ ክፍሎች ላይ ቢታይም «መራራዋን ሒስ እንዋጣትና» በኢትዮጵያውያን ላይ ጉላ ብሎ እንደሚታይ በርካታ በኮሚኒቲ አካባቢ የሚሰሩ አሜሪካውያን ይናገራሉ። እስካሁን ትብብራችን በጥሩ ሁኔታ የሚታየው ሰው ሲሞት ሬሳ ለመላክ ገንዘብ ስናዋጣና 12 ፓክ ኮካ ኮላ ይዘን ተኳኩለን ለቅሶ ስንደርስ ብቻ ነው። በአንዴ 500 ሆነን $10,000 ሬሳ ለመላክ ማዋጣት ከቻልን መፍትሔው በወር እንኳ $20 ብር በማውጣት ኮሚኒቲ ብንገነባ ጥቅሙ የት እየለሌ ነበር። ሰው ሲሞትም ገንዘብ በየጊዜው ከማዋጣት ሳይሞት አዋጥቶ ማስቀመጥና እርሱንም በሕይወት እያለ መርዳት ከሞተም በኋላ ሳንጨነቅ ለቀብሩ ብናስብ አይሻልምን? ምነው እንደዚህ ደንጊያ ራሶች ሆንን? እርሱንስ ከመሞቱ በፊት ኮሚኒቲ መስርተን $20 በወር ለሞትና ለቀብር ኢንሹራንስ እንዲከፍል በማድረግ ድኃ ዘመዶቹ ከድህነት እንዲላቀቁ ማስተማር ቀላል አይደለምን? ታዲያ ሁኔታው ቢኮረኩረን እንደገና ልድገመው-እኛ (እኔንም ይጨምራል) ድንጋይ ራሶች ካልሆን ማነው ድንጋይ ራሱ በአሜሪካ?

ከላይ የጠቀስኩት የግለሰብና የኮሚኒቲ ጠብን አንድ በማድረግ ኮሚኒቲንና ድርጅቶችን ማፈራረስ በእርግጥም እጅግ አሳፋሪ ነው። ለኮሚኒቲና ለሀገር እየቆሙ ግለሰቡን አስወግዶ መታገል ትልቅ ቁምነገር ነው። እዚህ ላይ መግለፅ የምፈልገው አንዳንድ «ከፈሳቸው የተጣሉ» የሚመስሉ ከሕዝብና ከኮሚኒቲ ባልረባ ነገር ሲቀያየሙ ግለሰቦችን የጉዱ ይመስል ከወያኔ የስለላ ድርጅት ጋር ይተባበራሉ። ድርጅቶችን ይቦረቡራሉ። የ«ዘመነ መሳፍንት» ጊዜን የድንጋይ ፖለቲካ በመጫወት ሕዝብን ይበታትናሉ። የራሳቸንም ክብር ደምስሰው ማንነታቸውን ያጫጫሉ። በምቀኝነት ቅዠትና ልክፍት ተልከፈው በስልክ ስብቅና ወደባሰ ጥፋት ራሳቸውንና የዋህ ተከታዮቻቸውን ይዘው ይጠፋሉ።

4) በግል ገንዘቤ የኢትዮጵያ ሬስቶራንት፣ ወይም የኢትዮጵያ የጉዞ ወኪል ባቋቁምና በገንዘቤ ኃይል ማንኛውንም ኢትዮጵያዊ ብበዘብዘው ሳንቲም ታህል ጥያቄ አይነሳም። ችግሩ የሚመጣው የጋራ ኮሚኒቲ ወይም ድርጅት ሲቋቋም ነው። ጥሩ እየሰራም ኮሚኒቲ ወይም ድርጅት የብሶት መወጪያና የጥላቻ ዒላማ ይሆናል። ይህ ለምን እንደሚሆን ከአቅሜ በላይ ስለሆነ ሌሎች ምሑራን እንዲያብራሩልኝና ፈራ ተባ እያሉ የይስሙላ ጥናት ሳያደርጉ እውነተኛውን ምርምር እንዲያደርጉ እጠይቃለሁ።

5) <u>በፈቃደኛነት የማገልገል የስደት ባሕል</u> — በእርግጥ በአሜሪካ በርካታ ሥፍራዎች በፈቃደኝነት በስደት ወገናቸውንና ሀገራቸውን የሚረዱ ጥቂት አኩሪ ወገኖች አሉ። እነዚህ ግን በምቀኝነት፣ ብሶትን በማሳበብና የወያኔ የጥላቻ ዒላማ በመሆናቸው የተፈለገውን ያህል ሕዝባችንን አላሰባሰቡም። ማንም ዱርዬ ተነስቶ ይዝትባቸዋል ይሰድባቸዋል። እንደእውነቱ ከሆነ ፥ እንደነኢትዮጵያ ሬጅስተር፥ ላንዳፍታ፥ ሪቪዩ፤ እንደነኢሕአፓ፥ኅብረ ሕዝብ፥ መድህን የኢንተርኔት ተሳታፊዎችና ሌሎችም በአጭር ጊዜ ለሕዝባችን

የተሟገተ ድርጅት የለም። ጠላትም ሲኮረኩማቸው ወገንም ያዳክማቸዋል። ምሁሮቻችንና ታጋዮቻችን ላይ ምን ሠራችሁ እያለ ሁሉም ያንጓጥጣል። ታጋዮቻችን እንደሌሎች ብቸኛ የገንዘብ አጋሰስ መሆን አቅቷቸው ነው በወገንና በሀገር ፍቅር ሌት ተቀን የሚባዝኑት? እነርሱስ ሳይሰደቡና ሳይጠሉ የፈቀዳቸውን ደግፈው ድምፃቸውን ሳያሰሙ በድሎት መኖር ከብዷቸው ነው ሌት ተቀን የሚንቋሸሹት? የኢትዮጵያ ታሪክና ሀገር የእነርሱ ብቻ ናቸውን? እንዲያውም ቤተሰቦቻቸውም ሆኑ እነርሱ በኃይለሥላሴና በደርግ ጊዜ የተሰቃዩ፣ አሁንም ያ ሁኔታ ሳይሰማቸው ሌት ተቀን ለኢትዮጵያ አንድነትና ዕድገት፣ እንደዚሁም ይህ የመጣው ጭለማ እንዲወገድ የሚባዝኑ አኩሪ ሀገርና ወገን አፍቃሪዎች አሉ። እነዚህን ማስቀየም ማለት ኢትዮጵያንና ሕዝቦቿን መክዳት ነው። ለፖለቲካ ድርጅቶች፣ ለኮሚኒቲ ማኅበራትና ለአብያተ ክርስቲያናት አምስት ሳንቲም ሳያወጣ ጥቅሙንና ክብሩን ግን አብሮ እየተቋደሰ በጉን የሚያፈርስ አፍራሽ ሞልቷል። ይህ የወገን ወቀሳ ስለሆነ ብዙዎቻችሁ ይህን የምታነቡ ኢትዮጵያውያን ሊሰማችሁ ይገባል፤ እኔም ይሰማኛል። ይህ እንግዲህ የእኛ ጉድ ነው ወርቃየሁ!

ሌላው ደግሞ በአንዳንድ ስፍራ ምሑራዊ ትምክህት (Intellectual Chauvinism) አለ። በኢትዮጵያ ሬጅስተር፣ በላንዳፍታም ሆነ በኢንተርኔት የማያስተምሩ፣ ነገር ግን ተደብቀው በተፃፈው ላይ የትችት ምላሳቸው የማይታክተው የጋን መብራቶች አሉ። በዚያ ሰሞን የአድዋን በዓል ስናከብር በኢንተርኔት «እኛ ያልተሳተፍንበት የድል በዓል ምን ይረባል?» ብሎም ያሾፈ የምሑር ሞልቃቃ ነበር። ምሑሮቻችን የቀለምና የርዕዮተ ዓለም ሽኩቻቸውን ትተው በአንድ ዓላማ ሀገራቸውን ከዚህ ጭለማ ለማላቀቅ መታገል ይኖርባቸዋል። ከቻሉ ሺህ «ላንዳፍታን»፣ ሺህ «ኢትዮጵያ ሬጅስተርን» ... ቢመሰርቱ ማንም መቃወም የለበትም። ለሀገር የሚታገሉ መጽሔቶች እንደ አሸን ቢፈሉ ሁሉም መደገፍ አለበት። የመከሊት የውድድር ፈሊጥ ይዞ ትግሉን ማዳከም አይገባም።

ባለፈው ጊዜ እንደገለፅኩት ከእኛ ጉድ ሌላ የወያኔ የስለላ ድርጅትም አጋጣሚዎችን በመጠቀም እርሱም አቁስሎናል። ብርቅዬ የኢትዮጵያ ልጆችን መነጠል ሲያቅተው በሕዝብ ለማስጠላት የኔው አባላት ናቸው በማለትና ውዥንብሩን (disinformation) በመርጨት እኛን ይከፋፍለናል፤ ብሩህ ታጋዮቻችንን ወደ ብቸኝነት ዓለም ያስከበልላል። በቁሶች ቀረቤታና በቤተክህነት እምነት በመጠጋትና በመጠቀም ሕዝባችንን ይከፋፍላል። በጉንደር፣ በጉጃም፣ በገጠሬ፣ በከተማ፣ በጉረቤትና በተማሪ/ባልተማረ በመከፋፈል የወያኔን ፖሊሲ የሚያራምድ ጥቂት ይሁን እንጂ አልፎ አልፎ የሚታይ ዕድሜ ልኩን ሕዝብን በምቀኝነት በመከፋፈል የሚኖር እንዳለ ይነገራል። እኔም እንደዚህ ዓይነት ግለሰብ አጋጥሞኛል። ከከፋቱ የተነሳ ይኸ የሰው ልጅ ሳይሆን ታይቶ የማይታወቅ ቃል የሌለው ከፋፋይ የጉርጥ ዘር ነው ያሉም ነበሩ። ብቻ የእኛ ጉድ ተዘርዝሮ አያልቅም። ይህንን የምንወያየው መፍትሔ እንዲገኝ ከሆነ ሁላችንም በኮሚኒቲና በግንባር ምሥረታ ወይም ግንባታ ላይ መፍትሔዎችን መጠቆም አለብን። ሁሉንም ከዚህ በፊት በወጡት የደብዳቤ ልውውጣችን ነካክተናል።

ውድ ወርቃየሁ!

አብዛኛው የእኛ ነገር ሲያስለቅሰን አንዳንዴ ደግሞ እጅግ ያስገርመናል። በሽታችንን ካላወቅን መድኃኒታችንን አናገኝም። ስለብዙኃን ድርጅትና የኮሚኒቲ ማኅበር ይህ የመጨረሻው ክፍል ነውና በሚቀጥሉት ደብዳቤዎች በሌሎች አርእስት አተኩራለሁ። «አለባብሰው ቢያርሱ ባረም ይመለሱ» ይላሉ አበው ሲተርቱ። በስደት ላይ መራር ነቀፌታንም መቅመስ አለብን። ለኮሚኒቲ አለመጠናከር ሁላችንም አስተዋፅኦ አድርገናል። ጉዳችን ብዙ ነው፤ ይህ የቤተሰብ ወቀሳ ስለሆነ ሁሉም በየፊናው መተከዝና ማሰላሰል አለበት። በዚህ ደብዳቤ ያልተነካ ካለ ኢትዮጵያዊ ነው ለማለት ያዳግተኛል። ስህተታችንን ከተረዳን መፍትሔው ቀላል ነው። መፍትሔው ከተገኘ ብርኃን ይመጣል። ጭለማ ይወገዳል። ብቻ ተስፋችን እንዳይጨልም!!

እነሆ ትንሽ ግጥም፥

## ምነው ባክህ ደግሞ

ምነው ባክህ ደግሞ ከጠላት አይለህ<br>
ያባትን አደራ የናትን ጡትን ነክሰህ<br>
ምንም ላያልፍልህ የጉሪጥ ተያይተህ<br>
በታሪክህና በአንተነትህ ዘምተህ<br>
ተሳቀብህ አሉ አርፈህ አንቀላፍተህ።<br>
ዘመዶችህ ታስረው ጣሪያ ሲሰቀሉ<br>
በጉሳ ተሳደው እንዲያ ሲበደሉ<br>
በዘር ሲቀቀሉ<br>
ተንጓለው ሲጣሉ፤<br>
ብሶታቸው ከፍቶህ፣ አንተም አንድ ካልመከርክ<br>
«ደመላሽ ነኝ» ብለህ፣ «ደርሻለሁ» ካላልክ<br>
የአንተ ኢትዮጵያዊነት በማንስ ሊተረክ<br>
እንዲያው በል ይከተት ላገር አትባረክ።

ቸር ይግጠመን<br>
ገብርዬ (አትላንታ/ጆርጂያ)

# የሲቪክ ማህበረ-ሰቦች (የብዙሃን ድርጅቶች) አስፈላጊነት

ጌታቸው በጋሻው ከሚሽጋን

ጽሁፎቻቸው እንደስሞቻቸው ያማሩት ገብርዬ፣ ወርቃየሁና ይግለጡ ሰላምታና ሀሳብ የሚለዋወጡበትን አምድ አስቀድሜ ሳላነብ ወደሌሎቹ አምዶች ያለፍኩበት ጊዜ ትዝ አይለኝም። ምንም እንኳዋን በእነዚህ ፀሀፊዎች ደረጃ ጥራትንና ለዛን በተላበሰ የሰላምታና ሀሳብ ልውውጥ ውስጥ ባልገባም፣ እነርሱ ከሚለዋወጡአቸው መልእክቶች ውስጥ ብዙ ብዙ ቁምነገሮችን የተማርኩ መሆኔን ለመደበቅ አልፈልግም። በደፈናው ላመስግናቸው እንጂ የተማርኩአቸውን ቁምነገሮች እዚህ ላይ ለመዘርዘር ይከብደኛል። ዛሬ ግን፣ እንደወትሮዬ አንብቤ፣ ተምሬና መርቄአቸው እንዳላልፍ ገብርዬ በላንዳፍታ 5ኛ አመት ቁጥር 4 ላይ ለወርቃየሁ የፃፈው ሰላምታ በጣም ኮረኮረኝ። የእርጐ ዝንብ አትበሉኝና፣ እኔ ብቻ የምጨነቅበት ይመስለኝ ስለነበረው ሲቪክ ማህበረ-ሰብ (ወይም በተለመደው አነጋገር ብዙኃን ድርጅት) አንስቶ ስለተቸ ነው በእነርሱ የሰላምታ ልውውጥ መሐል ራሴን የምዶለው። ዛሬ፣ አገራችን፣ እንደ አገርና እንደ ግዛት፣ ከአሁን ቀደም እንደምናውቃት ለመቀጠል መቻልዋን እርግጠኛ ባልሆንበት ወቅት፣ ብዙውን ጊዜ እኔን የሚከነክነኝ፣ ነገር ግን ብዙዎቹ የእኛ ሰዎች ደግሞ ያልተጨነቁበት የሚመስለኝ፣ ማህበራዊ ጉዳይ የዚሁ የሲቪክ ማህበረሰብ ጉዳይ ነበርና ያለአግባብ በሰዎች ጨዋታ መሃል ገብቼ ከሆነ ገና ከወዲሁ ይቅርታ እጠይቃለሁ። ሲቪክ ማህበረሰቦች በወደፊቱ የአገራችን ዕድል ላይ የሚኖራቸው ሚና ከፍተኛ መስሎ ስለሚታየኝና ጉዳዩ በተደጋጋሚ ከተለያዩ አቅጣጫዎች ሊመረመርና ሊነገር ይገባዋል ብዬ ስለማምን ባወጣው ያውጣኝ በማለት በጨዋታቸው መሀል ጥልቅ ብያለሁ።

ብዕሩ ይለምልምና ገብርዬ፣ ሲቪክ ማህበረሰቦች በተለያዩ ወቅቶች ለተለያዩ ህብረተሰቦች ያደረጉአቸውን አስተዋፅኦዎች ታሪክን በማስደገፍ ጠቆም ጠቆም አድርጎልናል። እንዲሁም፣ እኛ ኢትዮጵዊያን ሲቪክ ማህበረሰቦችን ለመፍጠርና ለማጠናከር ለምን እንዳልቻልን ሊሆኑ ይችላሉ ብሎ የሚያስባቸውን ዋና ቀና ምክንያቶች (ወደፊት በማስረጃ አስደግፎ ሊያቀረብልንም ቃል ገብቶአል) እንደተረዳቸው በየመልካቸውና በየፈርጃቸው ዘርዝሮልናል። ጥሩ አጀማመር፣ መልካም አካሄድ። ከላይ እንዳልኩት የሲቪክ ማህበረሰቦች ጉዳይ በጣም ጠቃሚ ነጥብ ነውና፣ በተደጋጋሚ ከተለያዩ አቅጣጫዎች እንነጋርበት፣ ሃሳቡንም እናዳብር። በመጀመሪያ ግን ሲቪክ ማህበረሰቦች በአንድ ህብረተሰብ የፖለቲካና ማህበራዊ ህይወት ውስጥ ምን ያክል ሚና ሊጫወቱ እንደሚችሉ ተጨማሪ የቅርብ የታሪክ ዋቢዎችን በመጠቃቀስ ገብርዬን ልርዳ።

ግልፅና ድብቅ የሆኑት የምዕራቡ አለም ዕርዳታ የሚናቁ ባይሆኑም፣ ሶሻሊስት ተብለው ይጠሩ በነበሩት የምስራቅ አውሮፓ አገሮች ውስጥ፣ በጣም ጠንካራ ናቸው ተብለው ይገመቱ የነበሩትን መንግሥታዊ ኃይሎችና አውታሮች የጣሉትና በአዲስ ማህበራዊ ስርዓቶች ለመተካት የበቁት በድብቅ የተደራጁትና በለውጡ ሂደት ውስጥ የተፈጠሩት ሲቪክ ማህበረሰቦች ናቸው። በደቡብ አፍሪቃ፣ ከኤ ኤን ሲ የትጥቅ ትግል ባላነሰ ደረጃ፣ ለኤ ኤን ሲ ህቡእዊ እንቅስቃሴ ከለላ የሆኑትና የዘረኛውን መንግሥት ለማንበርከክ ከፍተኛውን ሚና የተጫወቱት በኤ ኤን ሲ ዙሪያና ከኤ ኤን ሲ ነፃ ሆነው የተደራጁት ከሃምሳ የሚበልጡት ሲቪክ ማህበረሰቦች ናቸው። የፍልስጤምን ህጋዊ ህልውና አላውቅም ስትል የነበረችው እስራኤል ተገዳ ወደ ድርድር ጠረጴዛ እንድትቀርብና የፍልስጤምን ህጋዊ ህልውና እንድትቀበል ያስገደዳት ራሱን በፍልስጤማውያን እንትፋዳ የለጠው በርካታ የፍልስጤማውያን ሲቪክ ማህበረሰቦች ህብረት ነው። በአገራችንም ሁኔታ የወያኔን መንግሥት ባህሪና ምንነት በየዕለቱ ለአለም ህብረተሰብ እያሳዩ ካሉት ማህበራዊ ኃይሎች መሀል ከፍተኛውን ስፍራ ይዘው ያሉት በኢትዮጵያ ሰራተኞችና በኢትዮጵያ መምህራን የተመሰረቱት ሲቪክ ማህበረሰቦች ናቸው። ብዙ ብዙ ምሳሌዎችንና ዋቢዎችን ከአለም ዙሪያና ከራሳችን አገር ሁኔታ ለማቅረብ ይቻላል።

ገብርዬም እንዳሳየው፣ የእነዚህ ሲቪክ ማህበረሰቦች አስተዋጽኦ በፖለቲካው መስክ ብቻ የተወሰነ ሳይሆን ሁለ ገብ ማህበራዊ ጉዳዮችንና ክንዋኔ እንደሚያጠቃልል ልብ ማለቱ ጠቃሚ ነው። ከላይ የጠቀስኩአቸውን ዋቢዎች በፖለቲካ እንቅስቃሴ ዙሪያ የከለልኩበት ምክንያት አሁን አሉን ለምንላቸው ሁለገብ ማህበራዊ ችግሮች ቁልፍና መሰረት ናቸው ብዬ የማምነው ል ተብለው የሚጠቀሱት የፖለቲካ ችግሮች ስለሆኑ ብቻ ነው። ሲቪክ ማህበረሰቦች በሙያ፣ በፆታ፣ በእድሜ፣

በሃይማኖት፣ በጥቅም፣ በጤና፣ በዘር/በጐሳ፣ በአካባቢ፣ ወዘተ ሊመሰረቱና ሊሰሩ ይችላሉ። እንዲያውም፣ እኛ ዛሬ ስምና መልክ ሰጠናቸው እንጂ፣ ሲቪክ ማህበረሰቦች፣ ከጥንት ጥንት ጀምረው በተለያዩ ማህበረሰቦች ውስጥ ግልጥና የተወሰኑ አላማና ተግባር ይዘው ሲሰሩና ሲሰራባቸው የኖሩ ማህበረሰባዊ ክስተቶች ናቸው። የማህበረሰቦቹ አላማና ተግባር እንደ ህብረተሰቡ ቁሳዊና ስነልቡናዊ የእድገት ደረጃ መጠናዊ ልዩነቶች ቢኖራቸውም፣ ግልጋሎታቸው የመሰረቱትን አባላት ወይም ህብረተሰብ ክፍል ጥቅምና ደህንነት ማሙዋላት ነው። ስለዚህ፣ የሲቪክ ማህበረሰቦችን አስተዋፅኦ በፖለቲካ መልኩ ብቻ ብናወሳ ሌላ ትርጉም ሳይሰጠው እንዲያው በችግራችን ብቻ ላይ ለማተኮር እንደሆነ ግልጥ ቢሆን መልካም ነው።

የሲቪክ ማህበረሰቦች ሚናና ተግባር እንደማንኛውም የህብረተሰብ እንቅስቃሴ የሚወሰነውና የሚለካው ያንን ህብረተሰብ በወቅቱ በሚገልጡት ዋና ዋና ግንኙነቶችና የፖለቲካ ሁኔታዎች ነው። ይህም ማለት፣ አንድ ህብረተሰብ በሰላማዊና የተረጋጋ ማህበራዊ ዘመንና በችግር ወይም በቀውጢ ዘመን የሚኖረው የሲቪክ ማህበረሰቦችና እንቅስቃሴዎች አንድ አይሆኑም ማለት ነው። ለምሳሌ ያህል፣ ዛሬ የኢትዮጵያ የሰራተኞች ማህበር እንቅስቃሴ ይዘትና አላማ መሆን ያለበት፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ የተረጋጋና ህዝባዊ ድጋፍ ያለው መንግሥት ቢኖር ሊሆን ከሚገባው የተለየ ይሆናል ማለት ነው። ምንም እንኳ ማህበረሰቡ የሰራተኛውን መደባዊ ጥያቄዎች የሚያነሳ ቢሆንም፣ ጥያቄዎቹ ከመሰረታዊው ፀረ የጎሳ ክፍፍልና አድልዎ ጋር በጥብቅ ይያያዛሉ፣ ከስትራቴጂያዊው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና ጥያቄ ጋር ይተሳሰራሉ። በዘር መድልዎና በጎሳ ፖለቲካ ላይ ያልተመሰረተ፣ በአንፃሩ የመላ ኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም የሚያስጠብቅ የተረጋጋና ህዝባዊ ድጋፍ ያለው መንግሥት ቢኖር ግን፣ የሰራተኛው ጥያቄ የሚያተኩረውና የሚሽከረከረው በሰራተኛው መደባዊ ጥቅምና ፍላጎት ዙሪያ ብቻ ይሆናል።

በእኔ አስተያየት፣ የአብዛኛው ኢትዮጵያውያን አስተያየትም ይመስለኛል፣ ዛሬ በኢትዮጵያ የተከሰተው የፖለቲካ ስርዓትና ሁኔታ ከምንጊዜውም የከፋና የኢትዮጵያን ብሄራዊ ህልውና ያናጋ ክስተት ነው ብዬ አምናለሁ። እንዲሁም፣ የዚሁ ሁኔታ መለወጥ ደግሞ የአብዛኛው ኢትዮጵያውያን ፍላጎት ነው ብዬም አምናለሁ። ነገር ግን፣ ይህ በውሁዳን በኢትዮጵያ ላይ የተጫነው የጨለማ ዘን ሊገፈፍ ያልቻለው፣ ከፖለቲካ ድርጅቶች ውስጣዊ ድክመትና ከውጭ መንግሥት ጣልቃ ገብነት ባሻገር፣ ጥያቄዎቻቸውን ከመሰረታዊው ፀረ የጎሳ ክፍፍልና አድልዎ ጋር በጥብቅ የሚያያይዙና ከስትራቴጂያዊው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና ጥያቄ ጋር የሚያስተሳስሩ የሲቪክ ማህበረሰቦች ማነስና አለማደግ ይመስለኛል።

የሲቪክ ማህበረሰቦች ካልበዙና ካላደጉ ደግሞ ብዙ ችግሮች ሊገጥሙን እንደሚችሉና ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና የሚደረገው ትግል እምርታዊ እድገት ለማሳየት እንደሚቸገረው መገመት ትንቢተኝነት አይመስለኝም። ጊዜው የከፋ ሆነና፣ የሲቪክ ማህበረሰቦች መበራከትና ማደግ ሊያስገኙ የሚችሉአቸውን ጥቅሞች ይረዳሉ ተብለው የሚገመቱ የአንድነት ኃይል ድርጅቶች እንኳዋን ብዙ እንቅፋቶችን መፍጠራቸው ይስተዋላል። የሲቪክ ማህበረሰቦች ለፖለቲካ ስልጣን ስለማይታገሉ፣ ማንኛውንም ድርጅት የሚመለከቱትና የሚለኩት ከወገናዊ ጥቅማቸውና ከተመሰረቱበት አላማ አንፃር ብቻ ነው። እነኝህ የፖለቲካ ድርጅቶች ደግሞ የሚታገሉት ለፖለቲካ ስልጣን ስለሆነ የሲቪክ ማህበረሰቦችን የሚለኩት የቱን ያህል በታማኝነት እንደሚያገለግሉአቸው፣ የገንዘብና የማቴሪያል ድጋፍ እንደሚሰጡአቸውና ለፖለቲካ አላማቸው የማስተላለፊያ ሰንሰለት እንደሚሆኑላቸው ነው። በመሰረቱ፣ ማህበራዊ ስርአቱ የተረጋጋና ሰላማዊ ከሆነ፣ እነኝህ ፍላጐቶች ሰላማዊና ዴሞክራሲያዊ መፍትሄ የሚሹ ተፃራሪ ፍላጐቶች ናቸው። ነገር ግን፣ ዛሬ ያለንበት ስርአት ሰላማዊና የተረጋጋ ስላልሆነ፣ በፖለቲካ ድርጅቶችና የሲቪክ ማህበረሰቦች መሃል የሚከሰቱት ተፃራሪ ፍላጐቶች ብሄራዊ ጥቅምንና ህልውና ከግምት ውስጥ ያስገቡ ስምምነቶችን የሚፈጥሩ መሆን ይኖርባቸዋል።

የሲቪክ ማህበረሰቦች ወገናዊ ጥቅማቸውንና የተመሰረቱበትን አላማ ለማሙዋላት የሚችሉት የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅምና ህልውና ሲረጋገጥ መሆኑን የሚረዱ ይመስለኛል። እንደዚሁ፣ የፖለቲካ ድርጅቶችም የፖለቲካ ስልጣኑን ለመያዝ ይሁን የኢትዮጵያን ብሄራዊ ጥቅም ሊያስከብር ይችላል የሚሉትን የፖለቲካ ፕሮግራማቸውን ለመተግበር የኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና መረጋገጥ እንዳለበት አይረዱም ብዩ አልገምትም። ይህ ስምምነት ከሁሉም ድርጅታዊና ወገናዊ ጥቅም በላይ የሆነ አንድ ብሄራዊ አጀንዳ የሚፈጥር ይመስለኛል። የሲቪክ ማህረሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች ከመጠላለፍ ይልቅ በዚህ ብሄራዊ አጀንዳ ላይ ሊገናኙና ሊተባበሩ ይችላሉ ብዬ አምናለሁ። ታዲያ፣ ይህ ምንም ረቂቃዊነት የሌለው ሀሳብ ለምን በተግባር አልታየም? የሲቪክ ማህበረሰቦችስ ምን አልተበራከቱም? ገብርዬ የጠቀሳቸው ምክንያቶች እንዳሉ ሆነው፣ አንዳንድ መሰረታዊና ውስጣዊ ናቸው ብዬ የምገምታቸውን የግንዛቤ ችግሮች ልጠቁም።

አንደኛ፣ የአገራችን ሁኔታ ይቆረቁረናል የሚሉ ኢትዮጵያዊያን የሲቪክ ማህበረሰቦች

ሊያስገኙ የሚችሉአቸውን ጥቅሞች ጠንቅቀው አውቀው በቁርጠኝነት ሊታገሉላቸው ዝግጁ የሆኑ አይመስለኝም። የፖለቲካ ድርጅቶች ራሳቸው በሲቪክ ማህበረሰቦች ላይ የፈጠሩአቸው ጫናና እንቅፋት የዚሁ ነፀብራቅ ይመስለኛል። በመጀርይ ደረጃ፣ የሲቪክ ማህበረሰቦች በይዘታቸውም ሆነ በአሰራራቸው ዴሞክራሲያዊ ናቸው። የሚመሰረቱትና የሚያድጉት በአባላቶቻቸው ነፃ ፈቃደኝነት ላይ በመመርኮዝ ስለሆነ የተለየ አሰራር ሊከተሉ አይችሉም። የእነኝህ ማህበረሰቦች መበራከትና ማደግ አንድ ህብረተሰብ ምን ያህል የዜጎቹን ሰብአዊ መብትና ጥቅም እንደሚያከብር የሚያመለክቱ መለኪያዎች ናቸው። ስለዚህ፣ የሲቪክ ማህበረሰቦችን መበራከትና ማደግ የምንመለከተው ዛሬ ለሚደረገው የብሄራዊ ህልውና ትግል ከሚያደርጉት አስተዋፅኦ አንፃር ብቻ ሳይሆን ወደፊትም ሊኖረን ከሚገባው የተረጋጋና ዴሞክራሲያዊ ስርአተ–መንግስት ቁምር መሆን ይኖርበታል።

ሁለተኛ፣ ዛሬ በኢትዮጵያ ውስጥ መደረግ የሚኖርበት ትግል ካሁን ቀደም በልምድ ከምናውቃቸው የትግል ስልቶች ለየት ያለ ሊሆን እንደሚችል ቢያንስ አንጠረጥርም። የብሄራዊ ህልውና ትግሉ የሚያነጣጥርበት ኢላማ ጥላው በአንድ ጊዜ በብዙ ቦታዎች ይታያል። ትግሉም እንደዚሁ በአንድ ጊዜ በብዙ ቦታ አለሁ ለማለት መቻል ያለበት ይመስለኛል። ለዚህ ደግሞ ለኢትዮጵያዊነታቸው የሚታገሉትን ኢትዮጵያውያንን በሰፊው ለማሰባሰብ መቻል ይኖርበታል። ለዚህ ደግሞ ለኢትዮጵያዊነታቸው የሚታገሉትን ኢትዮጵያዊያንን በሰፊው ለማሰባሰብ መቻል ይኖርበታል። የፖለቲካ ድርጅቶች ለኢትዮጵያ ብሄራዊ ህልውና የሚያደርጉዋቸው ትግሎች ሁለንተናዊ አገራዊ ድጋፍ ሊያገኙ ይገባቸዋል። ይህንን ሁሉ ለማድረግ ኢትዮጵያውያንን በሚፈቅዱትና በሚመስላቸው የአደረጃትን የመሰባሰቢያ ዘዴ ማገናኘትና ማቀላለፍ የግድ ይሆናል። ለምሳሌ፣ አንድን ሰራተኛ ወይም አስተማሪ ለአንድ የፖለቲካ ድርጅት እንዲታገል ከማድረግ ይልቅ ለሙያ ማህበሩ እንዲቆም ማድረጉ የሚቀል ይመስለኛል። አስራ ሰባቱ የደርግ ፋሽስታዊ አገዛዝ አመታት ትተውልን ያለፉት ተጠራጣሪነት በነገሰበትና ያለፉት ዘግናኝ የፖለቲካ ትዕይንቶች የፈጠሩት ቁጥብነት ብሄራዊ ፀባይ በሆነበት ሁኔታ የፖለቲካ ድርጅቶች በሰፊው የመመልመልና የማደግ እድላቸው የተወሰነ ይሆናል። ይህ ገዋ ሊሞላ የሚችለው ዜጎች በሚያምኑአቸው የስብስብ አይነቶች ለመደራጀት ሲችሉ ብቻ ነው። ከእነዚህ የስብስብ አይነቶች ውስጥ ዋነኛውና አይነተኛው የሲቪክ ማህበረሰብ ድርጅት ነው። ሰዎች በነፃ ውሳኔአቸው እንደተቀላቀሉት ሁሉ፣ ምንጊዜም ስብስቡ ሰዎቹ የተቀላቀሉበትን አላማ ሲስት ወይም የአባላቱን መብት ሲፃረር በነፃ ውሳኔአቸው ጥለውት ሊወጡ እንደሚችሉ ያውቃሉ። ስለዚህ፣ የሲቪክ ማህበረሰብ የአደረጃጀት ዘዴ ወቅቱ የሚጠይቀውና ብዙ ጥቅም የሚሰጥ ይመስለኛል።

ሶስተኛ፣ የሲቪክ ማህበረሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች እንደ ፍፁም ተፃራሪና አንዱ አንዱን ሰራዥ ሆነው መታየት እንደሌለባቸው ብዙውን ጊዜ አንረዳም። እንዲያውም፣ አሁን አገሪቱ ባለችበት ልዩ የቀውጢ ሁኔታ፣ ሲቪክ ማህበረሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶች በጣም ተደጋጋፊና የብሄራዊ ህልውና መታገያ መሳሪያዎች መሆናቸው አፅንኦት ሊደረግበት የሚገባ ጉዳይ ነው። ሲቪክ ማህበረሰቦቹ የተደራጀ ሰሚና ደጋፊ ለፖለቲካ ድርጅቶቹ የሚያቀርቡ ህዝባዊ መግለጫዎች ናቸው። ይህንን ህዝባዊ መግለጫ ርቱአዊ በሆነ መንገድ ለመጠቀም መቻል ደግሞ የፖለቲካ ድርጅቶቹ ፈንታ ነው። የፖለቲካ ድርጅቶቹ ይህንን ህዝባዊ መግለጫ በይገባኛልነት የሚጠይቁት ሳይሆን በመልካም ስነ–ምግባራቸውና አጠቃላይ መስመራቸው የሚጎናፀፉት ፀጋ መሆኑን መረዳት ይኖርባቸዋል።

እነኝህ የጠቀስኩቸው ነጥቦች በውል ቢታወቁ ሁኔታዎችና አካባቢዎች የሚፈቅዱአቸውን የሲቪክ ማህበረሰቦችን ለመመስረትና የተመሰረቱትን ኮትኩቶ ለማሳደግ መንገዱ የተቃና ይሆናል የሚል ግምት አለኝ። ዜጐች ለሲቪክ ማህበረሰቦች የሚሰጡት ክብርና ድጋፍ መሰረታዊ ከሆነ፣ ዛሬ ኢትዮጵያ ውስጥ በግልፅ እንደምናየው፣ እያንዳንዱ ሲቪክ ማህበረሰብ እየተነጠለ የወያኔ የጥቃት ኢላማና መዘባበቻ አይሆንም። እንዲሁም፣ የተመሰረቱትና ወደፊት በትግሉ ሂደት ውስጥ የሚመሰረቱት የሲቪክ ማህበረሰቦች አንድነታቸውንና ህብረታቸውን ለማጠንከር ከበቂ ቀጣይነታቸውና እድገታቸው መሰረትና ዋስትና ይኖራቸዋል። የሲቪክ ማህበረሰቦችና የፖለቲካ ድርጅቶችም ሁኔታው በሚፈቅደው መሰረት ቢተባበሩና ቢቀናጁ የወያኔ ጥቃት አንዱ ላይ እንዳያመዝንና እንዳይጎዳ አንዱ ለአንዱ መተንፈሻ ሁኔታን ሊፈጥር ይችላል።

እንግዲህ ወንድሜ ገብርዬ፣ ባንተ ትክሻ ተንጠላጥዬ፣ የሲቪክ ማህበረሰቦችን አስመልክቶ ቢነሱና ቢታሰብባቸው ይበጃሉ ብዬ ያሰብኩአቸውን ጥቂት ነጥቦች እንዲያው በጅምላነታቸው ገረፍ ገረፍ አድርጌያለሁ። እንዲሁም ዛሬ ገጥሞን ካለው ብሄራዊ አደጋ አንፃር የሲቪክ ማህረሰቦች ምን ሊያደርጉልን እንደሚችሉ አንተ ከጠቀስካቸው በተጨማሪ ለማመላከት ሞክሬያለሁ። እስቲ እያቸውና እንደተለመደው አስተያየቶችህን ፈንጥቅባቸው።

ጌታቸው በጋሻው በሚሺጋን ስቴት ላንሲንግ ነዋሪ ናቸው።

# አዲሱ «ነፍሰ–በላው» (Draconian) የፍልሰ–ስደት (Immigration) አዋጅ

ቅንብርና ትርጉም፦ ላንዳፍታ ዝግጅት ክፍል

«የደከሙትን ድሆችና ግፉዐን ስጡኝ፣ የነፃነት አየር ይተነፍሱ ዘንድ» ከሚል የእንግዳ ተቀባይ ቃሏ የሚመሳሰለውን የፌደል ውቅራት በሕንፃዊ አካሏ ላይ ያፃፈችው በኤሊስ ደሴት የዴሞክራሲ መብራት ይዛ በግርማ ሞገስ የቆመችው ሐውልት እንኳ ቤተሰብ ሲበታተን፣ የመብት ፈላጊዎች ተስፋ ሲጨልምና ሕዝብ በግፍና በጉልበት ታንቆ ሲመለስ ግውዝነቷን ረስታ እርሷም ሳታለቅስ አትቀርም።

በእርግጥም ጊዜውን እየጠበቀ የሚያገረሽ ፀረ–ፍልሳውያን ስሜት በየወቅቱ በአሜሪካ ቢታይም የአሁኑ አዋጅ ነፍስ በላ የሆነና ብዙ የሕዝብ ወገኖችን እንደሚጐዳ ጠበቆችና ተከራካሪዎች ይናገራሉ። በእርግጥ ኢትዮጵያውያን በተደራጀ መልክ የሀገሪቷን ሕግ ተጠቅመው ጠንካራ ተቃውሞ ባያደርጉም በርካታ ወረቀት (ፈቃድ) የሌላቸው ወገኖቻችን በተናጠል ጥረታቸው እንዲሳካ በየፍርድ ቤቱና በየጠበቃ ጽሕፈት ቤቶች እየባዘኑ ነው። በደርግም ጊዜ ይሁን አሁን የመጡ ወገኖቻችንን እጅግ አስቸጋሪ ቢሆንም የፖለቲካ ጥገኝነት እንዲያገኙ ሁሉም ጥረት ማድረግ አለበት። የእነርሱ ድል የእኛ ድል ነው፤ የእነርሱ ትግል የእኛ ትግል ነው። የእነርሱ ቁስልና ስቃይ የእኛ ሕማማት ነው። በዚህ በኩል የቬትናማውያንና የሒስፓኒኮች ተጋድሎና ተቃውሞ ለብዙዎቻችን በጭለማ ውስጥ እንደሚያበራ ጧፍ ብርሃንን የሚለግሰን ስለሆነ ተስፋ የሚሰጥና የሚያበረታታ ነው።

የወያኔ ደጋፊዎችና የነሒርማን ኮኸን ተከታዮች ስቴት ዲፓርትሜንትን በመቀስቀስ «ከእንግዲህ ኢትዮጵያ ውስጥ ዴሞክራሲ ሰፍኗል፤ ኢትዮጵያውያን ስደተኞች መምጣት አይገባቸውም» በማለት ለጥገኝነት በሩን ዘግተዋል። እዚህ በሚያደርጉት ትግልና ተቃውሞ ዛሬ ኢትዮጵያ ቢመለሱ ችግር የሚገጥማቸው ወገኖቻችን ቁጥራቸው ቀላል አይደለም። በአሜሪካ የተደራጀው የወያኔ ስለላ ኃይል ቁጥሩ አነስተኛ ቢሆንም ትልቁ ሥራው ስለተቃዋሚ ግለሰቦች ለሀገር ቤት መዋቅሩ ሪፖርት ማስተላለፍ ነው። እነአበራ የማነአብ የታሰሩት ገና ቦሌ አውሮፕላን ጣቢያ እንደገቡ ነው። ለዴሞክራሲ የቆሙ በርካታ ወገኖቻችን ይህ ዕድል እንዳይገጥማቸው አጥብቀን መታገል አለብን። እንዴት?

1ኛ) ለኮንግሬስና ለሴኔት አባላት የተቃውሞ ደብዳቤ መፃፍ።

2ኛ) በአሁኑ መንግሥት የሚደረገውን የሰው ልጆች መብት ረገጣ ማጋለጥ፣ መረጃ መሰብሰብ

3ኛ) ፈቃድ የሌላቸውን ኢትዮጵያውያንን ለሕግ ወጪ የሚረዳ ማዕከል በአስቸኳይ መመሥረት፤ ገንዘብ ማዋጣት።

4ኛ) እኔ ምን ቸገረኝ የሚሉትን (የዜግነት መብትና የመኖሪያ ፈቃድ ያገኙትን) ገለልተኞች ማስተማር

5ኛ) ከአሜሪካ ኢሚግሬሽን ሎየርስ አሶሴሽንና ከሌሎች የፍልሳውያን ማኅበራት ጋር ትግሉን ማቀናጀት

6ኛ) ፍቅርንና መተባበርን ማንገስ። በታኞችንና የወያኔ ሠርጐ ገቦችን ማግለል።

በኢትዮጵያዊነታችን በሀገራችን የሚደርስብንን የመብት ጭቆና ማጋለጥ።

7ኛ) ይኸ ሕጋዊ ሀገር በመሆኑ ስቴት ዲፓርትሜንት ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ላለማስመጣት የወሰነውን ውሳኔ በደብዳቤ፣ በሕግና በማስተማር ለመቀልበስ መጣር።

8ኛ) በተቻለ መጠን በሕግና በፍቅር ላይ የተመሠረተ ጋብቻ እንዲኖር ማድረግ። ወቅቱን ተጠቅሞ ለግሪንካርድ የሚደረግ ጋብቻ ሕጋዊ ስላልሆነና ከተነቃም ከፍተኛ ጉዳትን ስለሚያስከትል መወገዝ አለበት። ክብርንና እውነትን የተመረኮዘ፤ ጋብቻችሁ ለፍቅርና ቤተሰብም ለመመስረት ይሁን። የውሸት ጋብቻ ወንጀል ነው። ራስን ከማታለል አልፎ መቀመቅና ከርቸሌ ያስገባል።

ከዚህ በታች የኢትዮጵያውያን ወዳጅ የሆኑ ጠበቃ የፃፉትን በአማርኛ ተርጉመን አቅርበነዋል። እኚህ ምሑር የኢትዮጵያውያን ወዳጅና ወንድም በመሆናቸው ስላቀረቡት ጽሑፍ ምሥጋናችን ከፍተኛ ነው። እድሜና ክብር ይስጥልን እንላለን፣ በኢትዮጵያዊ አክብሮታችን!!

«ባለፈው ስድስት ወር የአሜሪካንን የፍልሰ–ስደት አዋጅ በሚመለከት የሕጉን አጠቃላይ ለውጥና የይዘቱን ዐቢይ ሕብረተሰባዊ ተፅዕኖ ተመልክተናል፣ ታዝበናል። ሕጉ ውስጥ ካሉት አዋጆች በተለይም ሁለቱ ለፍል፡ሰ–ስደቱ ለውጥ ከፍተኛ አስተዋጽኦ ያደርጋሉ። የፀረ–ሽብር ፈጣሪ (ቴረሪዝም) እና ተገቢ የሞት ቅጣት ድንጋጌዎች በ1996 የቀረቡት የመጀመሪያውን ሥፍራ ሲይዙ በሁለተኛ ደረጃ ደግሞ የሕገወጥ ፍልሰ–ስደትና የስደት የ1996 ድንጋጌዎች በመለስተኛና በተጣማሪነት ይገለፃሉ። እነዚህ ለውጦች በጥላቻና በአድልዎ ላይ የተመሠረቱ ከፉና ፍትሕ የጐደላቸው ናቸው። ውሱንና ጠባብም ናቸው። አብዛኛዎቹ ድንጋጌዎች ወዲያውኑ ሲፀኑ ሌሎቹ ደግሞ ከአፕሪል 1, 1997 ጀምረው ፀድቀዋል። እነዚህም ሕጐችና ድንጋጌዎች በኢትዮጵያውያን ግለሰቦችና ቤተሰቦች ከፍተኛ አስከፊ ተፅዕኖ እንደሚያደርጉ ጥርጥር

የለውም። በሌሎችም ላይ እንደዚሁ ጉዳት ያደርሳሉ። የዚህም ጽሑፍ አላማ ይህንን ችግር የሚያብራራ ይሆናል።

## ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት
## (Legal Permanent Residency)

ኮንግሬሱ በደነገገው መሠረት ከ180 ቀናት በላይ በአሜሪካ ካለ ፈቃድ የሚኖሩ ግለሰቦች ከአፕሪል 1፣ 1997 ጀምሮ ከአሜሪካ ውጭ ለ3 ዓመት ያህል ካልኖሩ በስተቀር ሕጋዊ ቋሚ ነዋሪነት አይሰጣቸውም። ይህም ማለት በመጀመሪያ ከአሜሪካ ወጥተው 3 ዓመት መቆየት አለባቸው። በሌላ አነጋገር ከአፕሪል 1፣ 1997 ጀምሮ ማንኛውም ግለሰብ ከመስከረም 27፣ 1997 ጀምሮ ካለፈቃድ በአሜሪካ የሚኖር ግለሰብ ለ3 ዓመት ሕጋዊ ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ እንዳያገኝ ይገደባል። በተጨማሪም ከአንድ ዓመት በላይ ካለፈቃድ የሚኖሩ ግለሰቦች አሜሪካ ለመግባት በ10 ዓመት ይታገዳሉ።

የቃሉ አገባብ ሌላ ትርጉም ካልተሰጠው በስተቀር «ካለ ፈቃድ ወይም ካለ ሕጋዊ ፈቃድ» የሚኖር ማለት ከተሰጠው የቪዛ ጊዜ በማለፍ የቆየ ወይም ካለተገቢ ፈቃድ ወደ አሜሪካ የገባ ማለት ነው (ይህ ሁሉንም ዖታ ይመለከታል)። ይህ ሕግ የማይመለከታቸው ከ18 ዓመት በታች ያሉ ሕፃናት ወይም ግለሰቦች እና የፖለቲካ ጥገኝነት ጠይቀው በሕጉ መሠረት መልስ እስከሚሰጣቸው በመጠባበቅ ላይ ያሉ ናቸው።

ይህም በገቢራዊ ሁኔታ ሲተነተን የግሪን ካርድ ማመልከቻ አቅርበው በመጠባበቅ ላይ ያሉ አመልካቾች የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ ያልጠየቁና በመጠባበቅ ላይ ያልሆኑ፣ (ወይም ያቀረቡት የጥገኝነት ጥያቄ ሕጋዊ የመኖሪያ ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት የስድስት ወር የጊዜ ገደብ ከተሰጠውና ይህም ካለቀ)፣ አሜሪካንን ከሴፕቴምበር፣ 1997 በፊት ለቀው መውጣት ይኖርባቸዋል። የግለሰቦች ዝርዝር «ካለሕጋዊ ፈቃድ» ውስጥ ከገባና በ180 ቀን ውስጥ አሜሪካንን ከለቀቁ ግለሰቦቹ የቋሚ ነዋሪነት ፈቃድ ከማግኘታቸው በፊት ከአሜሪካ ውጭ ለ3 ዓመት መኖር አለባቸው። በተጨማሪም ለአንድ አመት ካለፈቃድ መኖር የ10 ዓመት የገደብ ቅጣትን ያስከትላል።

## የፖለቲካ ጥገኝነት አግባቦችና ቅደም ተከተሎች

በውሸት ሰነድ ወይም ካለተገቢ ሰነድ አሜሪካ መግባት በፖለቲካ ጥገኝነት ፈላጊዎች ዘንድ የተለመደ ቢመስልም የዚህ ዓይነቱ አድራጐት ከመግቢያው በር ላይ ከፍተኛ ችግርን ሊፈጥር ይችላል። የአሜሪካ ፍልሰ ስደትና ነዋሪነት ተቋም (አይ ኤን ኤስ (INS)) እነዚህን ግለሰቦች ካለፍርድና ዳኛ ፊት ሳይቀርቡና ይግባኝ ሳይጠይቁ አስሮ ሊመልሳቸው ወይም በቁጥጥር ስር እንደሚያደርጋቸው ሙሉ ስልጣንና ኃላፊነት (authority) በኮንግሬስ ተሰጥቶታል። የወንጀልና የፍትሐብሔር ቅጣት አውቀው የውሸት ሰነድ አሜሪካ ለመግባት በሚያቀርቡት ላይ እንደሚበየን ተደንግጓል። የውሸት ሰነድ በማቅረብ የተከሰሰ ግለሰብና ጥፋቱም የተረጋገጠበት (የተመሰከረበት) ለማንኛውም ጊዜ አሜሪካ እንዳይገባ ይከለከላል/ትከለከላለች። የፖለቲካ ጥገኝነት ጠያቂ ግለሰቦች ከዚህ ቅጣት ለመዳን ማመልከቻቸውን ማቸነፍ አለባቸው። የፖለቲካ ጥገኝነት ፈላጊ ግለሰብ አሜሪካ ለመግባት ማመልከቻ ወዲያውኑ ሲገባ ለማቅረብ አይችልም። በአዲሱ ሕግ መሠረት በመጀመሪያ ጥገኝነት ፈላጊው ግለሰብ «ወደሀገሩ ቢመለስ ሊገጥመው የሚችለውን አይቀሬና እውነተኛ ፍራቻ» በአሳማኝ ሁኔታ ማለትም በዘር/በጐሳ፣ በብሔር፣ በፖለቲካ አባልነት፣ በሕብረሰተባዊ ክፍል አባልነትና በፖለቲካና በኃይማኖት እምነቱ የመሰደድና የመብት መረገጥ እንደሚገጥመው ማሳየት መቻል አለበት። ይህንን ተገቢ ፍርሐት በአሳማኝ ሁኔታ ካቀረበ በኋላ ወደ ጥገኝነት መኮንኑ «ለእውነተኛ ፍራቻ» ወይም «ለአሳማኝ ፍራቻ» ቃለ መጠይቅ ይቀርባል። ግለሰቡ ሁኔታውን «በአሳማኝ ሁኔታ» ለመብቱ መረገጥ ስጋት ካላቀረበ ወዲያውኑ ጥያቄው ውድቅ በመሆን ሊመለስ ወይም በቁጥጥር ስር ለመመለስ ይውላል። ሆኖም አሳማኝ ነጥብ ካቀረበ ለተጨማሪ ምርመራ ወይም ፈተና ወደ ማረፊያ ቤት ይወሰዳል። በዚህም መሠረት ለዳኛው መረጃውንና ማመልከቻውን እንዲያቀርብ እድል ይሰጠዋል።

ኮንግሬስ የፖለቲካ ጥገኝነት ማመልከቻ በ6 ወራት ውስጥ ውሳኔ እንዲያገኝ ለአይ ኤን ኤስ (INS) ትዕዛዝ አስተላልፏል። ሌሎች ሁኔታውን የሚለውጡ ድንገተኛ ነገሮች እስከሌሉ ድረስ ማመልከቻው በገባ በ45 ቀናት ውስጥ የጥገኝነቱ ቃለ መጠይቅ መጀመር አለበት። ማመልከቻው ተቀባይነት ካላገኘ ሁኔታው ወደ ዳኛ ይተላለፋል፤ ዳኛውም በ180 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት።

ሌላው ለውጥ ከአፕሪል 1፣ 1997 ጀምሮ የሚፀናው የሥራ ፈቃድ ነው። በዚህ ድንጋጌ መሠረት በፖለቲካ ጥገኝነት ላይ የተመሠረተ የሥራ ፈቃድ የተረጋገጠ አይደለም። አይ ኤን ኤስ ካመነበት ለፖለቲካ ጥገኝነት አመልካቾች የሥራ ፈቃድ ሊሰጥም ላይሰጥም ይችላል። ስልጣኑ የኢሚግሬሽን ባለስልጣን ነው። በተጨማሪም በተያያዙትና በተጣመሩት ድንጋጌዎች መሠረት ለፖለቲካ ጥገኝነት ማመልከቻ የሚከፈል ገንዘብ ሊኖር እንደሚችል ከአዋጁ መረዳት ይቻላል።

በርካታ አዲስ ድንጋጌዎች የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄዎች ተቀባይነት እንዳይኖራቸው የተወሳሰቡ እንቀፆች ያብራራሉ። ከእነዚሁም ውስጥ ዐቢይ መሰናክል ሊፈጥር የሚችለው የአንድ ዓመት ጣሪያ ወይም ገደብ ነው። የፖለቲካ ጥገኝነት

ጠያቂዎች ማመልከቻቸውን አሜሪካ በገቡ በአንድ ዓመት ውስጥ ማቅረብ አለባቸው። በአንድ አመት ውስጥ ካላመለከቱ ማመልከቻቸው ምንጊዜም ቢሆን ተቀባይነት አይኖረውም። ይህም ሕግ የሚፀናው በአፕሪል 1፣ 1997 ቢሆንም አይ ኤን ኤስ(INS) እስከ አፕሪል 1፣ 1998 ይህ ድንጋጌ እንዳይፀና አድርጕታል።

በእርግጥም በዚህ ሕግ (አዋጅ) መሠረት ለፖለቲካ ጥገኝነት አሳማኝ ነጥብ ማቅረብ (ይህም አመልካቹ በገባ በአንድ አመት ውስጥ መሆን እንዳለበት መረዳት ያስፈልጋል)፣ የአመልካቹ ጥረትና ኃላፊነት ነው። በሌላ አነጋገር አመልካቹ ወደ አሜሪካ የገባበትን ትክክለኛ ቀን ማስረዳት፣ እንደዚሁም ማመልከቻው ግለሰቡ በገባ በ365 ቀናት ውስጥ እንዳቀረበ ማረጋገጥ አለበት። ይህን አለማድረግ ማመልከቻውን ውድቅ ያደርገዋል። አንድ ግልፅ መሆን ያለበት ነገር አለ። አመልካቹ በተማሪ ወይም በH-1B VISA ቢመጣም ይህም የ365 ቀናት የጊዜ ገደብ ከሕጉ ወይም ከአዋጁ ነፃ አያደርገውም።

ከላይ የተጠቀሰው የአንድ ዓመት ገደብ ሊነሳ የሚችለው አሳማኝ ከቁጥጥር በላይ የሆነ (Extraordinary Circumstance) ሁኔታ ካለ ነው። በአይ ኤን ኤስ(INS) አባባል እነዚህ ሁኔታዎች በእርግጥም ከአመልካቹ ቁጥጥር በላይ በመሆን ተፅዕኖ ሲያደርጉ ነው ተቀባይነት ሊኖራቸው የሚችለው። ለምሳሌ ድንገተኛ አደጋ፣ ከባድ በሽታ፣ አእምሮአዊና አካላዊ ጉዳት፣ ሕጋዊ የአካል ጉዳት (ሕመም)፣ በቂ የክርክር እርዳታ (ጠበቃ) ካልኖረ... እዚህ ውስጥ ሊጠቀሱ ይችላሉ።

በተጠቀሰው ጊዜ ማመልከቻ ማቅረብ ብቻም አይደለም ጥያቄውን ውድቅ የሚያደርጉት። ሦስተኛ ተቀባይና ረጂ ሀገርም አመልካቹ ሊሄድ ከቻለ ማመልከቻው ተቀባይት አይኖረውም። እንደነዚህ ዓይነት ሀገሮች አመልካቹ ከመጣበት የራሱ ሀገር የተለዩና አሜሪካም መልካም የወዳጅነት ግኑኝነት ያፈራባቸው መንግሥታት ናቸው። እነዚህ መንግሥታት የአመልካቹን በነፃነት መኖር ካረጋገጡና ማመልከቻውን መስማት ከቻሉ አመልካቹ ይህንን መንገድ የማሳካት ኃላፊነት አለበት። ይህ ሕግ ግን አሁን በዝርዝር ስላልቀረበ ወደፊት በተገቢው መልክ እንደሚደነገግ ይታመናል።

የፖለቲካ ጥገኝነት ጥያቄ ከዚህ በፊት ተቀባይነትን ካላገኘ አመልካች አዲስ ማመልከቻ ቢያስገባ ተቀባይነት አይኖረውም። ሆኖም አዲስ መብትን የሚፈን ሁኔታዎች በግለሰቡ እናት ሀገር ከተከሰቱና ሁኔታውም ለአመልካቹ አስጊ ከሆነ ማመልከቻው እንደገና ሊታይ ይችላል።

በአዋጁ መሠረት ማመልከቻዎች በሚከተሉት ሁኔታዎች ተቀባይነት አይኖራቸውም።

1ኛ) የሌሎችን ግለሰቦች መብት ለመርገጥ አመልካቹ ከዚህ በፊት ቅስቀሳ ካደረገ፣ ሌሎችን ካሰቃየ ወይም ከጐዳ፣ ጠብ ጫሮ የሌሎች የሕዝብ ክፍሎችን መብት ከረገጠ ወይም ግለሰቦችን ካሳደደ። በኢትዮጵያውያን አንፃር ሲታይ ይህ ሕግ ከዚህ በፊት ካለፈው መንግሥት ጋር የተያያዙትንና የተሳተፉትን አመልካቾች ሊጐዳ ይችላል።

2ኛ) በአሜሪካ አመልካቹ በወንጀል «በራሱ ጥፋት» የተነሳ ፍርድ ከተፈረደበት

3ኛ) አመልካቹ አሜሪካ ከመግባቱ በፊት ከባድ ፖለቲካዊ ያልሆነ ወንጀል ከፈፀመ

4ኛ) አመልካቹ ለአሜሪካ የሕዝብ ደህንነት አደገኛ ከሆነና በሽብር ፈጣሪነት ድርጊቶች ከተሳተፈ

5ኛ) በተገቢ መንገድ በሌላ ሀገር በቋሚ ነዋሪነት የተደላደለ ግለሰብ ለአሜሪካ ነዋሪነት ጥያቄው ተቀባይት አይኖረውም።

ግልፅ መሆን ያለበት ከዚህ በፊት መብታቸው ስለተረገጠና በእምነታቸው ስለተሰደዱ ግለሰቦች ሕጉ ለውጥ አላደረገም። አብዛኞዎቹ ኢትዮጵያውያን ከዚህ በፊት በነበረው መንግሥት(ደርግ) ኑሮአቸውና መብታቸው ተጐሳቁሏል። አመልካቹ ለአይኤንኤስ ከዚህ በፊት የደረሰበትን ጉዳት በአሳማኝ ሁኔታ ከገለፀ ለጠያቂው ሁኔታው አሁንም በተያያዘ መልክ አስጊ ነው ማለት ነው። ሆኖም አይኤንኤስ የአሁኑን ሁኔታ በተሻሻለ መልክ ለዳኛው ካሳየና የሀገሪቷም ሁኔታ ተለውጧል በማት አሳማኝ ክርክር ካቀረበ ማመልከቻው ውድቅ ይሆናል።

እጅግ የሚያስገርመው ግን የአሁኑ አዋጅ ለይግባኝና ማመልከቻው ውድቅ ከሆነ በኋላ ለፌዴራል ፍትሐዊ አቤቱታ በር አይከፍትም። ይህም ማለት የፌደራል ፍርድ ቤቶች የኢምግሬሽን ዳኛ የወሰነውን በይግባኝ መልክ አያዩም፤ ልዩ ሁኔታዎች እስካላስገደዱ ድረስ!

## መመለስን ስለማገድ ወይም ማስወጣትን ስለማቆም

በድሮው ሕግ ግለሰቡ ለ7 ዓመታት ያህል በተከታታይ ሳያቋርጥ አሜሪካ ከኖረ (ካለፈቃድም ቢሆን) ከአሜሪካ አይባረርም። ይህም የሚሆነው ግለሰቡ ሀገር ቤት ቢመለስ (እዚህ ከኑሮ ጋር ስለተለማመደ) የሚገጥመውን ችግር ለማስረዳት ከቻለና በወንጀል ካልተሳተፈ ነው። የአሁኑ ሕግ ግን ይህንን ለውጦታል። ከአፕሪል 1፣ 1997 ጀምሮ ግለሰቡ በአሜሪካ 10 ዓመታት ሳያቋርጥ መኖር አለበት። ሆኖም 10 ዓመቱ ዋጋ የማይኖረው ኢምግሬሽን በሆነ ምክንያት ከተጠራና ወንጀል ከፈፀመ ነው። ለምሳሌ ግለሰቡ በጁን 1፣ 1987 መጣ እንበል። ከሀገር ለመውጣት በዳኛው ለጁላይ 1፣ 1997 ይጠራ። አሜሪካንን በአስር አመቱ ጊዜ ውስጥ ካለቀቀ አሜሪካ ይቆያል። ሆኖም ለምሳሌ ዳኛው በሜይ 1፣ 1997 ቢቀጥረው በአንድ ወር ልዩነት ከሀገር ይወጣል ማለት ነው።

ሌላው ደግሞ ግለሰቡ ከዚህ ሀገር ቢወጣ

የሚያጋጥመው ችግር እርሱን ብቻ ሳይሆን ሌሎችንም የአሜሪካ ዜጐችና ቋሚ የነዋሪነት ፈቃድ ያላቸውንም፣ ሕፃናትንና ባለቤትን መጉዳት አለበት። ይህንንም ቁልጭ ባለ ሁኔታ ማሳየት ይኖርበታል።

## ወንጀል ስለፈፀሙ አመልካቾች አዋጁ ምን ያህል ያትታል?

አዋጁ ካለምንም ክርክር (ጠበቃ) ወንጀል የፈፀሙ አመልካቾች ከአሜሪካ እንዲወጡ ይወስናል። ስለሆነም የግለሰቦች ጠበቃዎች በወንጀል ከዚህ በፊት የተፈረደባቸውን አመልካቾች ሁኔታ ከአዲሱ ሕግ ጋር በማገናዘብ በውል መመርመርና ማጥናት ይኖርባቸዋል። ይህም ከሀገር መውጣቱን ለመመከት ሊረዳ ይችላል። በክስ የተፈረደበት አመልካች ሁሉ በሕጉ መሠረት ከአሜሪካ ሊባረር ይችላል። አይኤንኤስ ማንኛውንም የተፈረደበትን ግለሰብ የቅጣት ሁኔታ አይለይም። በዚህ አዋጅ መሠረት ወንጀል ወንጀል ነው።

አንዳንድ ወንጀሎች ባለግሪን ካርዶችንም ጭምር ከአሜሪካ ያስወጣሉ። እነዚህም የግብረገብና የመልካም ባህሪን ሕግ መጣስ፤ በተለይም ግለሰቡ በገባ በአምስት ዓመት ውስጥ እነዚህ ከተፈፀሙ ከሀገር ሊያስወጡ ይችላሉ። ባለቤት (ሚስት)ና ልጅ ላይ ጉዳት ማድረስ ይህም በፍርድ ቤት ከተረጋገጠና ግለሰቡ ከተፈረደበት ከሀገር ያስወጣል። ሌሎች በአመልካቹ ጥፋት የተነሳ የተፈፀሙ ወንጀሎች ከሀገር ያስወጣሉ። እነዚህም ለ29 ዓመት ግለሰቡ አሜሪካ እንደገና እንዳይገባ ያግዳሉ። ግለሰቡ በግሪን ካርድ ለብዙ ዓመታት ቢኖርም፣ እንደዚሁም በርካታ ቤተሰቦች በአሜሪካ ቢኖሩትም እነዚህ ከአሜሪካ ከመውጣት አያስቀሩትም። ግድያ፣ በአመልካቹ ጥፋት የተቀሰቀሰ ከሆነ ከአሜሪካ መውጣቱ የግድ ይሆናል። ሴት መድፈርም ትልቁ ወንጀል ነው፣ ከሀገር ያስወጣል። ሌላው የሚያስገርመው አመልካቹ ገበያ ሄዶ እቃ ሳይከፍል ቢሰርቅ (Shop lifting) ዳኛውም የአንድ አመት የማስጠንቀቂያ ፍርድ (Probation) ቢሰጠው ይህ በአይኤንኤስ (INS) ዓይን ወንጀል ስለሆነ ግለሰቡ ግሪን ካርድ ቢኖረውም ከሀገር ይወጣል።

ሌላው ደግሞ ከዚህ በፊትም የተሠራ ወንጀል ይቆጠራል። ለምሳሌ አንድ ግሪን ካርድ ያለው ግለሰብ አለ እንበል። በ1967 ግሪን ካርድ አገኘ። በዚያን ጊዜ 18 ዓመቱ ነበር። እርሱም በ1967 ወንጀል ፈጸመ፣ በ1997 ዓ.ም. በ48 ዓመቱ በዚህ ሕግ መሠረት ከሀገር ይወጣል ማለት ነው። ለዜግነት ማመልከቻ ሲያቀርቡ በዚህ ዓመት በታጠቁ የኢሚግሬሽን ፖሊሶች ከሀገር እንዲወጡ የተገደዱ ግለሰቦች በርካታ ናቸው። ስለሆነም ከዚህ በፊት ወንጀል ሠርታችሁ ከሆነ የዜግነት ማመልከቻ ከማቅረባችሁ በፊት ሁኔታውን ከጠበቃ ጋር ሆናችሁ መርምሩት።

## ከኢምግሬሽን ቢሮ በ3/21/97 የወጣ ማስታወቂያ

የአድጀስትመንት ኦፍ እስታተስ ማመልከቻን (Adjustment of Status for unlawfully present aliens) በተመለከተ የተወሰነውን የአፕሪል 1 1997 የመጨረሻ ቀን በኢምግራንት ኮሚኒቲ አካባቢ ያመጣውን ከፍተኛ ችግርና በዚያ ልክ በየ ኢምግሬሽን ቢሮ የሚታየውን ረዣዥም ሰልፍ በመመልከት የኢምግሬሽን ቢሮ የመጨረሻ ቀኑ አፕሪል 1 ሳይሆን ሴፕተምበር 30 1997 መሆኑን በ3/21/97 ባወጣው ማስታወቂያ የገለጠ መሆኑ ታውቋል።

3/21/97

### Deadline for Adjustment of Status Applications

Confusion in the immigrant community has arisen about the perceived need for filing Adjustment of Status (I-485) applications by April 1. This has resulted in unnecessary waits in long lines at INS offices in several cities.

Adjustment of Status (I-485) applications do not need be filed prior to April 1, 1997. Filing I-485 or getting married to try to adjust immigration status prior to April 1 provides no advantage to the applicant under the changes in the immigration law which will become effective April 1, 1997.

The deadline for unlawfully present aliens to adjust their immigration status is September 30, 1997. The Administration has urged Congress to extend the adjustment of status beyond that date. INS is making every effort to clarify these issues and address the problem of long lines at some offices caused by increased number of adjustment os status applications.

In order to avoid waiting in lines, INS has added a second shift to our forms requesttoll free phone lines 800/870-3676. In addition, our toll free ASK IMMIGRATION lines are available for general inquiries and individual immigration questions - 800-375-5283.

**Allstate®**

**You're in good hands.**

4122 East Ponce DeLeon Ave. Suite 4
Clarkston, GA 30021
Phone: (404)508-8978
Fax: (404)299-6266

AUTO
HOME OWNER'S
RENTERS
LIFE
BUSINESS
COMMERCIAL AUTO

*CALL US FOR NEW & USED CARS LOAN*



Theodros Hailegiorgis
*Exclusive Agent*

Allstate Life Insurance Company, Northbrook, Il.
Allstate Indemnity Company, Northbrook, Il.
Allstate Commercial Companies
(subject to limitations and availability)

**You're in good hands.**



**R T S**

# RAPID TAX SERVICE

ፈጣንና ቀልጣፋ
የታክስ
ሥራ አገልግሎት

PROFESSIONAL
TAX PREPARATION
INDIVIDUAL & BUSINESS
ELECTRONIC
TAX FILING

OFFICE HOURS
*Monday - Friday 8:00am to 7pm*
*Saturday 9am to 5 pm*
CALL (RTS) LEAKE MALEDE
PHONE: (404)296-3088
FAX: (404)296-7413
E-Mail: rapidtax@aol.com
*Accepted the past two years by the IRS to participate In the electronic filing Program*

# ASAP COPIES

**BEST PRICE IN TOWN!**
*High-Speed Duplicating*

ጎብኙን!!

Business Cards
Flyers
Typesetting
Resumes
Fax Services

Photo ID
Passport Photos
Laminations
Greeting Cards

Letterheads
Envelopes
Rubber Stamps
Copy Service
Self-Serve Copies

Conveniently located in Campus plaza Shopping Next to Dekalb Book Store

# ከ አ ን ባ ብ ያ ን



እንዴት አላችሁሳ ላንዳፍታዎች?

ይኼ ነው የእውነተኛ ኢትዮጵያውያን ቁምነገር! ጉሽ በኢትዮጵያ ብሔራዊ ቋንቋ (አማርኛ) ይህንን የውይይት መጽሔት ሳይታክታችሁ በውጭ ሀገር ማዘጋጀታችሁ እጅግ የሚያኮራ ነው። ድካሙንና ልፋቱን ስመዝነው ከሽያጩ ምንም የረባ ገንዘብ እንደማታገኙ እረዳለሁ። ሆኖም በመቻቻልና በመደማመጥ የውይይትን መድረክን በመፍጠር የምታደርጉት ጥረት ከፍተኛ እንደሆነ እገነዘባለሁ። እኛም ኃላፊነት እንዳለብን አውቃለሁ። ሰፊ ስርጭት እንዲኖር፣ ላልሰማው ለማሰማትና ሁሉም አስተያትን እንዲለግስ በተቻለኝ መጠን እጥራለሁ።

ከአሜሪካና ከሀገር ውስጥ በፀሐፊዎቻችሁ የሚደረጉት የደብዳቤ ልውውጦች የአመለካከቱን አድማስ በማስፋታቸውና እኔም በኢትዮጵያዊነቴ በዚህ ሀገራችን ላይ በሰፈነው ጭለማ የተቻለኝን ባለማድረጌ በእውነት አፍራለሁ።

ባለፉት እትሞች በይግለጡ፣ በወር-ቃየሁ፣ በገብርዬ፣ በውሒብ ጥሩነህና እያዩ በልልኝ ብዙ ቁምነገሮችች ተነስተዋል። እነርሱን መሠረት በማድረግ አንዳንድ አስተያየቶችን እሰነዝራለሁ።

ካለፉት ሶስትና አራት አመታት በተለ ሁኔታ አሁን ትግላችን ለምን ረገበ? ብዙ ምክንያቶች አሉት።

1ኛ) የጴንጤዎች መዋቅርና ስብሰባ በግላዊ ሰላም ስም የብዙውን ዜጋ ልብ በመለወጡና ወጣቱ ክፍል ለመብቱ፣ ለጥቅሙና ለሀገሩ እንዳይታገል ሐሞቱን ስላፈሰሱበት «ለሞራላዊ ንፅህናና ለፅድቅ» እንታገላን ቢሉም አሰላፍቸው ለጠላት ካምፕ ስትራቴጂና ታክቲክ የሚጠቅም ነው። የወያኔ መንግሥትም በኃይማኖት እኩልነት ስም የጥንቱን የተዋሕዶ እምነት እየመታ ለሚሲዮናውያን የወንጌል ሰበካ ድጋፍ መስጠቱ የክል መስተዳደርና «በቋንቋዎች የየሱስ ቃል መስበክ ፕሮፓጋንዳ ሕዝብን እንዲያወናብድና እንዲያዘናጋ አድርጓል። እያዩ ቢልልኝ ይህንን በማጋለጡ በኢትዮጵያዊነቴ አመሰግነዋለሁ።

2ኛ) ኢትዮጵያን በቱሪስት መልክ ለመጎብኘት በሚደረገው ጥድፊያና ሚስት ለማምጣት በሚደረገው ዘመቻ አንዳንድ ወገን ለዚህና ለመሳሰለው ፍላጐቱ ሲል ቀዝቅዟል። ወደ ኢትዮጵያ ለመሄድ ወር ሲቀራቸው ከፖለቲካ ድርጅቶች፣ ከእ-ብያተ ክርስቲያናት፣ ከኢትዮጵያዊ ማኅበራትና ከታጋይ ግለሰቦች ጋር በመቀያየም ወደ ወያኔ ደጋፊዎችና መሪዎች ፊታቸውን የሚያዞሩና የሚስቁ ሞልተዋል። እንዲያውም የወያኔን ፕሮፓጋንዳ በመርጨት «ሁሉም የኢትዮጵያ መንግሥታትና ድርጅቶች ለምሳሌ ኃይለሥላሴ፣ መንግሥቱ፣ መለስ ዜናዊ፣ ወያኔ፣ ኢሕአፓ፣ ኢዲዩ፣ ኢሰፓ፣ መኢሶን ... ወዘተ ሰይጣኖች ናቸው በማለት ሁሉንም በእኩልነት «ለማሳየት» ፕሮፓጋንዳ ያዛምታሉ። ልብ አድርጉ ሁሉም ሰይጣኖች ናቸው ሲሉ የወያኔ መንግሥት በጥፋቱ ከእነዚህ ልዩ አይደለም በማለት የማራል እኩልነትን ለመስጠትና ቢሆንም ሁሉም ያው ናቸው፤ ከሀገሪቱ ሁኔታ ተለይተው የመጡ አይደሉም ለማለት ነው። የወያኔን መንግሥት ተገቢ ለማድረግ የሚረጭ የተራቀቀ የፕሮፓጋንዳ ስልት ነው። በእኔ አመለካከት ኢትዮጵያን የጉሳ ቅራኔ ውስጥ በማስገባቱና የራሱን ሀገር ዙፋን ላይ ቁጭ ብሎ የብተናንና የመገንጣጠልን ፖሊሲ በመጠቀም እናት አገራችንን በመጉዳቱ ከወያኔ መንግሥት የከፋ አስተዳዳሪ በኢትዮጵያ ታሪክ ከቶ አልታየም እላለሁ።

በተለያየ መልክ የሚመጣባችሁን ነቀፌታ መርምሩ። በማር የተለወሰ ኮሶ ሆኖ ከጠላት ጉራም ሊወረወር ይችላል። ለገንዘብና ለግል ጥቅም ብቻ የሚራወጡ ሆዳሞችን አሁንም አስተምሩ። በበጎ ስራችሁ ቀጥሉበት።

ዘመድኩን ነኝ – ከሚኒሶታ

## ስንቱን አየሁ በሴትነቴ

አሜሪካን የመጣሁት ለጉብኝት በሚል ቪዛ ነበር። እንደሚታወቀው አሜሪካን አገር ለመኖር ፈቃድ ማግኘት ያስፈልጋልና የምችለው የፖለቲካ አሳይለም መጠየቅ ወይንም የአሜሪካ አገር ነዋሪነት ፍቃድ ያለው (ሲቲዝን) የሆነ ማግባት አለብኝ ማለት ነው።

ባል የተባሉትን ለወደፊቱ እመለስበታለሁ። ለጊዜው የፖለቲካ አሳይለም ለመጠየቅ ያዘዝኩት ስለጠበቃዬ ላውጋችሁ። አበሻ ነው ሰዎች ናቸው ያገናኙን። ኬዙ ተጀመረ የሚፈልገውን አንዳንድ ኢንፎርሜሽን ስለቤተሰብ ታሪክ ስለክፍያው ሁሉ ተነጋግረን ተጀመረ።

ጠበቃዬ ትልቅ ሰው ነው፤ እኔ ልጅ ልሆን እችላለሁ። ባለትዳርና የሁለት ልጆች አባት መሆኑን ሰዎች ነግረውኛል። አጅሬውም ከማን እንደምኖር የት ሰፈር እንደምኖር ጠንቅቆ ያውቃል። እልኪም ስላለው ቤተሰቦቼ በሌሉበት ሰዓት ይደውላል። ሻይ ልጋብዝሽ፣ አገር ላሳይሽ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ጥያቄዎች በጠየቀኝ ቁጥር እንደማይመቸኝ ብነግረውም ልሰ ማለኝ።

አንድ ቀን ደውሎ ከሰአት በኋላ የምፈርመው ወረቀት ስላለ እንደሚመጣ ነገረኝ። ልቤ ደስ ባይለውም እውነት የሚፈረም ነገር ካለ ብዬ እሺ አልኩት። አጅሬው ሽር ብሎ መጣ። አለባበሱንና

ቁመናውን በልቤ አድንቄለታለሁ። ይህ ሁሉ ቁመናና አለባበስ ለሚስቱ እንጂ ለእኔ ምን ያደርግልኛል? እንደመጣም ቤት ገባ። እኔም የሚፈረመውን ወረቀት ብጠይቀው የሰጠኝ መልስ «የሚፈረም ወረቀት የለም፤ እኔ የመጣትሕሁ አይንሽን ለማየት ነው ...» በማለት የውሸት የፍቅር ቃላቶቹን መደርደር ጀመረ። እኔም ሁኔታው ስላላማረኝ በሩ አጠገብ ቆሞ ብዬ እሰማው ጀመር። ሁሉ ነገሩ በጣም ገርሞኝ እያየሁት ሳለሁ አጅሬው ተነስቶ ሊይዘኝ ሲል በሩን ከፍቼ አመለጥኩትና እስኪሚሄድልኝ ድረስ ከቤት ውጪ ቆየሁ። በኋላም የስድብ መዓቱን ካወረደብኝ በኋላ ኬዚን እንምይበላሽብኝና እንምዝን እንዲያውም ተስፋሽን ቆርጠሽ አገርሽ ስትገቢ ታስታውሺኛለሽ እያለ እየተፈናጠረ ከቤት ወጥቶ መኪና ውስጥ ገብቶ ሄደ።

እኔም ነገሩን በሚስጢር ይዤ ለአምላኬ ኬዜ እንዲሳካልኝ ጠዋት ማታ መፀለይ ጀመርኩ። ለእግዚያብሔር የሚሳነው ነገር የለምና በ6ወሬ ተቀብለንሻል የሚል የምስራች ደብዳቤ ደረሰኝ። አንባቢ ፍረዱኝ ለአምላኬ ምን ዓይነት ምስጋና ላቀርብለት እንደው በትንሹ ተመስገን ከማለት በስተቀር።

ጠበቃዬም በኋላ ስሰማ ለካስ ዝህ ነገር የታወቀ ኖሮ ሚስቱ በዚሁ ስራው ለሌላ ሰው ጋር አግኝታው ከትዳሩ ተፋቶ አሁንም እየማገጠ ይገኛል። እና ዋናው ነገር እስቲ በዚህ በሰው አገር የእኔ ነው ያልኩት ሰው እንደፈለግኩ ካላደረግኩሽ ኬዝሽን አበላሽብሻለሁ ብሎ መዛቱ ምን ይባላል? እንደነዚህ ዓይነት ዋልጌዎችንስ ምን ቦታ ላስቀምጣቸው? በሉ በቸር ይግመጠን።

የሺመቤት ነኝ – ከሳንዲያጎ

---

ጤና ይስጥልኝ የላንዳፍታ አዘጋጆች

ምንም እንኳ በአይን ስጋ ባንተዋወቅም እንደማር የምትጥመው መጽሔታችሁ ምክንያት ሳላውቃችሁ አልቀረሁም።

መጽሔታችሁ ከወደ አገር ቤት፣ ከአሜሪካና አውሮፓ ያሉትን ኢትዮጵያውያን መልዕክትና አስተያየት የምታንፀባርቅ፣ የሐገራችንን ወቅታዊ ሁኔታዎችን የምታሳይ፣ የእውቀት መገብያና መዝናኛም ሁና አግኝታለሁና ከላንዳፍታ ወደ ብዙ ጊዜ ብትቀይሯትም የምትጠገብ አይደለችምና በርቱ ቀጥሉበት እላለሁ።

ሌላው ላሳስባችሁ የምወደው ቃላት በሰንጠረዡ በምታቀርቡበት ጊዜ እንምትወቀው የጐንደሩ አማርኛ፣ ከወሎው፣ የጐጃሙ ከሸዋው አለፍ አለፍ ብሎ ይለያያል። ለምሳሌ በጐንደር የምንጠቀምት የአንዳንድ ዛፎች ወይም ቁሳቁሶች ስም ከወሎው ጋር ይለያያል ስለዚህ በተቻለ መጠነ የምትመርጧቸውን ቃላቶች ለሁሉም አካባቢ የጋር አጠቃቀም ላይ የተመሰረቱ ቢሆን የሁሉን ተሳትፎና ሙከራ ያበረታታል ብዬ እገምታለሁ።

---

በመጨረሻ በድጋሚ መጽሔታችሁ ለህብረተሰባችን የእድገት ጐዳናና ሐሳብ ማንፀባረቂያ በመሆኗ አይዟችሁ በርቱ በማለት የምናበታችሁ

የናንተው

ጋሻው ተረፈ – ከሎሳንጀለስ

---

በስመ አብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሐዱ አምላክ አሜን ሰላም ለናንተ ይሁን፣ እግዚያብሔር አምላክ ስራችሁንና አላማችሁን ይባርክ።

መጽሔታችሁን አልፎ አልፎ አነበው ነበር። ብዙ ቁምነገሮችንም ስለምትይዝ እየሳበችኝ መጥታ ከአንባቢነት ወደ ተሳታፊነት ተሸጋገርኩ። በእውነት መጽሔት ማለት እንደዚህ ነው። እውትን ሳይለቁ የሁሉንም አንባቢ ስሜት መኮርኮር ሲቻል ነው። ለሀገራችን ለኢትዮጵያ የሚበጀውንና ህዝቦችዋን አንድ የማያደርገውን ጥበቡንና እውቀቱን እግዚያብሔር አምላክ ይሰጣችሁ ዘንድ ፀሎቴ ነው። ደግሞም እናንተን ምክንያት አድርጐ አንድ ያደርገን ይሆናልና በርቱ።

ባለፈው እትማችሁ ማለትም በህዳር/ታህሳስ 1989 ላይ «እምነት ወይስ ክህደት» በሚል ርዕስ ወንድም እያዩ በልልኝ የፃፉትን አንብቤ በጣም ደነቀኝ። ተደሰትኩኝም። ዋናው ቁምነገር የፃፍኩበት ለወንድም እያዩ ጥያቄ ስላለኝ ብታደርሱልኝ ወይም ማንኛውም አንባቢ መልስ እንዲሰጠኝ ነው። ጥያቄዬም የመናፍቃን ድርጅት (መንጤ ቆስጤ) የሚባለውን የሲ.አይ.ኤ. ድርጅት ወደአገራችን እንዳስገባው በብዙ ሰዎች ይነገራል፤ እንዲያውም ደርግም አጥብቆ ይከታተላቸው የነበረው ለዚህ ነበር ይባላል። በእርግጥ ደርግ ጉግማንጉግ (ሐይማኖት የለሽ) ነበር እና እንደምናውቀው ደርግም ሆነ በዘመኑ የነበሩ ወጣቶች እንደው ሙት ወቃሽ አያድርገኝና የሀገራችወን ታሪክ ትተው የነጭ ታሪክ፣ የራሽያን ታሪክ ሲያነበንቡ ኢትዮጵያ ጀግኖች ልጆች ለሀገራቸውና ለሐይማኖታቸው የሞቱ የሌላት አስመስለዋት ነበር። ወደ ጥያቄዬ ልመለስና ወንድሜ እያዩ ስለዚህ ጉዳይ ሳያውቁ አይቀሩምና ያላቸውን ቢያካፍሉኝ እወዳለሁ። ሌላው እዚህ እኔ ባለሁበት በቦስተን አንድ ወረቀት አንብቤ አልገባኝ አለ። ምን ይላል መሰላችሁ «ይኸ የኢትዮጵያ የወንጌላዊት ... ድርጅት ህልውናው ቢጠፋ (ቢፈርስ) ንብረቱ ለአሜሪካ ... ድርጅት እንዲሆን» ይላል። በእርግጥ «የቄሳሩን ለቄሳር» ስለሆነ አይደንቀኝም። ለማንኛውም ስለዚህስ ምን ትላለህ? እንግዲህ ወንድም እያዩ ስለፅሑፍህ እኔም ሆንኩ ወንድሞቼ ይበል! ብለናል እና በርታ! ለማንኛውም እግዚያብሔር አምላክ ሀገራችንንና ህዝቦቿን በመጠበቁ ይጠብቅልን እያልን ሁላችንም እንፀልይ። ወስብሐት ለእግዚአብሔር

የናንተው ብርሐን ነኝ –

ከቦስተን ማሳቹሴትስ

# እንዲህ ሆነ !

# ከዜና ማኅደር

## ተከታታይ የቦንብ ፍንዳታዎች በአዲስ አበባ

ከአለፈው ቅዳሜ አፕሪል 12 እስከ አፕሪል 14 1997 ባሉት ሁለት ቀናት ውስጥ በአዲስ አበባ ከተማ ሶስት የተለያዩ ቦታዎች በተወረወሩ የእጅ ቦንቦች ሳቢያ ባጠቃላይ 1 ሰው ሲሞት 75 ሰዎች የመቁሰል አደጋ ደርሶባቸዋል።

ቅዳሜ አፕሪል 12 ምሽት ላይ ፒያሳ ከሚገኘው ትግራይ ሆቴል ባልታወቁ ሰዎች የተወረወረው ቦንብ አንዲት የቡና ቤቱን ሠራተኛ ሲገድል 34 ሰዎችን ያቆሰለ መሆኑ ተገልጿል። ከትግራይ ሆቴል ፍንዳታ ጥቂት ደቂቃዎች በኋላ አምስት ኪሎ በሚገኘው የውጭ ዲፕሎማቶች፤ ቱሪስቶችና ሀብታም ኢትዮጵያውያን በሚዘወትሩበት ብሉ ቶፕስ በተሰኘ የጣልያን ምግብ ቤት በተወረወረ ሌላ ቦንብ 8 የውጭ አገር ሰዎች (6 እንግሊዞችና 2 ፈረንሳዮች) መቁሰላቸው ታውቋል። በብሉ ቶፕ ምግብ ቤት በደረሰው አደጋ ከፉኛ የቆሰሉት ሁለቱ የእንግሊዝ ተወላጆች ለፖሊስ ሥልጠና ከእንግሊዝ አገር በየቦታው ይላኩ የነበሩ መሆናቸው ይጠቀስ እንጂ በዚህ ወቅት ለዚሁ ተግባር አዲስ አበባ መገኘታቸው የተገለጸ ነገር የለም። ፈረንሣዮቹ ግን የኢትዮ ፈረንሣይን ግንኙነት 100ኛ ዓመት መታሰቢያ በተመለከተ በሚዘጋጅ የባህል ዝግጅት ላይ ተሣታፊ ለመሆን ባለፈው ፌብርዋሪ 15 1997 አዲስ አበባ የመጡ መጠናቸው ታውቋል። እነኚሁ ቀስለኞች ወደየግራቸው ለበለጠ ሕክምና ተልከዋል።

ይህ በዚህ እንዳለ ባለፈው ሰኞ አፕሪል 14 1997 ከሰዓት በኋላ 5 ፒ ኤም አካባቢ ማንነቱ ያልተረጋገጠ ሰው ሜርካቶ በሚገኘው ጣና የገበያ አዳራሽ በወረወረው ቦንብ 33 ሰዎች መቁሰላቸውን አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ የኢትዮጵያ ዜና አገልግሎትን በመጥቀስ ገልጿል። ይህን የቦንብ አደጋ ያደረግሁት እኔ ነኝ በማለት የደቡብ ምሥራቅ ኢትዮጵያን ኦጋዴን ግዛት ነፃ ለማውጣት ነው የምታገለው የሚለው አል ኢትሃድ አል ኢዝላም የተሰኘ ድርጅት መግለጹን ይኸው የፈረንሣይ ዜና ወኪል (AFP) ገልጿል።

---

## በአማራ ክልል የተደነገገውን የመሬት ይዞታ በመቃወም

### – የጎጃም ገበሬዎች ተቃውሞ ለማሰማት አዲስ አበባ ሄዱ፤
### – ተማሪዎች ሰልፍ በማድረጋቸው 200ዎቹ ታሰሩ፤
### – ከ20,000 በላይ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች ሰልፍ አደረጉ፤

ሁለት ሺህ የሚሆኑ የጐጃም ገበሬዎች ከ10 ቀን በላይ የፈጀ የእግር ጉዞ በማድረግ አዲስ አበባ ገብተው በጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ቢሮ አጠገብ በመስፈር በቅርብ ጊዜ የተደነገገውን የመሬት ይዞታ ድንጋጌ ከፉኛ የተቃወሙ መሆናቸውን አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ ማርች 14/1997 ባወጣው ዜና ገልጿል። እንደጋዜጣው አባባል ከነዚሁ ተቃዋሚ ገበሬዎች መካከል ሁለት መቶ የሚሆኑት ጉዳያቸው እስካልተፈፀመ ድረስ ከጠ/ሚኒስትሩ ቢሮ ፊት ለፊት የያዙትን ቦታ እንደማይለቁ ያስጠነቀቁ ሲሆን የተቀሩት ደግሞ አራዳ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተክርስቲያን ፊትለፊት ተሰብስበው ነበር። የአዲስ አበባ ሕዝብም ገበሬዎቹን ምግብና መጠጥ በመስጠት የረዳ መሆኑን ዜናው ጨምሮ ገልጿል።

ገበሬዎቹ የተቃወሙት የመሬት ይዞታ ማሻሻያ በተሰኘው ኮሚቴ በፊት ይጠቀሙበት ከነበረው መሬት ላይ ሁሉም ተወስዶ 1 ሄክታር መሬት ብቻ የመደበላቸው ሲሆን ቀደም ሲል በደርግ ጊዜ በተቋቋሙት የገበሬ ማኅበራት ኮሚቴ ውስጥ በገበሬው ተመርጠው ይሰሩ የነበሩ ገበሬዎች ሁሉ ምንም ያህል የቤተሰብ ብዛት ቢኖራቸውም ከአንድ ሄክታር በላይ መያዝ የለባቸውም ይላል ድንጋጌው። ከዚህ በተጨማሪም እነዚሁ የቀድሞ ገበሬ ማኅበራት ሹማምንት ካለፈው ሕዳር ወር ጀምሮ ከምሽቱ 12:00 (6:00 PM) በኋላ ከቤታቸው እንዳይንቀሳቀሱና ሌሎች ገበሬዎች በሚያደርጉት ስብሰባም ላይ እንዳይገኙ የተከለከሉ መሆኑን ዜናው ጠቁሟል።

የአዣንስ ፍራንስ ፕሬስ ጋዜጠኛ የጠ/ሚንስትሩን ጽ/ቤት ስለሁኔታው ሲጠይቅ አቶ ብርሃኑ ጀምበሬ የተባሉት የጽ/ቤቱ ተወካይ ስለነገሩ ምንም ነገር እንደማያውቁ መግለፃቸውን ሳይደብቅ፤ ከአንድ ወር በፊት ተመሳሳይ በሆኑ ጉዳይ ፓርላማ ውስጥ ለጠ/ሚኒስትር መለስ ዜናዊ ለቀረበላቸው ጥያቄ "ይህ ጉዳይ

ክልሎችን የሚመለከት እንጂ ‹የፌዴራሉን› መንግሥት አይመለከትም» ማለታቸውን ይኸው ዜና ጨምሮ አስታውቋል።

ባለፈው ማርች 21, 1997 የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ ተማሪዎች ይህንኑ በማስመልከት ለተቃውሞ ሰላማዊ ሰልፍ ከወጡት ተማሪዎች መካከል ወደ 200 የሚሆኑት ታስረው እንደነበረ ሲታወቅ ከእነዚህ ውስጥ ቁጥራቸው ያልታወቀ ተማሪዎች እስካሁን ድረስ እንዳልተፈቱም ታውቋል።

ባለፈው አፕሪል 6, 1997 ከ20,000 በላይ የሚሆኑ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የገበሬዎቹን ጥያቄ በመደገፍ በአማራ ክልል የተደነገገውን የመሬት ስሪት ፍጠ ተቃውመዋል። ይኸው ሰልፈኛ እስከ 1,500% ያደገውን የአ.አ ቤት ክራይ መጠንንም የተቃወመ ሲሆን የፖለቲካ እስረኞች እንዲፈቱ በተለይም የመሬት ስሪቱን ድንጋጌ በመቃወም ሰለተሰለፉ የታሰሩት የዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በአስቸኳይ እንዲፈቱ ጠይቀዋል።

## ዐባይ በ2002 ጉባኤ

የአባይን ውሃ አጠቃቀም በተመለከተ ከየካቲት 17–20 ድረስ የቆየ አለም አቀፍ ጉባኤ በአዲስ አበባ ውስጥ ተካሂዷል። በጉባኤው ላይ የላይኛውና የታችኛው አባይ ተፋሰስ ሀገሮች የሆኑት ኢትዮጵያ፣ ኬንያ፣ ታንዛኒያ፣ ብሩንዲ፣ ሩዋንዳ፣ ዛየር፣ ኡጋንዳና ሱዳን ሲሆኑ እንዲሁም የዓለም ባንክ፣ የአሜሪካ የካናዳና የሌሎች ሀገሮች ኤክስፐርቶች ጥናታዊ ዘገባዎችን በማቅረብ ተገኝተዋል።

ኢትዮጵያ የታችኛው ተፋሰስ ሀገሮች የሚባሉት ግብፅና ሱዳን ፍትሃዊ ባልሆነና የላይኛዎቹን የተፋሰሱን ሀገሮች በሚጐዳ መልክ ሲጠቀሙ መቆየታቸውን በዚሁ ጉባዔ ብትወቅስም ግብፅና ሱዳን ግን በዐባይ ወንዝ መጠቀም የሚገባንን ያህል አልተጠቀምንም ሲሉ ምላሽ ሰጥተዋል።

በዐባይ ውሐ አጠቃቀም ረገድ ግብፅና ኢትዮጵያ ብዙ ጊዜ አታካሮ መግጠማቸው የሚታወስ ሲሆን ኢትዮጵያ ግብፅን አባይን ከራሷ አሳልፋ ወደ ሌላ አገር ለመስጠት እንዳቀደች ስትናገር፤ ግብፅ ደግሞ ኢትዮጵያ ከእስራኤል መንግሥት ጋር በመተባበር ዐባይን ለመገደብ እንደወጠነች ወንጅላለች። ኢትዮጵያ በቅርቡ ለ50 ዓመት የሚቆይ የልማት እቅድ መንደፏን ባሳወቀችበት ወቅት ግብፅና ሱዳን አጥብቀው ተቃውመዋል። ግብፅ ግን በቅርቡ በዐባይ ውሃ በመጠቀም ተጨማሪ 26 ሚሊዮን ሕዝብ ሊያስፈርላት የሚችል የእርሻ ልማት ተግባራዊ በማድረግ ላይ ትገኛለች።

የዓለም ባንክ በበኩሉ ከእንግዲህ ለአነስተኛ ፕሮጀክቶች ካልሆነ በስተቀር የዘጠኙን የዓባይ ተፋሰስ ሀገሮች የጋራ ስምምነት ያላገኘ ዳጐስ ያለ ብድር እንደማይሰጥ አስታውቋል። በዚሁ ዐባይ በ2002 ጉባኤ ማጠናቀቂያ ላይ ዘጠኙ የተፋሰሱ ሀገሮች የዐባይን ውሃ ሚዛናዊ በሆነ መንገድ መጠቀሙ ለልማታቸው እንደሚበጅ የማጠቃለያ ሐሳብ ተሰንዝሯል።

## በአዲስ አበባ ጨርቆስ ገበያ ብዙ ንብረት ወደመ

ባለፈው የካቲት ወር በአዲስ አበባ ጨርቆስ ተብሎ በሚጠራው አካባቢ 976 የመኖሪያና የንግድ ሱቆች በእሳት ቃጠሎ መውደማቸው ይታወሳል። ይህ ባልታወቀ ምክንያት የተነሳውን የእሳት ቃጠሎ ለማጥፋት ከአንድ ቀን ተኩል በላይ የወሰደ ሲሆን በሰው ሕይወት ላይ አደጋ ያለመድረሱ ሲታወቅ በንብረት ረገድ ግን ከፍተኛ ውድመት እንደደረሰ ታውቋል። ጨርቆስ ከመርካቶ ቀጥሎ በአዲስ አበባ ከፍተኛ እንቅስቃሴ የሚታይበት የንግድ መናኸሪያ እንደሆነ ሲታወቅ በዚህ የእሳት ቃጠሎ ከ2 ሺህ ሕዝብ በላይ የሚሆኑ የአካባቢው ነዋሪዎች ያለመጠለያ የቀሩ በመሆኑ በ3 አዳራሾችና በ9 ድንኳኖች እንዲጠለሉ ተደርጉ ጊዜያዊ እርዳታ እየቀረበላቸው እንደሆነም ታውቋል። በሌላም በኩል ፖሊስ አደጋውን ያደረሰውን ያዝሁ በማለት አንድ ግለሰብ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን አቅርቦ ማሳየቱም የደረሰን ዜና ያሳያል።

## ምክትል የባንክ ገዥው ከ15 ግብረ አበሮቻቸው ጋር ተከሰሱ

የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ ምክትል ገዥ አቶ ነስረዲን መሐመድ ከ15 ግብረአበሮቻቸው ጋር በከባድ አታላይነትና በስልጣን ያላግባብ መገልገል በሚል ወንጀል በፌዴራሉ ከፍተኛ ፍርድ ቤት ክስ ተመስርቶባቸዋል።

ከብሔራዊ ምክትል ገዥው ጋር ክስ ከተመሰረተባቸው ውስጥ የኢትዮጵያ ንግድ ባንክ የቀድሞ ምክትል አስተዳዳሪና የባንክ ኢንስፔክተሮች እንደሚገኙበት ሲታወቅ በኢትዮጵያ ካቻማሊ ተብሎ የሚታወቀው የአውቶቡስ ኩባንያ ሥራ አስኪያጅ ኢጣሊያዊ ዜጋ፣ ከኢትዮጵያዊት ሚስታቸው ጋር ከአቶ

ነስረዲን ጉዳይ ከተከሰሱት የግል ነጋዴዎች ውስጥ እንደሚገኙበት ታውቋል። አቶ ነስረዲን ከባንኩ ምክትል ገዥነት የተባረሩት ምክትል ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩት አቶ ታምራት ከስልጣን ከመወገዳቸው ሁለት ቀናት ቀደም ብሎ ሲሆን የቅርብ ተባባሪ እንደነበሩም ይሰማል።

## የቀድሞ መንግሥት የደህንነት ሠራተኞች እየታሰሩ ነው

በደርግ መንግሥት ውስጥ በልዩ ልዩ ደረጃ በደህንነት ሠራተኝነት ያገለግሉ የነበሩ ግለሰቦች ተለቅመው እየታሰሩ መሆናቸው ታውቋል። ኢህአዴግ መላው ኢትዮጵያን በተቆጣጠረበት በ1983 ዓ/ም የደህንነት ሠራተኞች ታስረው ምንነታቸው ከተጣራ በል በነፃ መለቀቃቸው ሲታወስ አሁን እንደገና እየተለቀሙ የሚታሰሩበት ጉዳይ ግን ምክንያቱ አልታወቀም። በሌላ በኩል ደግሞ በደርግ መንግሥት በአብዮት ጥበቃ አባልነት ሲሰሩ የነበሩ የቀበሌ ተመራጮችና የቀድሞ መንግሥት መኮንኖች ባልተገለፀ ምክንያት ከአዲስ አበባና ከተቀሩትም የኢትዮጵያ ክልሎች መታሰራቸው ይሰማል።

## ሕወሐት የአንድነት ኃይሎች በሙሉ ኢትዮጵያን እንዲጠብቁ ጥሪ አቀረበ

የሕወሀት/ኢህአዴግ አመራር በምሥራቅና በምዕራብ በተቃዋሚ ኃይሎችና በሱዳን ተወጥሮ በተያዘበት በአሁን ወቅት ድርጅቱ የተመሰረተበትን 22ኛ አመት ምክንያት በማድረግ በቴሌቪዥን በሰጠው ድርጅታዊ መግለጫ የአንድነት ኃይሎች ሁሉ በመተባበር የኢትዮጵያን አንድነት መጠበቅ አለባቸው ሲል ጥሪ አቀረበ።

ኤርትራን ከኢትዮጵያ ለማስገንጠል ከፍተኛ ሚና የተጫወተውና ለተቀሩትም የኢትዮጵያ ክፍሎች ለመገንጣጠል አመቺ ሕገ መንግሥታዊ አንቀጽ ያስቀረጸው ሕወሀት ራሱ በፈጠረው ወታደራዊ ፍጥጫ አመራሩ ስጋት ላይ በወደቀበት ወቅት የአንድነት ጥበቃ ጥሪ ማሰማቱ የሚያስቅና የሚያሳዝን ስሜት በኢትዮጵያ ሕዝብ ዘንድ ፈጥሮአል። ህወሀት ኢትዮጵያ ለዳር ድንበር ጥበቃዋ ለዘመናት ያደራጀችውን የባህር፣ የአየር ኃይልና የምድር ጦር ድርጅታዊ ኃይል እንዳልነበር አድርጎ በማፍረሱና የባሕር በሯ እንዲዘጋ በማድረጉ የኢትዮጵያ ሕዝብ ክብሩና ኩራቱ ኮስሷል።

ህወሀት በሰጠው አመራር ራሱ ከተነሳበት ክልል ያሰባሰበውን ኃይል ማእከል ያደረገና ለቁጥር ያህል ከተለያዩ ክልሎች አቀናጅቶ የመከላከያ ሠራዊት መሰረትኩ ቢልም ይህ ሠራዊት አሁን በየጦር አውድማው እንደሚታየው ከልምድም ሆነ ከወታደራዊ ብቃቱ አንፃር የሚመጥን ሆኖ እንዳልተገኘ ዘገባዎች ይጠቁማሉ።

## በጅጅጋ በ15 ወረዳዎች ድርቅ ተከሰተ

በሶማሊያ ክልላዊ አስተዳደር በጅጅጋ አውራጃ በ15 ወረዳዎች በተከሰተው ድርቅ ሳቢያ በርካታ ቁጥር ያለው ሕዝብ እርዳታ እንደሚፈልግ ተገለጠ።

በዚህ አመት መግቢያ ላይ መጣል የነበረበት ዝናብ በመቅረቱ ድርቅ ላጠቃቸው የኦጋዴን አካባቢዎች 60 ሺህ ኩንታል የእህል እርዳታ ቀደም ሲል መላኩን የመንግሥት መገናኛ ብዙኃን ዘግበዋል። በአካባቢው ከፍተኛ የውኃ እጥረት በማጋጠሙ ከተለያዩ የግል ድርጅቶችና መንግሥታዊ መስሪያ ቤቶች በተገኙ የቦቴ መኪናዎች ውሃ በድርቁ ለተጎዳው ሕዝብ እየታደለ መሆኑም ታውቋል።

## አማራጭ ኃይሎች ኢህአዴግ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር የጀመረውን ግጭት ነቀፈ

የኢትዮጵያ የሰላም የዴሞክራሲ አማራጭ ኃይሎች ምክር ቤት የውስጥ ችግሮችን አቅጣጫ ለማሳት ከጎረቤት ጋር ግጭት መፍጠር የሕዝብ እምነት የሌለው መንግሥት ባሕርይ ነው በሚል ርዕስ ባወጣው መግለጫ ኢህአዴግ ከሱዳንና ከሱማሊያ ጋር የጀመረው ጦርነት ከኢትዮጵያ ሕዝብ እውቅና ውጪ የሚካሄድ መሆኑን አውግዞ፤ ኃላፊነት የጎደላቸው መሪዎቹን ፍቃድ ለማስፈፀም ሲል የኢትዮጵያ ሕዝብ የወጣት ልጆቹን ደም ለማፍሰስ የማይፈቅድ መሆኑን አስገነዘበ።

የአማራጭ ኃይሎች መግለጫ የሀገሪቱ ውስጣዊ የፖለቲካ ሁኔታና የኢኮኖሚ አቋም በውጥረት ላይ እያለ ከሱዳንና ከሱማሊያ ጋር የነበረው የመልካም ጉርብትና መንፈስ እየሻከረ እንዲሄድ ተደርጐ ወደ ጦርነት መግዛዝ መድረሱ አሳሳቢነት የዓለም የዜና አውታሮች የየዕለት ትኩረት መሆኑን ጠቅሶ የኢትዮጵያ መንግሥት ለጦርነት መማዘዝ ደረጃ የማያደርሱ፣ የኢትዮጵያን ሉዓላዊት የተጋፉ ሁኔታዎች በግልጽ ሳይከሰቱና ለባለቤቱ ለኢትዮጵያ ሕዝብ ሳይገለጽለትና ሳያውቀው ከጎረቤት መንግሥታት ጋር ጦር መማዘዙ ያለውን አሳሳቢነት ገልጿል።

አማራጭ ኃይሎች የተጀመረው የጦርነት

ፍልሚያ እየተባባሰ ከመሄዱ በፊት በተባበሩት መንግሥታትና በአፍሪካ አንድነት ድርጅት አማካይነት ውጥረቶች የሚላሉበት ሠላማዊ መንገድ ሁሉ በአስቸኳይ እንዲፈለግ ጥሪ አቅርቧል።

## የአክሱምን ሐውልት ለማስመለስ ልዑካን ሄዱ

በአምስት ዓመት የኢጣሊያ ወረራ ጊዜ ወደ ሮም የተወሰደው የአክሱም ሐውልት እንዲመለስ ለማነጋገር በውጭ ጉዳይ ምክትል ሚኒስትሩ በአቶ ተቀዳ ዓለሙ የሚመራ አንድ የልዑካን ቡድን ወደ ኢጣሊያ መሄዱ ታውቋል።

ሐውልቱ በሮም ማዕከል ተተክሎ ውበት የሰጠ ከመሆኑም በላይ ጣሊያኖች ከታሪካቸው ጋር ስለሚያያይዙት ባለሥልጣናቱ ሐውልቱን ከመመለስ ይልቅ በገንዘብ ሊደራደሩ የሚፈልጉ እንደሚመስል ይነገራል። ሥልጣን ላይ ያለው የኢትዮጵያ መንግሥት ከሌሎች ቅርሶች የበለጠ ለሀውልቱ ትኩረት መስጠቱና ከኢጣሊያ ጋር የተሻለ ግኑኝነት ያለው መሆኑ ለኢጣሊያ ባለሥልጣናት ጉዳዩን ውስብስብ ያደርግባቸዋል።

## በኦጋዴን የካሉብ ጋዝ ፋብሪካ ተከላ ይጀመራል ተባለ

አብዛኛውን በመንግሥት እንዲሁም ቀሪው በመንግሥታዊ ድርጅቶችና በግለሰቦች ሽርክና የሚንቀሳቀሰው የካሉብ ጋዝ ፋብሪካ ተከላ በቅርቡ ሥራውን እንደሚጀምር በኢትዮጵያ መንግሥት መገናኛ ብዙሃን መገለጡ ታወቀ። ሥራው ሲጠናቀቅ በየዓመቱ 65 ሺህ ቶን ቡታ ጋዝ፣ ቤንዚን፣ ናፍታና ላምባ የማምረት አቅም ይኖረዋል የሚባለው ይህ ፕሮጀክት እንዲፋጠን ከሐረር ሸላቦ ድረስ 570 ኪሎ ሜትር የመንገድ ሥራ መጀመሩም ተገልጿል። በቦታው 74 ቢሊዮን ኪዩቢክ ሜትር የተፈጥሮ ጋዝ ክምችት እንዳለ ተጠቅሷል።

## ከቤተክርስቲያን የታፈሰች አንዲት ወጣት በፖሊሶች ዱላ አእምሮዋን ሳተች

ጥር 4 ቀን 1989 በዮሐንስ ቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ በተነሳው ግጭት ሳቢያ በፖሊሶች ታፍሰው ከተወሰዱት ምዕመናን መካከል አንዲት ፍሬህይወት ኃይሉ የተባለች ወጣት በመርግሪ ፖሊሶች ዱላ ብዛት አእምሮዋን እንደሳተች ታወቀ። ይህች በፖሊሶች ዱላ አእምሮዋን የሳተችው ወጣት በእለቱ የኢትዮጵያ ሰንደቅ ዓላማ ቀለም ያለውን ከሹራብ ክር የተሰራ ኩፍያ አድርጋ በቤተክርስትያኑ ግቢ በመገኘቷ ብቻ ታፍሳ ለዚህ አስከፊ ችግር መዳረጓን የወላጆችዋንና የጓደኞቿን ምስክርነት በመጥቀስ ጋዜጣው ዘግቧል። መርማሪዎች በዕለቱ በታፈሱት ምዕመናን ላይ ከፍተኛ የድብደባና የግርፋት ስቃይ እንደሚፈፅሙና የተለያዩ ስለታም ጉራዴዎችን በመጠቀም ጭንቀት እንደሚፈጥሩባቸውም ሲታወቅ ፓትሪያርኩ ባሉበት በእስጢፋኖስ ቤተክርስቲያን የተገደሉት የባህታዊ ፈቃደሥላሴ ገዳዮች ለፍርድ እንዲቀርቡ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ግፊት እንዲያደርግ የሚያሳስቡ ጽሁፎች ለኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ጉባኤ፣ ለኢትዮጵያ የሕግ ባለሙያዎች ማኅበርና ለሌሎችም በአካልና በጽሑፍ እየቀረቡ መሆናቸው ታውቋል።

## የሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት በጄኔራል ኃየሎም ስም ተሰየመ

በኢትዮጵያ አንጋፋውና ለኢትዮጵያ አንድነት የተዋደቁ ምርጥ የጦር መኮንኖች በማፍራቱ የሚታወቀው የሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት፤ ሜጀር ጄኔራል ኃየሎም አርአያ አካዳሚ ተብሎ መሰየሙ ታወቀ።

ሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት ለመጀመሪያ ጊዜ አሰልጥኖ ያስመረቃቸው የጦር መኮንኖች በ1928 የወራሪውን የፋሺስት ጦር ለመውጋት በዱር በገደሉ በመሰማራት ታላቅ አርበኝነት የፈፀመው የጥቁር አንበሣ ጥንስስ መስራቾች እንደሆኑ ታሪክ የዘገበው ሲሆን የሆለታ ገነት ጦር ት/ቤት በኃየሎም ስም መሰየሙ ኢህአዴግ መራሹ መንግሥት የኢትዮጵያን ሕዝብ ስሜት ለማደብዘዝና ታሪኩንም ለማጥፋት በስልት የጀመረው ዘመቻ አካል ነው ሲሉ አንጋፋ የጦር መኮንኖችና የታሪክ ሰዎች ቅሬታቸውን ማሰማታቸው ተገልጿል። ከዚሁ ጋራ የደረሰን ዜና እንደሚያስረዳው ጄኔራል ኃየሎም አርአያን ገደለ የተባለው ኤርትራዊው ጀሚል ያሲን በሞት እንዲቀጣ የተወሰነበት መሆኑ ሲታወቅ ክሶችን መርምሮ ፍርድ ለመስጠት ከአምስት ዓመት በላይ በሚወስድበት በአሁኑ ጊዜ በሐየሎም ገዳይ ላይ በአንድ አመት ጊዜ ውስጥ አፋጣኝ ፍርድ መስጠቱም ብዙዎችን አነጋግሯል።

## በቀይ ሽብር ሳቢያ የተከሰሱት ለፍርድ ሊቀርቡ ነው ተባለ

በብዙ ሺህ የሚቆጠሩ በቀይ ሽብር ሳቢያ የተከሰሱ የቀድሞ ወታደሮች፣ ካድሬዎችና የኢሠፓ አባላት ፍርድ ቤት ሊቀርቡ ነው ተባለ።

የኦሎምፒክ ወርቅ ተሸላሚ ማራቶኒስቱና የ62 ዓመት አዛውንት የሆነው ማሞ ወልዴም ከነዚሁ ተከሳሾች መሐል እንደሚገኝ ተጠቁሟል።

ልዩ አቃቢ ሕግ ጽ/ቤት በተጨማሪ ከከሰሳቸው 5198 ሰዎች መሐል 2256ቱ ከ1991 (እ.ኤ.አ) ጀምሮ በቁጥጥር ስር የነበሩ ሲሆን ቀሪዎቹ 2942 ኰሎኔል መንግሥቱን ጨምሮ የተከሰሱት በሌሉበት ነው።

## የኦሮሚያ ልማት ማህበር ከ107 ሚሊዮን ብር በላይ አገኘሁ አለ

የኦሮሚያ ልማት ማህበር (ኦልማ) በስልክ ባደረገው ቅስቀሳ ከ107 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር በላይ ለኦሮሚያ ክልል ልማት ማግኘቱን አዲስ ዘመን ጋዜጣ ዘገበ። በተደረገወ የገንዘብ ስብሰባ ዘመቻ ላይ ፕሬዛዳንት ነጋሶ ጊዳዳም የተሳተፉበት መሆኑ ሲታወቅ ፕሬዝዳንቱ በኦሮሞ ሕዝቦች መካከል ምንም የተለያየ የፖለቲካ አመለካከት ቢኖርም ለልማት ጉዳይ እንዲተባበሩ ተማጥነው እንደነበረ ጋዜጣው ገልጿል። ይህ በስልክ የተነገረው መዋጮ ቃል የተገባ ይሁን በእጅ የገባ መሆኑ የተገለፀ ነገር የለም ተብሏል።

## እስረኞች ሊያመልጡ ሲሞክሩ ተገደሉ

በአዲስ አበባ ከርቸሌ 14 እስረኞች ማርች 10/1997 ለሕክምና ወደ ክሊኒክ ሲወሰዱ ለማምለጥ ባደረጉት ሙከራ አምስቱ ሲገደሉ የቀሩት ዘጠኙ ተመልሰው መያዛቸውን አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ የአዲስ አበባውን ሬዲዮ ጣቢያ በመጥቀስ ያስተላለፈው ዜና ይገልፃል። አምልጠው ከነበሩት እስረኞች 3ቱ በእስር ቤቱ አቅራቢያ ከሚገኘው የአፍሪካ አንድነት ድርጅት(OAU) ቢሮ ቢገቡም የአአድ ኃላፊዎች እስረኞቹን ይዘው መስጠታቸው ታውቋል። ይህ ከመሆኑ ጥቂት ሳምንታት በፊት ቀጠሮ ከነበራቸው እስረኞች መካከል ሁለቱ ከፍርድ ቤቱ አምልጠው መሰወራቸው ሲታወቅ በዕለቱ ፕሬዚዳንት ነጋሲ ጊዳዳ በቻይናው መሪ ሞት የተሰማቸውን ኃዘን ለመግለጽ ወደ ቻይና ኤምባሲ በመሄድ ላይ ባሉበትና ከፍተኛ በከፍተኛ ወታደራዊ ጥበቃ ተወጥሮ በነበረበት ሰዓት ነበር ተብሏል።

## የሳንባ ነቀርሳ በሽታ ፈውስ

በየቀኑ 4 ታብሌቶችን ለ6 ወር በመዋጥ ሳንባ ነቀርሳ ከተባለ ቀሳፊና ብዙ ሕዝብ ከፈጀ በሽታ ለመዳን የሚያስችል መድሐኒት መፈጠሩን የዓለም ጤንነት ድርጅት (WHO) ማርች 19, 1997 ባወጣው መግለጫ አብስሯል።

"በሚቀጥሉት 10 ዓመታት ውስጥ በበሽታው ሊሞቱ የሚችሉ 10 ሚሊዮን ሕዝብ ማዳን ይቻላል» በማለት የWHO ዲሬክተር ሂሮሺ ናካጂማ መግለፃቸውን አዣንስ ፍራንስ ፕሬስ ዘግቧል። የ1997 የዓለም ጤና ድርጅት (WHO) ሪፖርት እንደዘገበው 75% የሚሆኑት የሳንባ ነቀርሳ በሽተኞች የሚገኙት በ13 አገሮች ብቻ መሆኑንና ከእነዚህም ውስጥ አንዷ ኢትዮጵያ መሆኗንም ጠቁሟል።

## የጦቢያ አዘጋጆች ተፈቱ የኢትዮ ታይምስ ጋዜጣ አዘጋጅ 6 ወር ተፈረደበት

እስካለፈው ጥር ማብቂያ ድረስ ታስረው የነበሩት የጦቢያ አዘጋጆች በዋስ ተለቀው ሥራቸውን መጀመራቸው ታውቋል። የፌዴራሉ የመጀመሪያ ደረጃ ፍርድ ቤት እያንዳንዳቸው የ5 ሺህ ብር ዋስ በመጥራት እንዲፈቱ የወሰነባቸው መሆኑ ሲታወቅ አዘጋጆቹ ከተፈቱ በኋላም ተቋርጦ የነበረው ጦቢያ ሳምንታዊ ጋዜጣና ጦቢያ መጽሔት ለአንባቢዎቹ መቅረቡ ታውቋል።

ይህ በዚህ እንዳለ ኢትዮ–ታይም የተባለው ከፊል በአማርኛና ከፊል በእንግሊዝኛ ቋንቋዎች የሚታተመው ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ አቶ ክፍሌ ሙላት የፌዴራሉ ወንጀል ችሎት የ6 ወራት እስራት ፈርዶበታል። አዘጋጁ የተፈረደበት በዚምባብዌ–ሐራሬ በኰሎኔል መንግሥቱ ተቃጣ ስለተባለው ግድያ አቶ መለስ በጉዳዩ አሉበት የሚል ዜና በማስተላለፉ ነው ተብሏል።

## በቀይ ባህር በተገለበጠው ጀልባ 89 ኢትዮጵያውያንና ኤርትራውያን ሞቱ።

ባለፈው የካቲት ወር መጨረሻ ላይ 95 ሰዎችን አሳፍሮ ወደ ሳውዲ አረቢያ ይጓዝ የነበረው ጀልባ ባልታወቀ ምክንያት በደረሰበት የመገልበጥ አደጋ 89 ኢትዮጵያውያንና

ኤርትራውያን ሞተዋል። የፈረንሳይ ዜና ወኪል ባሰራጨው ዜና ከተሳፋሪዎቹ 18ቱ ኤርትራውያን ሲሆኑ የቀሩት ኢትዮጵያውያን ነበሩ ብሎአል። የኤርትራ ሬዲዮ ለጀልባው መገልበጥ የሰጠው ምክንያት መጫን ከሚገባው በላይ 50 ተሳፋሪዎችን በመጫኑ ነው ብሏል። 6 ሰዎች ብቻ ከአደጋው መትረፋቸው ሲታወቅ የኤርትራ መንግሥት ወጣቱን በብሔራዊ ውትድርና በማስጨነቁ፣ የሥራ አጥነት ችግር በመባባሱ፤ እንዲሁም የኢትዮጵያን መንግሥት የጐሳ ፖለቲካን በመቃወም የኢትዮጵያና የኤርትራ ወጣቶች ከአገር ለመውጣት በሚያደርጉት ሙከራ በተደጋጋሚ ጊዜ በቀይ ባህር ውስጥ እየሰጠሙ የአሣ ቀለብ ሆነው ቀርተዋል።

## በኤርትራ የሱዳን አማፂያን ጦር ሰፈር በሽምቆች ተመታ

በኤርትራ ባርካ አውራጃ ውስጥ ከሚገኙት የሱዳን አማፂያን ግንባሮች የአንዱ የጆን ጋራንግ ጦር ሰፈርን በከፍተኛ ወታደራዊ የማጥቃት ዘመቻ በመመታቱ 100 ያህሉ ሲሞቱ 250 መቁሰላቸውን ከኤርትራ አካባቢ የተገኙ የመረጃ ምንጮች ጠቅሰዋል ተባለ። በጋራንግ ጦር ላይ አደጋውን ያደረሱት በሱዳን መንግሥት የሚደገፉ አንጃ ታጣቂዎች ሳይሆኑ እንዳልቀሩ ተገምቷል።

ሱዳን በየጊዜው አማፂያኑ በኢትዮጵያ፣ በኤርትራና በኡጋንዳ ጦር ኃይሎች እንደሚደገፉ ወቀሳ የምታሰማ ቢሆንም ሦስቱም አገሮች የለንበትም በማለት የሱዳንን ወቀሳ ሐሰት ነው ቢሉም ሱዳን የኢትዮጵያ ወታደሮች ከአማፂያኑ ጋር ተደባልቀው ሲዋጉ መማረካቸውን በማስረጃ ለማቅረብ እንደምትችል ገልፃለች።

## ኤምባሲዎችና ዓለም አቀፍ ድርጅቶች የነበሩባቸውን ቤቶች ለኢሕአዴግ ባለሥልጣኖችና ደጋፊዎች ሊያስረክቡ ነው

በቦሌ አካባቢ የሚገኙ የኪራይ ቤቶች ለምርጥ ሕወሓት/ኢሕአዴግ ባለሥልጣናትና ደጋፊዎች መኖሪያ እንዲሆኑ ከ50 በላይ የሚሆኑ ቤቶች እንዲለቀቁ ጥናት ተይዟል። በዚሁ መሰረት ቤቶቹ ሲለቀቁ ኪራይ ቤቶች በዓመት ከ5 ሚሊዮን የኢትዮጵያ ብር ወይንም 794 ሺህ ዶላር በላይ ያጣል ተብሏል።

በዚህ ዘመቻ 26 ኤምባሲዎች፣ 3 በአውሮፓ ሕብረት፣ 2 በኢልካ፣ 1 በተባበሩት መንግሥታት፣ 1 በአሚቼ፣ 3 በክርስቲያን ሕፃናት ፈንድ፣ 1 በቶታል፣ 13 በውጭ አገር ግለሰቦችና ኢትዮጵያውያን የተያዙ ቤቶች ሲሆኑ እነዚህ ለጊዜው በግልፅ ለጥናት ይቀረቡ እንጂ በጥቅሉ የሚለቀቁት ቤቶች ወደ 160 እንደሚጠጉ አንዳንድ የዜና ምንጮች ይጠቁማሉ።

## ዲፕሎማቱና የቴሌቪዥን ኤክስፐርቱ ኮበለሉ

በተባበሩት መንግሥታት ድርጅት የኢትዮጵያ ሚሽን 2ኛ ፀሐፊ ሆነው በማገልገል ላይ የነበሩት አቶ ስለሽ የሸዋነው የውጭ ጉዳይ ሚኒስትር ሥዩም መስፍን የኢሕአዴግ አባል እንዲሆኑ ያቀረቡላቸውን ጥያቄና በተደጋጋሚም የተደረገባቸውን ማስፈራራት ለመቀበል ፈቃደኛ ባለመሆናቸው ሥራቸውን በመልቀቅ በስደት ለመቆየት መወሰናቸውን ታውቋል።

ይህ በእንዲህ እያለ በኢትዮጵያ ቴሌቪዥን ከስድስት ዓመት በላይ በቴክኒካል ኢንጅነሪንግ ማስተባበያ ተቆጣጣሪ ኤክስፐርትነት ሲያገለግሉ የቆዩት አቶ ሀብታሙ አዬታ በኢሕአዴግ የደረሰባቸው ችግር ምክንያት ጀርመን እንደሄዱ በዚያው ለመቅረት መገደዳቸውን አስታውቀዋል። «የኢሕአዴግ አባል እንድሆን ተገደድኩ፣ የኢሕዴድን ዓላማና ፕሮግራም እንዳጠና ፎርም እንድሞላ ተደረግሁ» የሚሉት አቶ ሀብታሙ አባል ከሆኑም በኋላ የኢሕአዴግ ካድሬዎችና የደህንነት አባላት በሥራዬ ጣልቃ እየገቡ ስውር የቪዲዮ ቀረፃዎችን ያለፍላጎታቸው እንዲሰሩ መገደዳቸውን፣ የመሥሪያ ቤቱ ንብረቶች ማለትም የተለያዩ የኢዲቲንግ ማሽኖችና የቪዲዮ ካሜራዎች በውሰት ስም ከወጡ በኋላ በግል ለከፈቷቸው ስቱዲዮች መገልገያ ሆነው መቅረታቸውን በቁጭት መግለፃቸው ታውቋል።


**በኮምፒውተር የአማርኛና የእንግሊዝኛ የጽሑፍ ሥራዎች በተቀላጠፈ ሁኔታ**

መጽሐፍት፤ መጽሔቶች ወይም የተለያዩ የአማርኛ ጽሑፎችን ጥራት ባለው ሁኔታ ለማሠራት ከፈለጉ ደውለው ገነትን ያነጋግሩ።
ስልክ — (404)508—4657
ፋክስ — (404)508—2447

# አልሰሙ እንደሆን !

## ያልሰሙት ዜና ሊሆን ይችላል በሚል ግምት ትንሽ ዘግየት ያሉ ዜናዎችን አጠር አድርገን የምናቀርብበት አምድ፡

□ በአዲስ አበባ የአሜሪካ ኤምባሲ ጽ/ቤት ባወጣው ዜና ጠቀስ መግለጫ አሜሪካ ከኢትዮጵያ መከላከያ ሚኒስትር ለተወጣጡ 30 ሲቪልና ወታደራዊ ባለሥልጣናት በአሜሪካ ወታደራዊ ጠበብት ለአንድ ሣምንት የቆየ ወታደራዊ ሕግ፣ ወታደሩ ሕግንና ሰላም ለማስጠበቅ ስላለው ድርሻና ግዳጅ፣ እንዲሁም የሕግ ሚና በሚል የውይይት ርዕስ ስልጠና መስጠቱን አስታወቀ። (የካቲት/1989)

□ የቀድሞው የሱዳን ጠቅላይ ሚኒስትር የነበሩትና በአሁኑ ወቅት የሱዳን አማ ፓርቲ መሪ የነበሩት ሳዲቅ አልመህዲ በድብቅ በአዲስ አበባ ቆይታ በማድረግ ከኢትዮጵያ ባለስልጣናት ጋር ከሀገራቸው ሱዳን ጋር ስለሚደረገው ጦርነት መነጋገራቸው ታውቋል።

□ በየካቲት ወር አጋማሽ ላይ አንድ የኢትዮጵያ አየር ኃይል አይሮፕላን መሬት ላይ ተከስክሶ በመውደቁ በውስጡ ያሉት በሙሉ መሞታቸው ታወቀ። ወያኔ የራሱን ፓይለቶች ማሰልጠን ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ ከዚህኛው ጋር ወደ አስር የሚሆኑ አውሮፕላኖች መከስከሳቸውን አብሮ የተያያዘው ዜና ገልጿል።

□ የቀድሞ የኢትዮጵያ ጦር አባላት ለግዳጅ የሚፈለጉ መሆኑ ተጠቅሶ በተወሰኑ ቦታቸው ቀርበው እንዲመዘገቡ የሕወአት መንግሥት ጥሪ አደረገ።

□ በአሁኑ ወቅት ኢትዮጵያ ውስጥ በመካሄድ ላይ ባለው የቀድሞ ባለስልጣናትና ኢሠፓ አባላት የፍርድ ችሎት ላይ የቀረበ አንድ ምስክር ቲሞቲ ዊልሰን የተባለ አሜሪካዊ በደርግ ዘመን በተካሄደው የቀይ ሽብር ግርፊያና እጅና እግሩ በመርማሪዎች ታስሮ በመሰቃየት ላይ እንደነበረ የተመለከተ መሆኑን ሲመሰክር ዋሽንግተን የሚገኝና የቀድሞ የስቴት ዲፓርትመንት ባለሥልጣን የሆነ ሰው ይህ የተጠቀሰው አሜሪካዊ ቲመቲ ዊልሰን በአሜሪካ ኤምባሲ ሠራተኝነት ሽፋን የሲአይኤ ወኪል እንደነበረና ለአንድ ወር ተኩል ያህል ታስሮ የተለቀቀ መሆኑንና በመገረፍም ሆነ በመደብደብ አካላቱ ላይ ምንም ጉዳት እንዳልደረሰበት ገልጿል።

□ የመላው ዐማራ ሕዝብ ድርጅት (መዐሕድ) በእስር የሚንገላቱትን መሪውን የ«ፕሮፌሰር አሥራት ወልደየስ ይፈቱ» 3ኛውን የሻማ ምሽት እንዳያካሂድ በክልል 14 የስብሰባ ፈቃድ ሲጪ ቢሮ ተከለከለ። ከዚህ በፊት ለሁለት ጊዜ ያህል በአዲስ አበባ ማዘጋጃ ቤት ፊት ለፊት በተካሄደው «አሥራት ይፈቱ» የሻማ ምሽት በአባላቱና ደጋፊዎቹ ሻማ በማብራትና የኢትዮጵያን ሰንደቅ ዓላማ በመያዝ ሰላማዊ በሆነ መንገድ ፕሮፌሰር አሥራት እንዲፈቱ ጥያቄያቸውን አስምተው እንደነበር አይዘነጋም። (የካቲት/1989)

□ ሐረር ውስጥ ጀጐል አካባቢ በሚገኝ በላይነህ ተብሎ በሚጠራ ሆቴል ላይ የካቲት 3 ቀን ማታ በተጣለ ቦምብ 2 ሰዎች ወዲያውኑ ሲሞቱ ከ40 በላይ ቆሰሉ። በፈንጂ አደጋው ሕይወታቸው ያለፈው አንድ የሆቴሉ ዘበኛና አንድ ፖሊስ መሆናቸው ሲታወቅ የቦንብ ፍንዳታውን ያደረሱ ኃይሎች ማንነት ገና ይፋ አልወጣም። (የካቲት/1989)

□ የኤርትራ መንግሥት በደርግ ዘመን ግለሰቦች በማኅበር ተደራጅተው የሰሯቸውን 147 መኖሪያ ቤቶች መውረሱን አንድ የኤርትራ ጋዜጣ አስታውቋል። በሌላ በኩልም ኤርትራ ውስጥ ሀብት አላቸው ተብለው የሚገመቱና በደርግ ጊዜ ቦታ በነፃ አግኝተው ቤት የሰሩ ግለሰቦችም በካሬ ሜትር 600 ብር ሂሳብ እንዲከፍሉ ተጠይቀዋል። (የካቲት/1989)

□ ኤርትራ ውስጥ በባህል አውራጃ ሃብሮ በቲባለ ቦታ ከየት አቅጣጫና ማን እንደወረወረው ባልታወቀ የእጅ ቦምብ 12 ወጣቶች ተገድለው 21 መቁሰላቸውን ተገለጠ። ወጣቶቹ የተገደሉት በጭፈራ ላይ እንዳሉ መሆኑ ሲታወቅ አደጋውን ያደረሰው ወንድና ሴት በአንድ ላይ ጭፈራ ማካሄዳቸውን የሚቃወም የእስልምና ቡድን ነው ሲል የኤርትራ መንግሥት ማስታወቁ ታውቋል። (የካቲት/1989)

□ የደቡብ አፍሪካ መንግሥት በሀገሩ ከሚገኙት ኢትዮጵያውያን ስደተኞች ውስጥ የተወሰኑትን ለኢህአዴግ አገዛዝ አሳልፎ ለመስጠት መወሰኑን ዋና ጽ/ቤቱ በርሊን ጀርመን የሆነው የኢትዮጵያ የፖለቲካ እስረኞች አንድነት ኮሚቴ ያስታወቀ ሲሆን ከእነዚህ ስደተኞች ውስጥ አቶ ብዛየሁ ዓለማየሁ የተባሉ በደርግ መንግሥት በሚኒስትር ማዕረግ የሚኒስትሮች ምክርቤት ኃላፊ የነበሩትን እንደሚጨምር ገልጿል። (የካቲት/1989)

# ስለ ኢትዮጵያ አንድነት ግንባር ሠራዊት መግለጫ ተሰጠ።



ሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት

"ሰላምና ዴሞክራሲ" በተሰኘው የኢትዮጵያውያን ድርጅት አማካይነት በተዘጋጀ ስብሰባ ላይ የኢድኃቅ ተወካይ የሆኑት ሻለቃ ኢያሱ አያልቅበትና አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ አትላንታ በመገኘት ስለኢትዮጵያ አንድነት ግንባር አፈጣጠርና ሠራዊት ምሥረታ ሰፋ ያለ መግለጫ ሰጡ። የአትላንታው ሰላምና ዴሞክራሲ ድርጅት ስብሰባው ሊቀንበር አቶ ተፈሪ ቸርነት የመግቢያና የማስተዋወቂያ መግለጫ ከሰጡ በኋላ የኢድኃቅ ተወካይ አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ የወያኔ መንግሥት አገሪቷን በማጥፋት በኩል እያደረገ ያለውን ደባ በማጋለጥ የተቃውሞ ኃይሎች በጋራ የሚደርጉት ትግልና እንቅስቃሴና ትልቅ ውጤት ሊያመጣ የሚችል መሆኑን በስፋት መግለጫ ሰጡ። በማከታተም የኢትዮጵያ አንድነት ግንባር በከፋኝ፣ በኢዲኃቅና በቤንሻንጉል ሕዝባዊ ንቅናቄ የተመሠረተ መሆኑንና ይኸው ግንባር ሠራዊት አቋቁሞ በሶስት ክፍላተ ሃገራት እንቅስቃሴ በማድረግ ላይ ያለ መሆኑን በቅርቡ ከቦታው ደርሰው የተመለሱት ሻለቃ ኢያሱ በስብሰባው ላይ ለተገኙ ወደ 200 ለሚሆኑ ኢትዮጵያውያን ገለጹ። በመጨረሻም ይኸው ስብሰባ "ይህንን እንቅስቃሴ ለማጎልበት ምን መደረግ አለበት" በሚለው ነጥብ በሰፊው ከተወያየ በኋላ ሠራዊቱን ሊያጠናክር የሚችል ዕርዳታ የሚያሰባስብ 10 አባላት ያሉበት ኮሚቴ ተቋቁሟል።

*"የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት አለ ወይም የለም ለማለት ቦታው ድረስ የምትፈልጉትን ሰው መርጣችሁ ለመላክ ከፈለጋችሁ አስፈላጊውን ሁሉ አሟልተን ቦታው ድረስ ለመውሰድ የምንችል መሆናችንን ለመግለፅ እወዳለሁ።" ከሻለቃ ኢያሱ ንግግር።*

## የሻለቃ ኢያሱ አያልቅበት ሙሉ መግለጫ

"ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት በአሁኑ ጊዜ በሶስት ክፍለ ሐገሮች በ4 የተለያዩ አካባቢዎች ውስጥ ተከፋፍሎ እየተንቀሳቀሰ ይገኛል። ይህ ሠራዊት በኢትዮጵያ ውስጥ ማለትም ወያኔ ከገባ በኋላ የተፈጠረ አዲስ እንቅስቃሴ ነው። አዲስ ነው ስንልም ከዚህ በፊት ያሉት ወይም የነበሩት የብሔር እንቅስቃሴዎች ያላቸውና አብዛኞዎቹ መገንጠልን የሚደግፉ ሲሆኑ አንዳንዶቹ እንደ ቤንሻንጉል፣ እንደ አፋር ሕዝብ እንቅስቃሴዎች ያሉት ደግሞ የራሳቸው የውስጥ መብት ተከብሮ የኢትዮጵያም አንድነት እንዲኖርና እንዲከበር የሚፈልጉ ናቸው። ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ግን መላው ኢትዮጵያን የሚመለከትና ለኢትዮጵያ አንድነት፣ ነፃነትና ክብር መስዋዕት ሆኖ መታገል የሚፈልግ ኃይል ነው።

"ይሄ ኃይል በሁለተኛ ደረጃ አገር አቀፍ ነው ማለትም ከአንድ ብሔር ወይም ከተወሰኑ ብሔሮች ብቻ የተወጣጣ ሳይሆን ሁሉንም የኢትዮጵያ ብሔሮች የሚያጠቃልል ነው።
ይህ ሠራዊት በአሁኑ ሰዓት በተወሰኑ ድርጅቶች የተቋቋመ ቢሆንም ወደፊት ግን እየሰፋ ይሄዳል። የዚህ ሠራዊት ኃይል ወሰን የለውም። ደግሞም እንደሌሎች እንደግንባር ወይም እንደ የብሔር ድርጅቶች በአንድ ቦታ ብቻ ተወስኖ የሚንቀሳቀስ ሳይሆን በየትም ቦታ በማንኛውም ቦታ ሄዶ ለኢትዮጵያ የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት በመክፈል የኢትዮጵያን ክብር ለመጠበቅ የሚችል ነው። ከዚህም በላይ ኃይሉን ከፍ የሚያደርገው መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ሊሳተፍበት የሚችልበት ሠራዊት መሆኑ ነው። በአሁኑ ጊዜ በወያኔ አገዛዝ፣ በወያኔ ኢትዮጵያን መድፈር፣ አንድነቷን ማናጋት፣ ህዝቧን ማበጣበጥ፣ በጐሳና በዘር መከፋፈል የተቆጩ ብዙ ኢትዮጵያውያን በመኖራቸውና በተጨማሪም በግል ኑሮአቸው ላይ ወያኔ አድልዎ እየፈጠረ አንተ ከዚህ፣ አንተ ከዚያ መጣህ በማለት የሚያጉላላቸውና የሚጨቁናቸው ብዙ ኢትዮጵያውያን አሉ። በእነዚህና በመሳሰሉት ምክንያቶች በአጠቃላይ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ በዚህ ሠራዊት ሊሳተፉና ሊደግፉት ስለሚችሉ ኃይሉ ከማንኛውም የተሻለና ከፍተኛ ነው።

"ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ሠራዊቱ በጠቀስኳቸው አካባቢዎች እየተንቀሳቀሰ አስፈላጊውን ዝግጅት እያደረገ ነው። በሕዝቡ ውስጥ በመንቀሳቀስም የጠላትን አቀማመጥና እንቅስቃሴ ያጠናል፣ በራሱ በኩልም መዋቅሩን ያስተካክላል፣

አባላትን ይመለምላል፣ ያሰለጥናል እናም ራሱን እያጠናከረ በቅርብ ጊዜ ደግሞ አስፈላጊ ሆኖ ሲያገኘው እንቅስቃሴዎችን አድርጐ በጠላት ላይ እርምጃ የሚወስድበት ቀን ሩቅ አይሆንም።

"ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ከከፋኝ፣ ከኢዲኃቅ፣ ከቤንሻንጉል ሕዝባዊ ንቅናቄ የተመሰረተ ቢሆንም የሠራዊቱ አባላት በእነዚህ ብቻ የተወሰነ አይደለም። የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት አባላት በድርጅት ወይም በቅንጅት ብቻ ሳይወሰን በማንኛውም ድርጅት መግባት የማይፈልጉ ነገር ግን በአገራችን ትግል ውስጥ ገብተን የሚያስፈልገውን መስዋዕትነት መክፈል እንፈልጋለን የሚሉ ግለሰቦችን ጭምር ያቀፈ ነው። ከእነዚህ ውስጥ የቀድሞ ሠራዊት አባላት፣ በተጨማሪ ደግሞ ከዩኒቨርስቲውና ከየትምህርት ቤቱ በወያኔ ግፍ እየተሰደዱ የወጡ ምሁራንና ተማሪዎች፣ የሕክምና ዶክተሮች፣ ሌሎች ምሁራኖች፣ የቀድሞ ሠራዊት አባል እስከ ኰሎኔል ድረስ አሉበት። ይሄ ትግሉን በአስተማማኝ መሰረት ላይ የተገነባ ያደርገዋል። እኔ እንዳየሁት የእነዚህ ታጋዮችና ሞራልና ስሜት ላየው ቀርቶ ለሰማውም በጣም የሚያኮራ ነው።

"የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ማነው? የማነው? የሚል ጥያቄ ቢነሣ መልሱ ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት የኢድኃቅ አይደለም፣ የቤንሻንጉል ወይም የከፋኝ ወይም የኢሕአፓ ወይም የኢዱፍ አይደለም ይህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት የኢትዮጵያ ሠራዊት ነው ይሆናል። ስለዚህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት የእናንተም የሁላችንም በመሆኑ ስለዚህ ሁላችንም መደገፍ ያስፈልገናል ማለት ነው።

"እንዴት የኢትዮጵያ ሠራዊት ሊሆን የሚችለው ለሚለው ደግሞ ይህን ያቋቋሙት ድርጅቶችና ቅንጅቶች ማንኛውም የኢትዮጵያ ድርጅት ወይም ግለሰብም ጭምር በአመራሩ ውስጥ፣ በህግና በሥነሥርዓት አወጣጡ ውስጥ በሁሉም ደረጃ እንዲሳተፍና ይህ ከአንድ ድርጅት ወይም ቅንጅት ብቻ ወጥቶ ለጠቅላላ ለኢትዮጵያ እንዲያገለግል ታስቦ የተዘጋጀ ነው። ይህም ያስፈለገበት ትልቅ ምክንያት እንደሚታወቀው በአንድ ሀገር ውስጥ ከአንድ የበለጠ ሠራዊት የለም ካለም የሚያመጣው ችግር በተለይ እንደ እኛ ላሉት ብዕር ይዘን መስማማት ለማንችል ሕዝቦች ጠመንጃና ጥይት ይዘን እንስማማለን ማለቱ ለእኛ ዘበት ይመስለናል። ሁለት የታጠቁ ኃይሎች አገራችን ነፃ ከወጣች በኋላ እንስማማለን ወይም አንድ ሠራዊት እንመሰርታለን የሚባለው በእኔ ግምትም ሆነ በሁላችንም የማይሆን መሆኑን ብዙ አስበንበትና ተነጋግረንበት እንዲያውም እንደ ቦስኒያ፣ ሱማሊያና ሩዋንዳ የመሰለ የማይበርድ የጦርነት ሁኔታን ሊያስከትል እንደሚችል በማሰብ ምንም እንኳን ወያኔን በአንድነት ብናጠፋም የዚህ አይነቱን ጉዳት ለሕዝቡ መዳረግ የለብንም በሚለው ደርሰናል። ስለዚህ ወያኔን ለመጣልና ኢትዮጵያን ደግሞ ክብሯን



አቶ ሙሉጌታ ኃይሉ

ነፃነቷንና አንድነቷን ደግሞም የሕዝብን እርጋታ ይዛ እንድትቀይ ከተፈለገ አንድ የጋራ ሠራዊት ማመስረትና ይህንንም ሠራዊት ሁላችንም መደገፍ፣ በሁሉም ነገር ማሳተፍ የኢትዮጵያዊነት ግዴታ ይሆናል።

"በአሁኑ ጊዜ ለአንድ ድርጅት ዝና ብቻ የሚለውን ትተን ትንሽ ላቅ ብለናል። እና የሌሎች ድርጅቶች አባል የሆናችሁና ያልሆናችሁም በዚህ ግንባር እንድትሳተፉና ፈቃደኛነታችሁን እንድታሳዩ፣ ይህ በዛ ይህ አነሰ በማለት ማስተካከያ ሀሳባችሁን እንድትሰነዝሩ እንጠይቃለን። ይህ ድርጅት የኢትዮጵያ ነው እስካልን ድረስ የሚጠቅመውን ነገር ሁሉ እንቀበላለን።

"እንዲሁም ማንኛውም ድርጅት ሠራዊት ያላችሁም ሆነ የሌላችሁ ድርጅቶች የምትፈልጉትን ሰው ከመጀመሪያው ጀምሮ ሠራዊቱ ውስጥ በማስገባት አብሮ እንዲሰለጥኑና በአንድነት በአንድ እዝ ስር እንዲዋቀሩ፣ እንዲታጠቁ፣ እንዲታገሉ ከተደረገ እርስ በእርሱ ፍቅር ያተርፋል ደግሞም ፍቅሩና ስሜቱ አብሮ ስለሚያድግ ትግሉ ለድርጅት ሳይሆን ለኢትዮጵያ ይሆናል ማለት ነው።

"ስለዚህ አገራችንን ከዚህ ውርደት፣ መከራና ውድቀት ለማዳን በተለይ እዚህ ያለው ሕዝብ ብዙ ተስፋ የሚጣልባችሁ ናችሁ። ብዙ ማድረግ ትችላላችሁና በእርግጥ የአገራችሁ ውርደትና ውድቀት የሚሰማችሁ ከሆነ ድጋፋችሁን በብዙ አይነት ማድረግ ይቻላል. ስለዚህ ከዚህ የኢትዮጵያ አንድነት ሠራዊት ድርጅት ጋር ተባብራችሁ የሚፈለገውን ድጋፍ እንድታደርጉ አሳስባለሁ። "

# ከጥቁር አሜሪካውያን የትግላችን ደጋፊዎች በአርያንቱ የቀረበ ጽሑፍ

ከላንዳፍታ ጥናት ክፍል

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት ቤኒቶ ሞሶሊኒ በኢትዮጵያ ሕዝቦች ላይ ግፍ ሲፈፅምና መርዝ (Mustard gas) በአውሮፕላን ሲያዘንብ የተናደዱ ጥቁር አሜሪካውያን በገንዘብ፣ በሞራልና ወደ ዘመቻ ዘምተው ለመዋጋት ያቀረቡት ፈቃደኝነት የሚዘነጋ አይደለም። በዚሁ በላንዳፍታ መጽሔት ከዚህ በፊት ታጋዩና ሊቁ የጥቁር ምሑር ዶክተር ጆንሰን ስለጥቁር ታሪክና ስለኢትዮጵያ ያስተማሩትን አንባቢዎች የረሳነው አይመስለንም። ዛሬም በየትምህርት ተቋሙ፣ በስብሰባዎችና በጋዜጦች የነቁ የጥቁር አሜሪካውያን ምሑራን የሚያደርጉት ትግል እጅግ የሚያስደስት ነው። እንደነዚህ ዓይነት ምሑራንን መቅረብና በትግላችን ማሳተፍ ከእያንዳንዱ ኢትዮጵያዊ ምሑርና ተማሪ የሚጠበቅ ነው። በአሜሪካ በዩኒቨርስቲው ስለጥቁር ሕዝቦች ጥናት የሚያደርግ ኢትዮጵያዊ ፕሮፌሰርና ተማሪ ለጥቁር ምሑራን የሀገራችንን ሁኔታ በማስረዳትና ጥናቱም ውስጥ እንደ አመቺነቱ ለማዋቀር ያላሰለሰ ጥረት ማድረግ አለበት። እስራኤላውያን ለ1948ቱ ድል የበቁት አንዱ ምክንያት ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞችን፣ የጥናት ማዕከሎችንና የአሜሪካ የፊልም መዲናን (Holywood) በመጠቀም ነው። ትግላችን በሁሉም መስክ መስረግ አለበት። ሌላው ቀርቶ በወንጂ ስኳር የፕላስቲክ ከረጢት መሰል ማስታወቂያ ላይ ሁሉ ከተቻለ መውጣት አለበት። በግርግዳችን ላይ መፃፍ አለበት። በመኪናችን ላይም መለጠፍ አለበት። በቀን መቁጠሪያ ማስታወሻዎች፣ በፊልሞች፣ በፖስተሮች፣ በማስታወቂያዎች፣ በልብሳችን፣ በወጥ ቤት ዕቃዎች፣ በግሮሠሪዎችና በሌሎችም መገልገያዎች እንደአመቺነቱ ክብሩን ጠብቆ (Dignity) መታየት አለበት። እስካሁን ለወያኔ አስደንጋጭ የሆነበት (Nightmare) ይህ በምዕራቡ ዓለም የተከሰተውና በምሑሮቻችን ጥረት ጉልቶ የሚታየው ኢትዮጵያዊነት ነው። ይህን በፍፁም ወያኔ ሊቋቋመው አልቻለም። ወያኔ በብልህነቱና በጉሪጥ አመለካከቱ የምዕራቡን ኢትዮጵያዊ ምሑር ካልያዘ ምንም እንደማያዛልቀው ያውቀዋል። ጊዜ ይውሰድ እንጂ ማንኛውም እንቅስቃሴ በምሑሩ እንደሚመራ ይረዳል። የአሜሪካ መንግሥትም በተራቀቀ መንገድ ነገሩን አግኝቶታል። «በምዕራብ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ጠንካራ አይደሉም» የሚለው ፕሮፓጋንዳ እንዲያው ለይስሙላ የሚረጭ ውዥንብር ነው። ብዙ ማድረግ እየቻልን የሚገባንን አላደረግንም ከሚል እንጂ በደረሰው ተቃውሞ ወያኔም ሆነ የምዕራቡ ደጋፊዎቹ እጅግ ደንግጠዋል። ፕሮፓጋንዳቸው በምዕራቡ ምሁር ላይ ያተኮረውም ለዚህ ነው። ብቻ ጥሩ እየሠራን ነው ብለን እንዳንዝናና፤ ገና ብዙ መንገድ ይቀረናል።

ወያኔም አንዳንድ የአሜሪካ ጥቁር ምሑራንን በመቅረብ ያደረገው ጥረት እጅግ የሚያስደንቅ ነው። አንዳንዴ የጠላትንም ስልት ማድነቅ ያስፈልጋል። ሌላው ቀርቶ የአክሱም ሐውልት ያለበት የጣት የወርቅ ቀለበት ለጥቁር አሜሪካ ደጋፊዎቹ ሸልሟል።

እሪ በከንቱ በምናየው የጥቁር ወጣት ወንጀለኝነት ሳናዝን (ይህም ሁኔታ የራሱ የሆነ ምክንያት አለውና)፤ ተስፋችን ሳይጨልምና በኢትዮጵያዊነታችን የተለየ የአመለካከት ሁኔታን ሳናሳይ ከጥቁር ወንድሞቻችንና እህቶቻችን እጅ ለእጅ ተያይዘን ለአርነት፣ ለነፃነት፣ ለሰው ልጆች መብት መከበር፣ ዘረኝነትንና ናዚ ቀመስ የጐሳ ማፅዳትን (Ethnic Cleansing) አጥብቀን እንታገል። የጎሳ ፋሽዝምን በሀገራችንም ሆነ በዓለም አቀፍ ደረጃ እንፋለም። ኢቶጲስ የሚለው ቃል ራሱ ጥቁር ማለት ነው። በርካታ ሊቃውንት የጥቁር ዘርና የሰው ልጅ ኢትዮጵያ እንደበቀለ ይናገራሉ። ለዚህም በርካታ መረጃዎችን ያቀርባሉ። የነሉሲና የሌሎችም የጥንት ሰው መሰል እንስሳት አፅም የተገኙት ከኢትዮጵያችን ነው። እነዚህም አስትሮሎፒቲከስ አፋሬንሲስ (Austrolopeticus afarensis) እና አስትሮሎፒቲከስ ራሚዲስ (Austrolopeticus ramidis) የተባሉት የተገኙት ከእኛው ነው። እስካሁን ከነጭ ሀገር ወደ 4 ሚሊዮን ዓመት የሚጠጋ አፅም አልተገኘም። ነጪም ራሱ የዘረኝነት ኃጢአቱ ስለሚያቃጥለው እንደዚሁም ለገንዘብና ለዝና የአፅም ቁፈራውን ተግባር ስራዬ ብሎ ስለያዘው ችካሉንና ድንኳኑን ይዞ እንዳበደ ውሻ በየስርጡና በየሸለቆው እየባዘነ ነው። ስለጥቁር መጥፎነት በፃፈበት የምርምር ብዕሩ ዛሬ ደግሞ «የሰው ልጆች መፍለቂያ» እያለ ኢትዮጵያንም ሆነ ሌሎች ጐረቤት ሐገሮችን አንዳንዴ መካሱ አልቀረም። የሳይንስ ብርኃንና የእርሱ የበላይነት ስለቱምታታበት ዕውነቱን ለማግኘት ጊንጥና እባብ ሳይፈራ በአዋሽ በረሃ፣ በስምጥ ሸለቆ ሐይቆች አካባቢ፣ በቱርካና ኃይቅ ስርጦች በሰራው ሥራ ሳያፍር አፅም እየቆፈረ ነው።

የጭለማ አህጉር (Dark continent) ባለበት አፉ ለመብራት የሚሆን አብሪ እሳት (Discovery of fire) የተፈጠረው በነዚሁ በነሉሲ ድንጋይ

በማጋጨት ዘዴ ነው በማለት የእርሱን ውርጩና በረዶው አጥንትን የሚቦረቡር ሀገር በወጣትነቱ በማጋለጥ የስልጣኔውን በኩርነት ሳይወድ በግድ ለአፍሪቃ ለመስጠት የተገደደ ይመስላል። ደፍጣጣ የጥቁር አፍንጫ በሞቃት አየርና በአፍሪቃ አቧራ መስፋቱንና የእርሱ የሰለለ አፍንጫና ቀለም ከበረዶ ቀጭን የአየር አተነፋፈስ ጋር መያያዙንም የዘገበ ይመስላል። ለዚህም እንግሊዛዊ ኬንያዊው አፅም ቆፋሪ ፕሮፌሰር ሊኪ (Leaky) የተሻለ መልስ ሳይኖራቸው አይቀርም ተብሎ ተገምቷል።

የሆኖ ሆኖ ወደ አሜሪካ የጥቁር ምሑራን ድጋፍ እንመለስ። በርካታ የጥቁር አሜሪካውያን ምሑራን ኢትዮጵያን ያከብራሉ። ዘረኝነትን ጐሰኝነትን አይደግፉም። የሚረጨው ፕሮፓጋንዳም ብዙዎቹን ከእውነተኛ ምርምራቸው ፍንክች አላደረገም። የፕሮፓጋንዳ ነገር ከተነሳ አንድ ነገር ግልፅ ይሁን። ኤርትራ ያንን የውሸት «ሪፈረንደም» «ስታገኝ» በርካታ ኤርትራዊ ነኝ ባዮች ጥቁሩን አታለውታል። ብዙ ‹‹ኤርትራውያን›› ኢትዮጵያውያን ባርያ ይሸጡ ነበር፤ እኛም በባርነት በርካታ ዘመን ኖረናል፤ ነገር ግን በእናንተ ዕርዳታ ነፃ ወጣን በማለት በየስብሰባው ጥቁር አሜሪካውያንን ብሶታቸውን በመስረቅ አስለቅሰዋል። በእርግጥ የባሪያ ንግድ ባልሰለጠነው ዘመን እንደማንኛውም ሀገር በአንድ ታሪካዊ ወቅት በኢትዮጵያ ቢከሰትም ኢትዮጵያውያንን ለማስጠላት የዚህ ዓይነቱን ፕሮፓጋንዳ መጠቀም እጅግ የሚያሳዝን ነው። እንዲያውም «ኢትዮጵያዊ ነን ባዮች ትግሬዎችንና ኤርትራውያንን የሚቃወሙት በባርነት እንኖርም ስላሉ ነው» እያሉ የሚያወናብዱ የወያኔና የሻቢያ አባሎች በየእስቴቱ ይገኛሉ። በእርግጥ ወደ አሜሪካ የመጣ ኢትዮጵያዊ ነኝ ባይ ባሪያ ይሸጣልን? ይህ እጅግ የሚገርምና የሚያሳዝን ከማንኛውም ዜጋ የማይጠበቅ ቅጥፈት ነው።

የአሜሪካ ጥቁር ሕዝቦች ትግል ከአፍሪቃ ሕዝቦች ጋር የተቆራኘ ነው። በአደዋና በማይጨው ጦርነቶች ለጥቁር ሕዝብ (የአርበኞቻችንን ነፍስ ይማርና) ኢትዮጵያ የሚያስመካ ሚና ተጫውታለች። የበርካታ የአሜሪካን ጥቁር ሕዝቦችንም ድጋፍ አግኝታለች።

በቅርቡ በሚዙሪ የታወቁት ጥቁር ፕሮፌሰር ጂኒ ዋሽንግተን በፓልም ቢች ጋዜጣ (Palm Beach Gazette, 11/28/96) የተሰማቸውን ብሶት ለጥቁሮች የኮንግሬስ አባላት በሚከተለው ሁኔታ ገልፀዋል።

**ፕሮፌሰር ጅኒ ዋሽንግተን ለጥቁር የኮንግሬስ ሸማግሌዎች ኢትዮጵያ ውስጥ ስለሚደረገው ጭቆና መግለጫዊ ጽሁፍ አወጡ።**
**(Palm Beach Gazette, 11/28/96)**

ለተከበሩ ዶናልድ ፔይን፣ ሊቀመንበር
የጥቁር ኮንግሬስ አባላት «ውክለ ጉባኤ»
(caucus)

ውድ ተወካይ ፔይን፦

ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝቦች በቅኝ አገዛዝ ተዋረዳዊ ስልት፣ በፖለቲካው ጉጠኝነት፣ በእርስ በእርስ የጐሳ ቅራኔና እንደዚሁም ማንነታቸው ጠፍቶና ባሕላቸው ተንቆ በባሕላዊ የጭቆና ቀንበር ተጠምደው ይገኛሉ። የአሁኑ የኢትዮጵያ መንግሥት ማለትም የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት ከዚህ በፊት ኢትዮጵያን የወረረውን የቅኝ አገዛዝ ወኪል የቤኒቶ ሞሶሎኒን የፖለቲካ ፖሊሲ በማራመድና በመቀበል የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ኃይልንና ማስፈራራትን በመጠቀም ኢትዮጵያዊ ፊደሎችን በላቲን ተክቷል። ላቲን በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍሎች በጭፍን ጉልበት በሥራ ላይ ውሏል። በደቡብ ምዕራብ ኢትዮጵያ የሚኖሩ ሕፃን ዜጐች በራሳቸው ፊደል ትምህርታቸውን ሊያገኙ አልቻሉም፤ ይህም ፊደል የጥቁር የስልጣኔ ምንጭ እንደሆነ ይታወቃል። በዚህም ግብሩ የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት የጥቁሮችን የስልጣኔ ታሪክ እያንቋሸሸው እያሳደፈውና እየመታው ነው። የኢትዮጵያ ሕዝቦች ታሪክና የስልጣኔ ግስጋሴ ከፊደላቸው ጋር የተያያዘ ነው።

የኢትዮጵያ ፊደል የጥቁር ሕዝቦች የሥልጣኔ ናምራና ምልክት በመሆኑ ይህንን ታሪካችንን ከጉጂ አደጋ ለመከላከልና ለመመከት አፍሪቃዊ አሜሪካውያንና በየትኛውም ዓለም የሚገኙ ነፃነት አፍቃሪ ሕዝቦች ገንቢና ተገቢውን አስተዋጽኦ የማድረግ ተገቢና አስፈላጊ ድርሻ አለባቸው። ለዚህም ግብ ይረዳ ዘንድ በአሜሪካ በርካታ ግለሰቦችና ድርጅቶች ፊለጋችንን በመከተልና የሞራል ድጋፍም ለአቋማችን በመስጠት የአሜሪካ መንግሥት የራሱን ድጋፍ ለትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት እንዳይሰጥ እንደዚሁም ላቲን በኢትዮጵያ በጭፍን ኃይል ግብር ላይ እንዳይውል የተቻላቸውን ሁሉ አድርገዋል።

ለዚህም ሞራላዊ ድጋፍ በምሣሌያዊነት ይጠቀስ ዘንድ በኦክቶበር 17 እና 18, 1996 የተዘገበው «ከትግል የተወለደ ፍልስፍና» በሚለው ሳልሳዊ ኮንፈረንስ፣ በሮክላንድ ኮሚኒቲ

ኮሌጅ–ሰፈርን (ኒውዮርክ) ተወካዮች የፈረሙበትን ሰነድ እንደአባሪ አድርጌ አቀርባለሁ። ከደጋፊ ተቋሞችም መካከል የአሌይን ሎክ የፈላስፋዎች ስብስብ፣ የአሜሪካን ተመራማሪዎች የሊቃውንት ጉባዔ እና ሌሎችም ይገኙባቸዋል። ሰነዱን ከፈረሙት ግለሰቦችም ውስጥ የሚከተሉት ይገኙባቸዋል።
– ፕሮፌሰር ጁዲዝ ግሪን (ፎርዳም ዩኒቨርስቲ፣ ኒውዮርክ)
– ብላንሽ ራድፎርድ ከሪ (ፌየትቪል ዩኒ ቨርስቲ፣ ኖርዝ ካሮላይና)
– ቶሚ ላት (ሚዙሪ ዩኒቨርስቲ–UMSL፣ ሴንትሊዊስ)
– ኤስሚ ብሐን (ጆርጅታውን ዩኒቨርስቲ፣ ዋሽንግተን ዲሲ)
– ስቴፈን ቶምሰን (ሐዋርድ ዩኒቨርስቲ፣ ዋሽንግተን ዲሲ)
– ጄ. ኢቬሬት ግሪን የኮንፈረንሱ ሊቀመንበር (ሮክላንድ ኮሚኒቲ ኮሌጅ፣ ኒውዮርክ)።

በተጠቀሱት ፈራሚዎች ውክልናና ስም ለኮንግሬስ አባላት የጥቁር ውክለ ጉባኤ (caucus) የማመለከተው ጉዳይ ይህንን ማመልከቻችንን በመመርመር ርዕሰ ብሔር ክሊንተን ቲፒኤልኤፍ (የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት)፣ ላቲንን በደቡብ ኢትዮጵያ ክፍሎች በጉልበት ሥራ ላይ እንዳያውል ድጋፋቸውን እንዳይሰጡ ነው። አንዱ መፍትሔ ሊሆን ይችላል ብለን ያመንበት ዘዴ የአሜሪካ መንግሥት ዲፕሎማሲያዊና የገንዘብ ድጋፍን እንዲያግድ (እንዲያቆም) ማድረግ ነው።

ይህንን በሚመለከት ጥያቄ ካለዎት በሚቀጥለው አድራሻ እንዲያስታውቁኝ በአክብሮት እጠይቃለሁ።

ጆኒ ዋሽንግተን ፡ ፒኤችዲ
የፍልስፍና ጠበብት (ፕሮፌሰር)

የአፍሪቃዊ–አሜሪካኖች ጥናትና ምርምር ፕሮፌሰርና ሥራ አስኪያጅ፣ የአሜሪካ ጥናት ክፍል፣ ሳውዝ ዌስተርን ሚዙሪ ስቴት ዩኒቨርስቲ፣ ስፕሪንግ ፊልድ፣ ሚዙሪ።

<u>ላቲንን በኢትዮጵያ አንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በጉልበት (በኃይል) ሥራ ላይ ለማዋል በሚካሄደው ፖሊሲ በተቃውሞነት የቀረበ የፊርማ ሰነድ። (PETITION)</u>

ለዘመናት ኢትዮጵያ ለአፍሪቃውያን ሥልጣኔ በአርአያዊ የምሳሌ ብርኃንነት ስታበራ ቆይታለች። አሁን ባለንበት ምዕተ–ዓመት (መቶኛ ዓመት) ዋዜማም ኢትዮጵያ ለአፍሪቃዊ ሀገር ወዳድነት የማሰባሰቢያ የነፃነት መድረክ በመሆን ብርኃን አብርታለች፤ ከዚያም በኋላ ለተባበሩት የአፍሪቃ ድርጅትና ለፀረ–ቅኝ ግዛት እንቅስቃሴ እንደዚሁም በመላው ዓለም ለሚገኙ ጥቁር ሕዝቦች መመኪያ ሆና የነፃነትን ችቦ ለኩሳለች። ከጣልያን ወረራ በፊት ኢትዮጵያ የሕዝቦቿን አንድነትና የብሔረሰቦችን ውሑዳዊ ተሳትፎ ጠብቃ ኖራለች።

ዛሬ የአንድነት ተሳትፎ ወይም የጋራ ሐገርነት በትግሬ ነፃ አውጪ መንግሥትና በተዋቀረው የፖለቲካ ድርጅቱ ኢሕአድግ ፖሊሲ የተነሳ በኃይልና በሽብር አደጋ ላይ ወድቋል። ዛሬ የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ኢትዮጵያውያኖችን ከመጉዳትም አልፎ የባሕላቸውን ሕይወት ለመግደል በመጣር ላይ ነው። ኢትዮጵያ ላይ የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት የፈፀመውን በደልና ግፍ ለማተት የዚህ ወረቀት ቦታ አይበቃንም፤ ዝርዝሩ ብዙ ነው። ከዚህ ሁሉ ትልቁ ግፍ የትግራይ ነፃ አውጪ ድርጅት ኢትዮጵያውያን የራሳቸውን ሀገር–በቀል ፊደልና ቋንቋ እንዲጠሉ በማድረግ ላቲንን እንዲቀበሉ እያደረገ ነው። ይህም የላቲን የአውሮጳውያን የአፃፃፍ ዓይነት በደቡብ ምዕራብ የኢትዮጵያ ክፍሎች በአንደኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የነዋሪውን ሕዝብ ፊደል በመተካት ላይ ይገኛል።

በእርግጠኝነት ለማሳሰብ የምንፈልገው የላቲን ፊደል ከጥቁር ሕዝቦች የኪነት ባሕልና ታሪክ እንዳልመጣ ነው።

ስለሆነም፣ ላቲንን በጥቁር ሕዝቦች ላይ በጉልበት ለመጫን የሚካሄደው ድርጊት ኢትዮጵያ በእጅ አዙር ቅኝ አገዛዝ ስር መኖሯን ስለሚያረጋግጥ፤

ስለሆነም፣ የላቲን በጉልበት በሕዝብ ላይ መጫን የኢትዮጵያን ቀና የስልጣኔ ግስጋሴ ስለሚያጉድፈው ወይም ስለሚያበላሸው፤

ስለሆነም፣ ለዚህ የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት የከፋፋይ ፖሊሲ ትምህርት የአሜሪካ መንግሥት $80 ሚሊዮን ብር ለመስጠቱ ማስረጃዎች ስለሚያረጋግጡ፤

ስለሆነም፣ ምዕራባውያን ባይደግፉትም የትግሬ ነፃ አውጪ ድርጅት የቅኝ አገዛዝን ስልትና ዘዴ ማስፋፋቱ ስለማይቀር፤

ለዚህም የፊርማ ሰነዳችን ተገቢ ይሆን ዘንድ ዕምነታችንን አስተሳሰባችንን በመግለፅ፤ የአሜሪካ መንግሥት ከላይ በተጠቀሱት ችግሮች(ጉዳዮች) ላይ እንዲያስብና የበለጠ ዕውቀትም እንዲያገኝ፣ ከዚያም አልፎ የኢትዮጵያ ሕዝቦች መብታቸውና ክብራቸው እንደማንኛውም ሕዝብ ተጠብቆ በነፃነት እንዲኖሩ የተቻለውን ሁሉ እንዲያደርግ እንጠይቃለን።

## John Washington writes to Black Caucus about Ethiopian suppression

**Honorable Donald M. Payne -- Chair, Congressional Black Caucus**

**Dear Representative Payne:**

The people of Ethiopia today are subjected to the legacy of colonialism, including political tribalism, interethnic conflict, identity crisis and cultural suppression. The current regime of Ethiopia, The Tigre Peoples' Liberation Front (TPLF), is reviving the political policies of the former colonial invader of Ethiopia, of whom Mussolini was representative. In adopting such neo-colonial policies, the TPLF through the use of intimidation and force has replaced the Ethiopian script with Latin language. Latin is imposed in elementary schools of southwestern Ethiopia. The children of southwestern Ethiopia are not allowed to obtain education through the use of their own alphabet, on which the Black civilization is based. In this regard, the TPLF's action is undermining the heritage of Black civilization. The Ethiopians' history as well as their destiny is connected to the Ethiopian script.

In view of the fact that the Ethiopian alphabet is the symbol of the civilization of Black people, it is fitting and proper for African-Americans and, indeed, all freedom-loving people to play a constructive role in protecting and preserving this heritage that is now being threatened. To this end, already a number of individuals and organizations in the United States are expressing moral support in our effort to urge the U.S. government to dissuade the TPLF in imposing Latin in Ethiopia.

As a sample of this moral support, I am herewith forwarding to you a petition ... which includes singatures of some of the participants of the Oct. 17-18, 1996 *Philosophy Born of Struggle III* conference that convened at Rockland Community College, Suferen, New York. Among the sponsors of the conference were the Alain Locke Society, The American Council of Learned Society, and others. Some of the signatories to the petition are: Professors Judith Mary Green, Fordham University, NY; Blanche Radford Curry, Fayetteville State University, NC; Tommy Lott, University of Missouri at St. Louis, MO; Esme Bhan, Georgetown University, District of Columbia; Stephen Thompson, Howard University, District of of Columbia; and J. Everett Green, Rockland Community College, NY, Chairperson of the conference.

On Behalf of the signatories, I request the Congressional Black Caucus present the concerns here raised to President Bill Clinton, so that he may dissuade the TPLF to discontinue imposing Latin in south-western Ethiopia. A possible approach to this problem is to urge the U.S. government to withdraw its' diplomatic and finanical support of the TPLF regime. If you have any questions regarding this matter, please let me know.

**- Johnny Washington, Ph.D.**

*Professor of Philosophy, Professor of African-American Studies and director of African-American Studies Program, Southwestern Missouri State University, Springfield, Missouri*

***

### Petition of Discontinue the Imposition of Latin in Ethiopian Elementary Schools

Since time immemorial, Ethiopia has stood as a symbol of splendor of African civilization. At the turn of the century, Ethiopia served as unifying symbol for Pan Africanism, subsequently the Organization of African Unity, the various decolonizing movements on the continent of Africa, and freedom movements in the African Diaspora. Until the Italian invasion, Ethiopia had preserved ethnic pluralism and unity. Today that symbol of unity is being treatened by Ethiopia's existing political regime, the Tigre People's Liberation Front (TPLF), which rules under the auspices of Ethiopian People's Revolutionary Democratic Front with force and terror. The TPLF now harms the Ethiopians and undermines their cultural survival. Space does not permit us here to enumerate all of the problems the TPLF are causing Ethiopia. One stands out:: The TPLF is forcing Ethiopians to reject their indigenous Ethiopic alphabet (i.e, languages) and adopt latin alphabet, a European language, which has replaced the Ethiopian script in elementary schools in southwestern Ethiopia. Ofcourse, the Latin alphabet is not part of the heritage of Black people.

Whereas, the imposition of Latin on the entire Black population reaffirms that Ethiopia is under an indirect colonial rule,

Whereas, evidence indicates that the U.S. government has provided the TPLF with over $80 million in its divisive educational programs; and,

Whereas, despite the western government's persistent support of the TPLF regime, it is reoccupied with perpetuating colonialism; thus,

Be it resolved that the U.S. government develop a greater awareness of the problems described above, and take actions forthwith to resolve them, so that the Ethiopian people can enjoy human rights, dignity, freedom.

**(Palm Beach Gazette 11/28/96 Page 3A)**




በኢትዮጵያ ጎንጎና ፊደል

መፅሔት፣ መፅሀፍና ልዩ ልዩ ሰነዶችን፤
ስፕሬድሽቶች፤
ዴታቤዝ፤
ንግግር ማቅረቢያ ዝግጅት፤
ኤሌክትሮኒክ መልከት፤
ዌብ ገፅ፤
ልዩ ልዩ ስእላዊ ፊደላትና የመሳሰሉትን
ከታወቁ ሶፍትዌሮች ጋር ለማዘጋጀት
የሚያስችል ሲስተም።

## EthiO Systems

PO Box 36921
Houston, TX 77236
**(713)995-4360**
ethiosys@neosoft.com
http://www.neosoft.com/~ethiosys/ethiosys.html

ዋሽራ 2.0
በነዚህ መደብሮች ይገኛል

**Maru Grocery**
Houston, TX (713)665-6608
Dallas, TX (214)373-6278

**Ethio Sound**
Washington, DC (202)232-0076

**Addisu Gebeya**
Washington, DC (202)986-6013

**Queen of Sheeba**
Fallis Church, VA (703)998-0180

**Supported Software**

Word Processing: MS Word, WordPerfect, WordPro, AmiPro, ...

Spreadsheets: Lotus 1-2-3, MS Excel, Quattro Pro, ...

Database: MS Access, Lotus Approach, ...

Publishing: PageMaker, QuarkXPress, Corel Ventura, ...

Illustration: CorelDRAW, Adobe Photoshop, Photoworks, ...

Internet: Eudora, Internet Explorer, Netscape Navigator, ...

Windows 3.1x and Windows 95 resident programs

# ማሩ ግሮሰሪ Maru Grocery

## ቅመማ ቅመሞች፣ ጥራ ጥሬዎች፣ የጤፍ ዱቄት፣ እንዲሁም እንጀራ፣...

**በUPS (United Parcel Service) ለመላክ ዝግጁ ነን።**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| የገብስ ዱቄት | 1.29/lb | የሀረር ቡና ጥሬ | 5.49/lb | የቂቤ ማንጠሪያ | 1.00/OZ |
| ሱፍ | 2.99/lb | የሲዳሞ ቡና ጥሬ | 5.49/lb | መከለሻ | 1.00/OZ |
| ጤፍ | 1.89/lb | ቡላ | 9.99/lb | ኮረሪማ ድፍን | 1.50/OZ |
| ተልባ | 1.99/lb | ብቅል | 1.99/lb | በሶብላ | 1.75/OZ |
| ቅንጨ | 0.99/lb | የባቄላ ዱቄት | 4.99/lb | ኮሰረት | 1.75/OZ |
| አተር ክክ | 0.99/lb | ባቄላ | 0.99/lb | እርድ | 1.29/OZ |
| ሽምብራ ክክ | 0.99/lb | የሽምብራ ዱቄት | 2.99/lb | ኮረሪማ የተፈጨ | 1.75/OZ |
| ምስር ክክ | 0.99/lb | በሶ | 4.99/lb | ጤና አዳም ፍሬ | 1.75/OZ |
| ሽንብራ | 0.99/lb | ጦስኝ | 1.75/OZ | ጥቁር አዝሙድ | 0.89/OZ |
| አብሽ ድፍን | 2.99/lb | ሰናፍጭ | 1.75/OZ | የሻሂ ቅመም | 1.29/OZ |
| አብሽ የተፈጨ | 5.99/lb | ስልጆ | 4.99/lb | ጥቁር ቅመም | 1.75/OZ |
| የገንፎ ዱቄት | 4.99/lb | ቅሩንፉድ | 0.69/OZ | ነጭ ቅመም | 1.75/OZ |
| እጥሚት | 4.99/lb | ዝንጅብል የተፈጨ | 0.50/OZ | ቀረፋ | 0.99/OZ |
| አልበት | 4.99/lb | ነጭ ሽንኩርት የተፈጨ | 0.50/OZ | ነጭ አዝሙድ | 0.79/OZ |
| ጌሾ ለጠጅ | 7.99/lb | በርበሬ | 6.49/lb | እንጀራ (15pc/pk) | 5.00/pk |
| ጌሾ ለጠላ | 7.99/lb | ሚጥሚጣ | 7.99/lb | ጤፍ 25 ፓውንድ | 37.25/bag |
| ጌሾ ደቃቅ ለጠላ | 6.99/lb | ያዋዜ በርበሬ | 6.29/lb | | |
| እሻሮ የገብስ | 1.99/lb | ምጥን ሽሮ | 4.99/lb | | |

**8353 Park Ln Dallas, TX 75231**
**(214)373-6278**
**6065 Bissonnet, Houston, TX 77081**
**(713)665-6662 (713)665-6608**

## ከትዝታና ከታሪክ ማህደር

# ጣጣቴ ገዳይ
## (አውቶማቲክ ካላሺንኮቭ 1947)

(ከሠይፉ መኩሪያ)

በአንድ ሴኮንድ አስር ዙር ጥይቶችን መተኮስ የሚችለውና በታጋዮች ዓለም ውስጥ የእምቢተኝነት ምልክት ለመሆን የበቃው ካላሺንኮቭ መትረየስ በሥራ (ግድያ) ላይ ከዋለ እነሆ 50 ዓመት ሲሆን፣ በመትረየሱ ብቃትና ተወዳጅነት ኩራት የሚሰማው የራሽያ ጦር ኃይል ይህንን የልደት በዓል ባለፈው ወር በታላቅ ድምቀት ያከበረው የመትረየሱን ፈልሳፊ ሜጀር ጀኔራል ሚካኤል ቲ ካላሺንኮቭን ኮከብ እንግዳ በማድረግ ነበር።

ሠባ ዓመት ዕድሜ ያላቸው ሜ. ጀነራል ካላሽንኮቭ በመሣሪያ ፈልሳፊነታቸው ሶስት «አርደር አፍ ሌኒን» የተሰኘውን ታላቅ የሶቭየቶች ሽልማት ያገኙ ሲሆን፣ ቀዝቃዛው ጦርነት ካከተመ በኋላም «ለእናት አገር ግልጋሎት» የሚሰጠውን የክብር ኒሻን ከፕሬዚዳንት ቦሪስ የልስቲን መንግሥት የተሸለሙና በአሁኑ ሰዓት ጡረታ ላይ የሚገኙ አዛውንት ናቸው። በቅርቡ በወጣው የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ላይ መትረየሱን በሁለት እጃቸው ጨብጠው ከሙሉ ፈገግታ ጋር የሚታዩት ካላሽንኮቭ «ገና በልጅነቴ ሽጉጥ ፈትቼ መግጠም እንደቻልኩ ቀሪው ህይወቴ ከመሣሪያዎች ጋር እንደሚያያዝ ተሰምቶኝ ነበር» በማለት ፈጠራቸው ያስገኘላቸውን ዝና በኩራት ይገልጣሉ። የጀነራሉ የፈጠራ ሥራ እርሳቸውን ብቻ ሳይሆን በመላ ራሽያ ውስጥ ብሔራዊ ኩራትን የፈነጠቀ በመሆኑ የ50ኛው የልደት በዓል ሲከበር ክራዝናያ-ዝቬዳ የተባለው የጦር ኃይሎች ጋዜጣ «መልካም ልደት ይሁንልህ-ካላሽንኮቭ!» የሚል አርእስት ይዞ በመውጣት በዓሉን አድምቆታል።

ካላሽንኮቭ በእርግጥ የሚገርም መሣሪያ ነው። ለብዙ ወራቶች ከተቀበረበት የጭቃ ወይም የአሸዋ ጉድጓድ ውስጥ ወጥቶ ያለአንዳች እንከን ጥይቶቹን ማንጣጣት የሚችልና በልዩ ልዩ የአየር ጠባዮችና መልክአ ምድሮች የተፈተነ ብቁና አጥጋቢ መትረየስ ነው። በአንድ ሴኮንድ አሥር ዙር መተኮስ የሚችለውና 30 ዙር ማጋዚን መታጠቅ የሚችለው ይህ መትረየስ ክብደቱ ከ3 ኪሎ በላይ የማይመዝን በመሆኑ ተዋጊዎችን (ተኳሾችን) በክብደት የማይጫን አመቺ (ዩዘር ፍሬንድሊ) የሆነ መሣሪያ ነው።

እስከዛሬ ድረስ ወደ 70 ሚሊዮን የሚሆኑ ካላሽንኮቭ መትረየሶች በሥራ ላይ መዋላቸውን የገለጠው የኒውዮርክ ታይምስ ጋዜጣ ይህ መሣሪያ ለ55 አገር የወታደሮች ቋሚ ትጥቅ በመሆን ግልጋሎት እንደሚሰጥም ጠቅሷል። ካላሽንኮቭ በዚህ ግልጋሎቱ ዝናን ያተረፈ መሣሪያ ቢሆንም በይበልጥ የሚታወቀው የእምቢተኝነት አርማ (Symbol of rebelion) በመሆኑ ነው። ብዙ የትጥቅ ታጋዮች የመትረየሱን ምስል በማህተማቸውና በባንዲራቸው ላይ መቅረፃቸው የእምቢተኝነት ጠባያቸውን ለመግለፅ ሲሆን ከተራ ታጋይነት ተምዘግዝጎ ወደ ስልጣን ርካብ ላይ መውጣት የቻለው የሞዛምቢክ መንግሥትም የካላሺንኮቭን ምስል የአገሪቱ ሰንደቅ ዓላማ ላይ ቀርፆ አስቀምጦታል። በአገራችንም ውስጥ በስልጣን ላይ የሚገኙት የሻቢያና የወያኔ ድርጅቶችም መትረየሱን ዓርማቸው ላይ ያስቀረፁት ከዚሁ ጋር የሚገናኝ የእምቢተኝነት ምልክት ነው።

በሞስኮ ከተማ ውስጥ በሚገኘው የጦር ኃይሎች ሙዚየም ውስጥ ለትርዒት የቀረበው ካላሽንኮቭ መትረየስ የራሱ ታሪክ አለው። ኒኮላይ ካርፓቭ የተባለው የሙዚየሙ ኃላፊ «በተቻለ መጠን በተፋፋመ ውጊያ ላይ ያገለገሉ መሣሪያዎችን ለማቅረብ እንሞክራለን» ብሎ እንደገለፀው በሙዚየሙ ውስጥ አንድ የቬትናም ሽምቅ ተዋጊ 78 አሜሪካኖችን ባንዴ ያጨደበት የካላሽንኮቭ መትረየስ ቀርቧል። የሽምቅ ተዋጊው በዚህ ጀብድ «የሶሻሊስት ሪፐብሊክ ቬትናም ጀግና›› (Hero) የተሰኘ ክብር እንደተሰጠው ከመትረየሱ ጋር የቀረበው ገለጣ ያስረዳል።

ሜ.ጀነራል ካላሽንኮቭ ገና በወጣትነት ዕድሜያቸው መሣሪያዎችን መፍታትና መገጣጠም ብቻ ሳይሆን ጠለቅ ያለ ጥናት ያካሂዱ እንደነበር ይናገራሉ። ዝና ያስገኘላቸውን መትረየስ ከመፈልሰፋቸው በፊት ሽጉጦችን በራሳቸው እየሰሩ ለራሳቸውና ለቅርብ ጓደኞቻቸው ይሰጡ ነበር። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ላይ የታንክ አዛዥ ሆነው ሲያገለግሉ በመቁሰላቸው ህክምና ሲደረግላቸው ከቆየ በኋላ ወደነበሩበት ጋንታ ሲመለሱ ጓደኞቻቸው በሙሉ በጀርመን ወታደሮች መገደላቸውና የተገደሉበትም መሣሪያ አውቶማቲኮች እንደነበሩ ሰሙ። ከዚያን ጊዜ ጀምሮ የጠመንጃ እርቆ ተኳሽነትንና የአውቶማቲክ ፍጥነትን አጣምሮ የያዘ ለመፈልሰፍ ምኞቱ አደረባቸው። ከብዙ ጥረት በኋላ ይህንን ምኞት በሥራ ለመተርጐም የመጀመሪያውን ንድፍ በወረቀትር ላይ ነደፉ።

በ1947 ዓ/ም የሶቭየት ጦር ኃይሎች ሊታጠቁት የሚገባ አዲስ መሣሪያ እንዲፈጠር በተደረገው ጥሪ መሠረት ከቀረቡት ተወዳዳሪዎች

ውስጥ ሚካኤል ቲ ካላሽንኮቭ አንዱ በመሆን ሽልማት ሊቀበሉ ችለዋል። ወዲያውኑ የሶቭየቱ መሪ ማርሻል ስታሊን መትረየሱ እንዲመረት ፈቃድ በመስጠቱ «አውቶማቲክ ካላሽንኮቭ 1947» የሚል ስም ተሰጥቶት መሣሪያው በገፍ ሊመረት በቅቷል(Automatic Kalashinkov 1947)። ቧአሁኑ ወቅት «ኤኬ 47» በሚል ስም የሚታወቀውም የስሙን ምዕፃረቃልና የተመረተበትን ዓመተ ምህረት ቆንፅሎ በመውሰድ ነው።

ሜ.ጀነራል ካላሽንኮቭ ከ«ኤኬ 47» ሌላ ልዩ ልዩ መሣሪያዎችን የፈለሰፉ ሲሆን ለአዳኞችም የሚሆኑ ጠመንጃዎችንም ያቀረቡ ሰው ናቸው። በደቂቃ አንድ መቶ ጥይቶች ማንጣጣት የሚችል ሌላ መትረየስም ፈልስፈዋል። ለብዙ ህይወቶች መጥፋትና ለብዙዎች አካለ ስንኩላን ሆኖ መቅረት መትረየሱ የሰጠው ግልጋሎት የሚያጠያይቅ አይደለም። ይህንንም በሚመለከት ሜ.ጀነራሉ የሚሰማቸው ቅሬታ/አዘኔታ እንዳለ ተጠይቀው ነበር። ለዚህ ጥያቄ የሰጡት አስተያየት በአሁኑ ወቅት በአፍሪቃ ውስጥ የሚታየውን የእርስ በርስ ግጭቶችን የሚነካ መልስ ነው፦

«እናት አገራችንን ከጥቃት ለመከላከል መሣሪያውን ፈልስፈናል። ይህን ከመሰለው የተቀደሰ ዓላማ ውጪ አሁን በየቦታው እንደሚታየው የጐሣ ግጭቶች ላይ መሣሪያው ለሚያስከትለው ጉዳት ኃላፊነቱን የሚሸከሙት ፖለቲከኞች እንጂ የመሣሪያው ፈልሳፊዎች አይደሉም።»

(ኒውዮርክ ታይምስ ማርች 13, 1997)

*ምንጭና አገናዛቢ ቅንብር (Reference)- Rudis Resident News, 1996፣ Encyclopedia Britanica (1995), Scientific American (1995)

---

# ከአበው

## ታሪክና ምሳሌ

(ከመጋቢ አእላፍ መክብብ አጥናው)

በመሠረቱ የሰውን ማንነት ሳያውቁ ለመንቀፍም ሆነ ለማሞገስ መቸኮል ትልቅ ውርደት ነው። ያሳፍራልም። ይህንኑ በሚመለከት በአንድ ታላቅ ሳይንቲስትና በአንድ መሐይም/ያልተማረ የሆቴል ቤት ምግብ አቅራቢ መካከል የተካሄደውን ውዝግብ የሚገልጥ አጭር ታሪክና ምሳሌ እንደዚህ ይላል፦

### የአፍ ወለምታ/ዳህፀ ልሣን

የመጀመሪያውን የሐይድሮጅን ቦምብ
ፈልስፎ የሰራ እጅግ ባለጥበብ
ስመ ጥር ሣይንቲስት በሙያው የኮራ
አልበርት አንስታይን ተብሎ የሚጠራ
በሃሳብ ሲናጥ ውሎ በሣይንስ አሰሳ
ወደ አንድ ምግብ ቤት አመራ ለምሣ።
እንደተቀመጠም ወንበር አመቻችቶ
አስተናባሪውን ቦዩን አስጠርቶ
«ምን ምን ምግብ አለህ እስኪ አስረዳኝ በቃል»
ብሎ ቢጠይቀው ቦዩ በመቸኮል
ዓይኑን አፈጠጠ ተቆጥቶ በኃይል
«ያለው የምግብ ዓይነት በወረቀት ቀርቧል
አንብበው ይረዱት ምን ያጠያይቃል?
መለፍለፍ ነውር ነው በጣም ያስገምታል»
ብሎ ገላመጠው፥ አየው እንደ ሕፃን
እንዳልሰለጠነ ልክ እንደመሐይማን።
በመሠረቱ ግን ምግቡ በያይነቱ
በጽሑፍ ቀርቦለት እያየው እፊቱ
ፈላስፋው ዝርዝሩን ማንበብ ያልቻለበት
ዋናው ምክንያቱ
መነጥር ረስቶ ትቶ በመምጣቱ
ተቸግሮ ነበር ይህች ናት ስሕተቱ።

ታዲያስ መጨረሻው ምን ሆነ ውጤቱ?
አሁንም ፈላስፋው ሳያልቅ ትዕግሥቱ
«እስቲ አትቆጣኝ ወዳጄ ኧረ እባክህ!
አንተው አንብብልኝ የምግቡን ሊስት አይተህ»
ብሎ ሲለምነው በፍፁም ትሕትና
«ይስሙኝ የእኔ ጌታ መቸ ተማርኩና
እኔም እንደርስዎ መሐይም ነኝ ገና»
ብሎ መለሰለት ቦዩ ተሳስቶ
ሣይንቲስት መሆኑን አልተረዳም ከቶ።
የአንድን ሰው ሁኔታ ቀድሞ ማንነቱን
ሙያውን ጠባዩን ጠቅላላ ይዘቱን
ደግ ይሁን ወይ ክፉ ምግባሩን ሳትመዝን
መልኩን ቁመናውን ቅርጹን ብቻ አይተህ
ለፍርድ አትቸኩል እንዳይታዘብህ።
ዘመን በወለደው በቴክኖሎጂ ዕውቀት
የመፍጠር ችሎታ ጥበብና ብልሐት
የንግድና የእርሻ የኢንዱስትሪ ዕድገት
በዕጥፍ ከፍ እንዲል የምርት በረከት
ጾጋና ሞገስ ነው የምሁራን ብዛት።

# የግጥም ጉባኤ

## እርሱማ ለነገሩ ነው እንጂ!

ከልሳኑ ስምረት/ሴንትሉዊስ ሚዙሪ

እርሱማ ለነገሩ ነው እንጂ
አፍራሾች ምክንያት አያጡም
በትዕቢት የሠከሩ፣ በስብቀት የገረሩ
እንደ አንጆ የገነተሩ
መሳይ ነገር አይጠፋቸውም
እውነት መሰል ዥጉርጉሩ
የሠርገኛ ጤፍ ጥርጥሩ።
ጣልጣል የሚደረግ ነገር
የጭቅቅት ዕባጭ ብጉር
ለማሳመን አያጡም
ዋግምታቸውም አይበጅም
ፍቱን ሆኖ አያግምም
ጠማማ ነው መርፌያቸውም
እንኳን ዓይን ሊያወጣ ቀርቶ –
የረጋ ቅቤን አይወጋም።
ታዲያ እንደዚያም ሆኖ
ገምባሌያቸው ተተምኖ
ባሕላቸው ተተንትኖ
ፍርጥማቸው ተመጥኖ
ግብራቸው ተፈትኖ።
ሲለካ ጠባያቸው
ሲገመገም ባሕርያቸው
የወረ ጢም ጉፈሬያቸው
የበረዶ ወናፍ ነው
አቦሬ አፋቸው የሚለጠጥ፣ ግን ግብራቸው ሁሉ የጭራቅ ነው
የሰው ሥጋ የለበሱ፣ የእፉኝት እባቦች ናቸው።
ድክመት ጥንካሬያችንን
መላላጥ መውደቃችንን
መነሳት መበርታትን
መታገል መፋለምን፣
ቢሆንስ ለሕይወታችን ዕዘል፣ የቱ ደራሲ ካናቸው
እየወጉ ሲጥሉን ወጌሻነቱን ማን ቀባቸው
እያፈረሱ ሲጠጉን
የቱ ዳኛ ብቃቱን
ማንስ ቪዛውን መታላቸው
ለነፍሳችን ባዮግራፌ
ለሕይወታችን ቅራፌ
የቱ ባለቅኔ ሾማቸው።
እናም ለነገሩ ነው እንጂ
በታኞች ለምን ይጥፋቸው
መፈክር መለባበድ
በቋንቋችን መናገራቸው
በወገን ፍቅር ክሳድ
ሳይቃጠሉ መንደዳቸው
በሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ–
አንድነትን መንፈጋቸው።
እኛም መልስን ልንቸው
እንዲህም ብለን ወቀስናቸው
ቃላችንን እንኳ ሰምተው
ብሶታችን እንዲገባቸው
ልብ እንኳ ባይኖራቸው
ቢጠጥር ኩላሊታቸው።
"ሁሉም ዜጋ ይሁቀብ ይረዳዳን ካነሳችሁ
ዴሞክራሲ ሰፍቶ አዳሜ ይታቀፍ ካላችሁ
ማኅበርተኛው ሲበዛ ዓለም–አቀፍ ሲመስላችሁ
እንዴት ሳያስችላችሁ የገጠርና የከተማን –
ሥንኙን ቆራርጣችሁ
ቅኝቱን አላላችሁ
የዋጣችሁት አጥወልውሏችሁ
ምነው ቅርሻቱ ለበቃችሁ
የጉሳ አይበቃ ብሎ በሣርና በቆርቆሮ ቤት
ሕዝብን አዘናጋችሁ
እንዴት እንደተራ ሌባ ወሸካች ተርታሪ ሆናችሁ
ከተሜውም ሳይሰማችሁ
ለምን እንደገደል ማሚቶ በድምፃችሁ ተላጋችሁ።"
እርሱማ ለነገሩ ነው እንጂ
አፍራሾች ምክንያት አያጡም
በትዕቢት የሰከሩ፣ በስብቀት የገረሩ
እንደ አንጆ የገነተሩ
መሳይ ነገር አይጠፋቸውም
ጣልጣል የሚደረግ ነገር ለማሳመን አያጡም።
እናም ለነገሩ ነው እንጂ
በታኞች ቃል እንዴት ይጥፋቸው
መፈክር መለባበድ
በቋንቋችን መናገራቸው
በወገን ፍቅር ክሳድ
ሳይቃጠሉ መንደዳቸው
በሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ
አንድነትን መንፈጋቸው፣
እንደመሸገር ተለጥፈው
እንደትኋን ማበጣቸው
የደምን ሐውጥ አፍርጠው
እንደውርዴ መመዝመዛቸው
በሀገር ፍቅር ስሜት –
ሳይቃጠሉ መንደዳቸው
በሆድ ሲያውቅ ዶሮ ማታ –
አንድነትን መንፈጋቸው።
እርሱማ ለነገሩ ነው እንጂ
በታኞች እንዴት ይጥፋቸው
የጉርጥ ጥርስ ማፋጨት
በቋንቋችን መስበካቸው
በለንቦጫቸው ንቃቃት
ቅጥፈትን ማደለባቸው።

ከፀር–አምባ ቢፈርሹ
ባይሆን እንኳ ካላቅማቸው
ተኩረፍርፈው ቢጉሸሹ
ሒፍረተ መች ቀርቶላቸው።
ተንቅቶባቸው እስኪሸሹ
ወገንን መውጋታቸው
ከሰላዮች መምነሽነሹ
በምሽት መምከራቸው
እንደ ስልቻ እስኪታሹ
ታሪክ እስኪተፋቸው።

—//—

## ሰላም ጤና እንሁን

(ካሣሁን በቀለ–አትላንታ)

ወንድሜ ብትሆን መከታ ጋሻዬ
አለኝታዬ ብልህ ጥላ ከለላዬ
ቅርበታችን ታውቆ ታሪክ ቢፃፍልን
ቤትህ ካንተ ተርፎ ንብረት ለእኔ አይሆን
ብቻ ባለንበት ሠላም ጤና እንሁን።
ብፎክር ብደንስ ብዘፍን ባቅራራ
የእኔ ቤት ሌላ ነው አልኖር ካንተ ጋራ
ሠርተህ ጥረህ ግረህ አንተም ለራስህ ነው
የወንድሙን የራስ ያደረገ ማነው?
ብትዋሰኝ እንጂ አንድ ክስ ቢመጣ
ብትረዳኝ እንጂ ተቸግሬ ሳጣ
በቤትህ ብኖርም ጉጆ እስከምወጣ
ላዝበት የማልችል የማስተዳድረው
ቤትህ ያንተ ንብረት ያንተ ሀብት ብቻ ነው።
የፍቅራችንን መጠን ሰው ሁሉ ቢደንቀው
ቢዘገብ ታሪኩ ዓለም እስከሚያውቀው
ልመካበት አልችል ንብረቴ ነው ብዬ
ላስይዘው የማልችል ላለብኝ እዳዬ።
ብበላበት እንጂ ጥቂት ቀን እንጀራ
ብኖርበት እንጂ የእኔን እስክሰራ
ላንድ ሰሞን እንጂ ጥቂት መኖሪያዬ
ያንተ ቤት ያንተ ነው ለእኔ ምን ጉዳዬ።
መከታ መመኪያ አለኸኝ ልበልህ
ይህ ታላቅ ፀጋ ነው ቀላል እንዳይመስልህ
አምነን ተቀብለን ይህን ታላቅ እውነት
ሠላም ጤና እንሁን ብቻ ባለንበት።

## ለካ አልጠላሁሽም

ከዶ/ር ፍቅሬ ቶለሳ

ልለፈው ሳትዪ «ጥፋቴን» ቆልለሽ ከሰሽ አሳጥተሽኝ
«ኋንከኔን» ከምረሽ ከፍተሽ ወንጅለሽኝ
ከጉድለት በስተቀር ዋጋ የሌለው ሰው አድርገሽ
ስለሽኝ
ቀና ብዬ እንዳላይ ግርማዬን ገፈሽኝ
ልጄን ሳይቀር ነጥቀሽ ባዶ ቤት ጥለሽኝ
ለልጁ ስትዪ ተመለሺ ብልሽ ወይድልኝ ብለሽኝ
ጥቂት ሳትራራልኝ ጨፍጭፈሽ ገለሽኝ
በበደል ላይ በደል እጅግ በድለሽኝ
እንክትክት አድርገሽ አይሰብሩት ሰብረሽኝ
ነፍሴን አቁስለሽኝ ልቤን አድምተሽኝ
ከእንግዲህስ ወዲያ በቃኝ የእሷ ነገር
እያልኩኝ ሳዝንብሽ ቆይቼ ስማረር
ገበያ ወጥቼ መኪና ጌጡን ሳይ
«እግዚአብሔር ቢሰጠኝ ድንገት አንድ ሲሳይ
ይህንን ይህንን እገዛላታለሁ»
እያልኩኝ ለአንቺ መልካም እመኛለሁ
እራሴን ረስቼ ላንቺ አስባለሁ
ለካ አልጠላሁሽም! ለካ እወድሻለሁ!


# ኢትዮወርድ EthioWord

## ግዕዝና የዓለም ፊደላት በኢንተርኔት

በተሟሉና ባልተቀጠሉ እንዲሁም በተቀጠሉና በጎደሉ ፊደላት ማንኛውም ፎንት የሚቀበል የዊንደውስ ፕሮግራም ውስጥ በማንም ፎንት ለመጻፍ ግዕዝኤዲት GeezEdit $99.00 ። ኢትዮወርድ/ግዕዝኤዲት EthioWord/GeezEdit $199.00 - for use in any Windows 3.1 and Windows 95 program which allow font substitution. ግዕዝን ከዓለም ፊደላት ጋር ኢንተርኔት ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ለማተምና ለመፈለጊያ ኢትዮሳይበር EthioCyber $495.00 ። (Multi-lingual hyper linked documents) ምሳሌ:- ዐረብኛ/Arabic (جشجرجخـشـ) ግሪክ/Greek (Σ'Ωϱ,ῦώεῦ) ሕብራይስጥ/Hebrew (ד"ק,ו"ג) ጃፓን/Japanese (ムラモトメヤメトニ) etc. Type, publish and search Ethiopic documents on the Internet and enjoy it on Windows, Macintosh an UNIX platforms. Check out the Ethiopic pioneers at *http://www.ethiopic.com* and get FREE software.

የኢትዮጵያ ኮምፒዩተሮችና ሶፍትዌር

**Ethiopian Computers and Software**

**9781 W. Fremont Pl., Littleton, Colorado 80123, USA**

**Fettan Graphics 1209 U St. NW, Washington, DC 20009**

Tel: 303/972-2186, 202/785-1618 and 301/270-3865

Fax: 303/973-4342 or 202/785-1626

E-mail: Ethiopian@aol.com – ዶ/ር አበራ ሞላ ኢ-ሜል በግዕዝ (Ethiopic E-Mail)

# ይድረስ ለመታሰቢያ (አሜሪካ) ከአገኘሁ (ጠቅላይ ቢሮ ሸገር)

ሰላም እንደምን ሰንብተሻል? መቼም የአሜሪካን ኑሮ የልፋት ጥረት በሚፈተንበት እንጀራ የድካም ዋጋ የሚከፈልበት ሀገር መሆኑን እንሰማለን። ዓመታት በተቆጠረው የስደት ኑሮሽ የሀገር ቤታችንን የሚያስንቅ አከራረም እንዳልሰነበትሽ እርግጠኛ ነኝ። ለመሆኑ እየበነነ የሚበርደው የአሜሪካ በረዶ ከቅዝቃዜው ጋር ታክሎ እንዴት ይዞሻል? በተቃራኒው እኛ ጋ ፀሐዩ እናት ሰንጥቆ ሊገባ ምንም አልቀረውም። በዚህ ላይ ሰሜን ሸዋን ወያኔ እያመሰችው ነው። እንደ እንኩሮ የሚታመሰው ገበሬ በሞላሌ፣ በሸዋ ሮቢትና በደብረ ብርሃን መሣሪያ አስረክብ በሚል ፈሊጥ የእስረኞች ማጐሪያው ከእስረኛው ብዛት አንፃር በተላላፊ በሽታዎች እንዳይጠቃ በጣም ፈርተናል። ከጐጃም ደብረ ማርቆስ፣ ቢቸና፣ ደጀን የመጣው ወደ 2000 የሚጠጋ አባወራ አርሶ አደር ስሞታውን ለማቅረብ ቢሞክርም ጆሮ ዳባ ልበስ ተብሏል። ይኼም የሰሞኑ የከተማችን የትኩረት ትዕይንት ሆኖ ሰንብቷል። እነዚህ ገበሬዎች ወያኔ ባወጣው የመሬት ሽግሽግ ፖሊሲ በመሬት ክፍፍሉ ድርሻቸውን ባለፈው ሥርዓት ተመራጮች ነበሩ በሚል ከአሁኑ መንግሥት አሽቃባጮች ባነሰ ሁኔታ መሬታቸው እየተሸነሸነላቸው ነው። የእነዚህን ገበሬዎች የደም እንባ ለቅሶ እዚህ ሆነሽ ብትመለከቺ ከልብ ያሳዝናል። ሌላው የሚገርመው ደግሞ በዚያን ጊዜ የህብረት ሱቅ ሠራተኛ የነበሩ የቀበሌ ገበሬ ማህበር ሠራተኞችም ንኪኪ ናችሁ ተብለው በመሬት ሽንሸናው ተዘለው ታልፈዋል።

ለውድ መታሰቢያ፣ የባንዲራና የሀገር ፍቅርን ደህና ሰንብት በማለት በአሁኑ ወቅት የዚህ መግለጪያ በሆነው ጥንት ክብር ለነበረው ብሔራዊ መዝሙርና ባንዲራ ማንም ደንታ የለውም እልሻለሁ። ህዝቡ እኮ ጠልቶት አይደለም፣ ከሥርዓቱ በተወራረሰ የሂደት ምልክቶች ሁነኛ የሆኑትን የሀገር ፍቅር ምሳሌዎች ወደ ጐን ብሎአቸዋል። የዛሬውን ህዝብ መዝሙርና የምክትል መቶ ዕልቅና ባለማዕረጉ ባንዲራችን በቅሌት መዝገብ አስፍሮት ዕውቅናው እንኳን ዘንግተውታል።

መታሰቢያዬ፣ ዛሬ ብዙ ነገር አጫውትሻለሁ ብዬ ስለተዘጋጀሁ ድሮ የግብፅ እስክንድሪያ አፌ ቀላጤ የነበረችውና ዛሬ በፕሮቴስታንት ጽጽስና ላይ ማረፊያዋን ስላበጀችው የክርስትና ግዛታችን ኦርቶዶክስ እንድ ልበልሽ። እዚያ እናንተ ሀገር ታዋቂ እንደሆነው አክተር ቫንዳም በቅልጥፍናቸው በተመረጡ የታጋይ ጳውሎስ ቦዲ ጋርዶች በቤተክርስቲያን ቅጥር ግቢ በመስቀል ፈንታ ሽጉጥ ይዘው ሲጉማለሉ አንበሳ ገዳይ ይመስላሉ። እንደ አረመኔ በጥይት ቆመው ያስደበደቡትና ባህታዊውን ያስገደሉት ጳጳስ፣ እንደ ጲላጦስ ከደሙ ንፁህ ነኝ የሚሉት እንግሊዝኛ ተናጋሪው ጳውሎስ አይን ያወጣው ቅጥፈት ደግሞ ለጉድ ነው። በየቤተክርስቲያኑ የሚደረገውን የምዕመናን አፈሳና እስር እኔ አላየሁም በማሊት የነፍጠኛ ጋሻ ጃግሬ ናቸው የሚሉት አፈቀላጤዎቻቸው ናቸው። በወያኔ አይን ዛሬ ቤተክርስቲያን በተናወጠ ሁኔታ ያለችበትን የሚገልፅ ሁሉ የመ.አ.ህ.ድ. አባል ነው። የእነርሱ መልስ ሌላው በየገዳማቱና በየአድባራቱ የሚካሄደው ግልፅ ዘረፋ ለብዙ ዓመት የተቀመጡ ቅርሶቻችን ጥያቄ ውስጥ ገብተዋል። የሚኒሊክ ቤተ መዘክር በአዲስ አለም የመቃጠሉ ነገር እያንገበገበን እያለ በ1300 ዓ.ም. በግዕዝ የተፃፈ ከግማሽ ሚሊዮን ብር በላይ የሚያወጣው ተዓምረ ኢየሱስ የብራና መፅሐፍ ከሰሜን ኢትዮጵያ ጠፍቷል። እንዲሁ በቤተ መድሃኒዓለም 800 ዓመት ታሪክ ያለው የላሊበላ የወርቅ መስቀልም ተዘርፏል። በእንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ እንዲሉ ከወደ ሰሜን አሜሪካ የመጣ አንድ መጤ ጓደኛዬ ደግሞ በዚሁ በቤተክርስቲያን ዙሪያ በተነሣ ጉዳይ ብግን ነው ያደረገኝ። ይኸ ጓደኛዬ የመጣው በጥምቀት ሰሞን በመሆኑ ታቦታት ሁሉ ሲወጡ ታቦቱን የተሸከሙትን ቄሶች በማንቋሸሽ ታቦቱን የተሸከመው ቄስ ሁሏ ትናንትና ከሚስቱ ጋር ሲባልግ አምሽቶ ነው ሲል ከመጤፍም አልቆጠረውም። የመጀመሪያ የስደት ሀገሩን የአቴንስ ቤተ ክርስቲያን እያደነቀ ታቦቱ የሚወጣው በወርቅ ሰረገላ ነው ብሎኝ ቁጭ! ታዲያ ይሄን ምን ትይዋለሽ? እኔ የሚናገር የሜዳ አህያ ነህ ብዬዋለሁ። በዚህ አጋጣሚ አንድ ነገር ልነግርሽ ፈለግሁ በእስጢፋኖሱ ቤተ ክርስቲያን በጥይት ተደብድበው የተገደሉት ባህታዊ ፈቃደ ሥላሴ መካነ መቃብራቸው ያረፈበት ጭቁኑ ሚካኤል ቤ/ክርስቲያን ታቦት ለዘንድሮው ጥምቀት ከተራ በዓል በቤቱ እንዳሳለፈ ታውቂያለሽ? ወደ ጃንሜዳም ብቅም አላለም። እርሱም የቁም እስረኛ ሆኖ ነው የዋለው።

ወዲህ ወዲያ ቀባዠረ አትበይኝና ውድ መታሰቢያዬ ሁሉንም እንድታውቂው ስለምፈልግ

ነው ከሞላ ጐደል በአገራችን የተከሰቱ አሳፋሪና አስደንጋጭ ገፅታዎችን የማመላከትሽ። በዚህም እንደማትስለቺኝ እርግጠኛ ነኝ። ኦ.ል.ማ. (ኦሮማ ልማት ማህበር) በሚል በጐሰኝነት የተመሠረተው ለደሀው ግን ትንሽ ጠብ የማይልለት ማዕከል ለገንዘብ ማሰባሰቢያ ቴሌቶን አዘጋጅቶ በሚጠሉት አማርኛ እየለመነ ከ107 ሚሊዮን ብር በላይ አግበስብሷል። ይህ የባለሥልጣኖች መተያያ ይሆናል ተብሎ በተገመተው ገንዘብ የደሀው ገበሬ ችግርና አበሳን በጥያቄ ምልክት ውስጥ ብቻ አስቀምጦ በእነርሱ ስም የሚነገድ ጉዳይ እንደሆነ ኢትዮጵያዊው ሁሉ አውቋል። የቦብ ማርሊ ቤተሰቦችም እንደ እግዚአብሔር ከሚያመልኩት ከራስ ተፈሪ ምድር መጥተው የሙዚቃ ዝግጅታቸውን በመስቀል አደባባይ የአድዋን ድል አስታከው ሲያቀርቡ ገቢው ለዚህ ለተወሰኑ ሰዎች የኪስ ማድለቢያ ለሆነው ማዕከል ለአልማ መሆኑ ራስ ተፈሪያንም መጠቀሚያ መሆናቸው ሁሉንም አሳዝኗል።

በመጨረሻ አቶ ታምራት ላይኔ በዘመነ ደርግ ያላዩትን እስር ቤት በእርሳቸው ትግል አጋርነት በተገኘው አብዮት ሥር ዘብጥያ የመውረዳቸው ጉዳይ የድፍን አዲስ አበባ ግርምት ሆኗል። የአራዳ ልጆችማ እንደሚሉት ስንቅ የሚያመላልስላቸው የአሁኑ ጠ/ሚኒስትር ታጋይ መለስ ዜናዊ ነው ብለው የሚያወሩት። የሚያስቀው ግን የሁለቱ የአማራ ድርጅት የብአዴንና የመአህድ የአመራር አካል ሊቀመንበሮች ከርቸሌ ተፋጠው ቁጭ አሉልሽ! ትናንት ነፍጠኛሲሏቸው ከነበሩት ፕሮፌሰር አሥራት ሰፈር እሳቸውም የሙስና ነፍጠኛ ሆነው ሲገቡ፣

*ተረኛ ነኝና ... እንዳትሸበሪ፣*

*ሰለይሽ አዝናለሁ ኢ.ሀ.አ.ዴ.ግ ደህና እደሪ።* የሚለውን ዜማ በፉጨት እያስነኩት ነው ብለውኛል። የዚህንም መጨረሻ እንዲሁ እየተከታተልኩ እፅፍልሻለሁ። በመጨረሻም ከዛሬ ሃያ አመት በፊት «ኢትዮጵያ ቢያ ኬኛ» (ኢትዮጵያ የእኛ ሀገር) እያለ በልሳኑ እንዳላንጐራጐረላት ዛሬ «ኦሮሚያ» እያለ ዲስኩሩን ለሚያሰማው፤ በሰሜን አሜሪካ በተደላደለ ኑሮ የሚኖረው የአሊ ቢራን አድራሻን ካገኘሽ በቶሎ ላኪልኝ። ብዙ ኢትዮጵያውያኖች ሊፅፉለት ይፈልጋሉ። የእርሱ የኮንትራት ልሳን የሶስት ሺ ዘመኑን የአንድነት ቆይታ አይንደውም ነው የምንለው።

እስከዚያው ደህና ቆይኝ።

## ስለ ኢትዮጵያ ቋንቋና ጽሁፍ በአቶ ሰይፉ መኩሪያ

ማርች 8, 1997 በአትላንታ ማዘጋጃ ቤት HA-HU In America በሚል ርዕስ ተዘጋጅቶ በነበረው ውይይት መሪ የሆኑት አቶ ሰይፉ መኩሪያ ከሃያ አምስት አመታት በላይ በአዲስ አበባና በካርቱም ዩኒቨርስቲ አማርኛና ፎክሎር ያስተማሩ ሲሆን ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በወያኔ መንግሥት ከተባረሩት 42 የዩኒቨርስቲ መምህራኖች ውስጥ አንዱ ናቸው። አቶ ሰይፉ አራት የግጥም መጻሕፍትም ያወጡ ሲሆን መጣጥፎቻቸውም በልዩ ልዩ ያካዳሚክ መጽሔቶች ወጥተውላቸዋል። ከግጥሞቻቸውም ውስጥ፣ በግሪክኛ፣ በመስኮብኛ፣ በኢጣሊያንኛና በእንግሊዝኛም የተተረጐሙ ይገኙባቸዋል።

አቶ ሰይፉ ለውይይቱ መነሻ አድርገው ያቀረቡት ስለ ኢትዮጵያዊ ባህላችን በተለይም በዚህ ባህል ውስጥ ስለሚገኘው ብቸኛ የጥቁሮች ፊደል የሆነው አማርኛ ፊደል ቋንቋና ጽሁፍ በአሁኑ ጊዜ በኢትዮጵያም ሆነ እዚህ በአሜሪካ ባለው ኢትዮጵያዊ በግላዊና በቤተሰባዊ የኑሮ መልካችን ምን ቦታ ይዘው ይገኛሉ? እያንዳንዳችንስ እየተንፀባረቀብን ያለው



ኢትዮጵያዊ ባሕል ያሳስበናል? እንፈልግሀም ብንለውስ ይተወናል? በሚሉትና በመሳሰሉት ጥያቄዎች ላይ ያተኮሩ ሲሆን በእነዚህና በሌሎች ጥያቄዎች ላይ ከውይይቱ ተሳታፊዎችም ጥሩ ጥሩ የተለያዩ ሀሳቦች ተሰንዝረዋል። ይህ ውይይት በአይነቱ ከሌላው ጊዜ የተለየ በመሆኑ በዕለቱ የተገኙ ኢትዮጵያውያን ትምህርት ያገኙበት መሆኑን አውስተዋል።

# ዜና ቤተክርስቲያናት

## የቶሮንቶው ሐዋርያዊ ጉዞ



### በቶሮንቶ አዲስ የቅድስት ማርያም ቤተክርስቲያን ተመረቀ

ከኤልሳቤጥ መስፍን
(ከአትላንታ የሐዋርያ ጉዞ ተወካይ)

**በስመአብ ወወልድ ወመንፈስ ቅዱስ አሀዱ አምላክ አሜን!**

ዕለቱ ዓርብ የካቲት 14, 1989 ወይም (ፌብረዋሪ 21, 1997) ስምንት የምንሆን የአትላንታ ሰአሊተ ምህረት ቅድስት ማርያም ቤ/ክርስቲያን መዘምራንና አንድ ምዕመንን ጨምሮ ወደ ካናዳ ቶሮንቶ የተደረገ ሐዋርያ ጉዞ መነሻነቱ በቶሮንቶ ከሚገኙ ከአባት፣ ከእናቶቻችንና ከእህት ወንድሞቻችን ጉን ለመቆምና የደስታቸው ተካፋይ ሆኖ ለመገኘት ሲሆን፤ በተለያየ ችግርና ምክንያት ለመሳተፍ ያልቻሉ የቤተክርስቲያናችንን ምዕመናንና መዘምራንን በመወከል የእመቤታችን የቅድስት ድንግል ማርያም ልመናና የልጇም ቸርነት ከእኛ ጋር እንደሆነ በማመን በአባታችን በአባ መላከ ፀኃይ ገ/ማርያም የቀረበልንን ፀሎተ ቡራኬ ከተቀበልን በኋላ በወንድማችን በዲያቆን ኃይለኢየሱስ ሸኝነት ጉዟችንን ጀምረን ከቀኑ 1:30 ሰዓት ላይ ካናዳ አየር ማረፊያ ደረስን። እንደደረስንም ከሚመረቀው ቤ/ክርስቲያን የተወከሉ ሶስት የቦርዱ አባላት ይጠብቁን ስለነበር ያለምንም ችግር ለማየት ወደጓጓነው ቤ/ክርስቲያን አመራን።

ከአቅራቢያው እንደደረስን የእኛነታችን መለያና መኩሪያ የሆነው ባንዲራችን በቤተክርስቲያኑ ዙሪያ አገልድሞና ተንቆጥቁጦ ስናይ ከደስታ ብዛት ዕንባ የተናነቀን ብዙዎች ነበርን። ከዚያም እንደእኛ ከተለያዩ ቦታዎች ከመጡት እንግዶችና ከቤተክርቲያኑ አባላት ጋር ከተዋወቅንና የእግዚያብሔር ሰላምታ ከተለዋወጥን በኋላ ከተቀበሉን አንዷ ከነበረችው በእህታችን በወ/ሮ ፀሐይ አማካኝነት ዙሪያ ገባውን በጉብኙንበት ወቅት እንዳየነው የተገዙት ሁለት በጣም ሰፋፊ ዌር ሀውስ የነበሩ ቤቶችን ሲሆን ሁለቱም ጉን ለጉን ከመሆናቸው የተነሣ ከውስጥ ሆኖ ሲታይ በራሱ ክፍል ውስጥ የሚዘዋወሩ ከመምሰሉም በላይ ከአንዱ ወደሌላው በቀላሉ ሲረማመዱ አይተናል። በተጨማሪም እያንዳንዳቸው እጅግ በርካታ ክፍሎችና አዳራሾች ያላቸው ሲሆን ክፍሎቹም ለተለያዩ ንዑሳን ዘርፎች መጠቀሚያ እንደሚሆኑ ገፀውልናል። እንዲሁም በውጭ በኩል ተንጣሎ የሚገኘው የፓርኪንግ ቦታ በትንሹ እስከ 600 መኪናዎች ማቆም እንደሚችል ተረድተናል። ሌላው የተመለከትነውና ትምህርት የወሰድንበት ነገር እያንዳንዱ ለራሱ ቤት ከሚሰጠው ክብር በበለጠ ለእግዚያብሔር ቤት ማድረግ እንዳለበት የገባቸው በመሆናቸው በተግባር ሲተረጉሙት ማለትም እውነተኛ ፍቅር በተሞላበት ሁኔታ ደፋ ቀና ሲሉ ግማሹ መቅደሱን ቀለም ሲቀባ፣ ሌላው መጋረጃ ሲሰራ፣ አንዱ ኤሌክትሪክ ሲዘረጋ፣ ዕዳት ሲያፀዳ እንዲሁም ሴቶቹ ለበአሉ ቀን መድረስ ያለበትን የመዝሙር ልብሶች ሲሰፉ ግማሾቹ እንግዶቻቸውን ለማስተናገድ ምግብ ለመሥራት በትልቁ ኪችናቸው ሞልተው ሲንጉዳጉዱ በተለይም ወንዱ ልጅ ሽርጡን ታጥቆ ሽንኩርት ከተፋውን ሲያሳምረው ተመልክትናል። በእውነት ህብረታቸውንና አንድነታቸውን ለተመለከተና የኢትዮጵያዊነት ደም ለሌለው ሲያስቀሞ ለእኛ ግን በኢትዮጵያዊነታችን እንድንኮራ አድርጉናል። ዛሬ በአንዳንድ ቦታ እየጠፋ ያለውና ነገር ግን ሊጠፋ የማይገባው ባህላችንና የጥንት የአባቶቻችን መታወቂያ የሆነው መከባበር ትህትናና ፍቅር በእነሱ ዘንድ ተከማችቶ በተግባር ሲተረጉም እንደ አንድ ልብ አሳቢ እንደ አንድ አፍ ተናጋሪነታቸውን አይተናል።

ከዚያም በእለቱ የሚደረገው ማህሌት የተቆመ ሲሆን እንደባህሉና ወጉ ዙሪያው ሲረጭ ቅባቅዱስ ሲቀባና ስርአቱ ሁሉ ሲካሄድ ከቆየ በኋላ ቅዳሜ ልክ ከንጋቱ 8:00 ሲሆን በአባታችን በአቡነ ዜና ማርቆስ ቅዳሴ መሪነት በሌሎች አባቶች ማለትም በብፁዕ አባታችን በአቡነ ይስሀቅ የምዕራቡ ዓለም ሊቀ ጳጳስና እንዲሁም በአቡነ መልከጼዴቅ፣ በአባ መንግሥቱ፣ በአባ ሲሳይ፣ በአባ ገ/ሥላሴ፣ በአባ ማርቆስ፣ በጃማይካው ካህን በአባ ጳውሎስና በእለቱ በተመረቀው አባት ሊቀ ካህን ምሳሌና እዛው ካናዳ የሚገኙ 5 ዲያቆናትና ሁለት የጃማይካ ዲያቆናትን ጨምሮ እጅግ በጣም በደመቀ ሁኔታ ሲካሄድ ስናይ



በእውነት ባህላችንና ሐይማኖታችን በእኛ ብቻ ሳይሆን በሌሎች ሀገር ዜጐችም ሲንፀባረቅና ሲመሰከረለት ሲታይ በዘላለማዊው ንጉስ በእግዚያብሔር የተቀደሰችና የተባረከች የማትጠፋዋ ትንቢት የተነገረላት ሃይማኖቷ የጠነከረ ባህሏ የማይጠፋ አኩሪ የሆነችው የኢትዮጵያ ልጅነታችን ሊያኮራን ይገባል። ሌላው በጣም የተገረምንበት ነገር ለቅዱስ ቁርባን የቀረበው ሰው ብዛት ሲሆን ጠቅላላው ምዕመን ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም። ከዚያም ከቀኑ 11:00 ላይ ቅዳሴው እንዳበቃ የቦርዱ ሊቀመንበር ስለቤተክርስቲያኑ አመሠራረት ሰፊ ማብራሪያ የሰጡ ሲሆን በአጭሩ ከአሁን በፊት ቤ/ክርስቲያን በኪራይ ሲጠቀሙ ቆይተው በምዕመናኑ ታላቅ ጥረት የተለያዩ መዋጮዎችን በመሰብሰብና ፈንድሬዚንግ በማዘጋጀት 900,000 ሺህ የካናዳ ዶላር በማውጣት ይህን የመሰለ ቤተክርስቲያን ሊገዙ እንደቻሉ የገለፁ ሲሆን በተለይም በገንዘብ ሊተመን የማይችለው የተለያየ ሙያ ያላቸው ታታሪ ምዕመናኖች በእውቀታቸውና በጉልበታቸው ያደረጉት፣ ታላቅ አስተዋጽኦ እንደሆነ ጨምረው ገልፀዋል። በመቀጠልም ያሉት 3 ታቦታት ማለትም የማርያም፣ የገብርኤልና የሚካኤል ሲወጡ በአባቶች አጃቢነት አዳራሹን በሞላው ምዕመናን እልልታና ዊብጨባ እንዲሁም ከተለያየ ደብር በመምጣት ለበዓሉ ታላቅ ድምቀትን በሰጡት መዘምራን ሽብሸባና ዝማሬ በመታገዝ ዞሮ ከገባ በኋላ ከሩማኒያ፣ ከግሪክና ከተለያዩ የውጭ ሀገር የመጡ ዜጐች የማበረታቻ ንግግር የተደረገ ሲሆን የሀገሩ የቶሮንቶ ሜር (ከንቲባ) ከኪራይ ቤት ተነስተው እዚህ መድረሳቸውን በማስመልከት አድናቆታቸውን ገልፀዋል። በመጨረሻም በአባቶች የተባረከልንን ማዕድ ተቋድሰን የደከመ ሰውነታችንን አሳረፍን።

በማግስቱ ማለትም ዕሁድ ዕለት መደበኛው ቅዳሴ በመቀጠል ከቅዳሜው ባላነሰ ደማቅ በዓል የነበረ ሲሆን በዓሉ የሚያበቃበት 3ኛ ቀን በመሆኑ በከበሮ በዝማሬ በሽብሸባና በእልልታ ኢትዮጵያ ሀገራችንን በማያስታውስ የአከባበር ሁኔታ በዓሉን በደስታ አሳልፈናል።

ይህ ሁሉ ከውዲቷ አገራችን ከስንት ሺህ ማይልስ ርቀት ላይ ሆነን የአገራችንን ቤተክርስቲያንና ህዝቡን እንድናስብና እንድናስታውስ ያደረጉን የእነዚህ የቶሮንቶ የምድኃኒያለም የቦርድ አባላትና ምዕመናንን በአትላንታ ምዕመናን ስም እያመሰገንን፤ በመጨረሻም በተለይ 3 ቀን ሙሉ ያን ሁሉ ከተለያየ ሀገር የመጣ ምዕመናንን በትህትናና በትዕግስት ያስተናግዱ የነበሩት አባላት ብርታት ፍፁም የማንረሳው ሲሆን፤ በተለይም ሶስት ቀን ሙሉ ሁለት ክፍል ቤታቸውን ለእኛ ማለትም ለአትላንታ ተጓዦች ለቀው በአንድ ክፍል ውስጥ ልጆቻቸውን አጉረው በትህትናና በፍቅር ሲያስተናግዱን የነበሩት ወ/ሮ ወይንሸትና ቤተሰቦቻቸው፣ ቤተክርስትያኑንና ሀገሩን ሲያስጐበኙን ሲቀበሉንና ሲሸኙን የነበሩት ለወ/ሮ ፀሐይና ቤተሰቦቻቸው፣ ለጠቅላላው ቦርድ አባላትና ምዕመናን ምስጋናችን እያቀረብን ፍቅራችሁ ለዘላለም እንዲህ እንዳማረ እንዲቆይና እኛም ከእናንተ ያየነውን ደግነትና ትህትና በተግባር ለመተረጉም አምላክ እንዲረዳን የሁላችን ፀሎት ይሁን እንላለን።

እግዚያብሔር ኢትዮጵያ ሀገራችንንና ሕዝቦቿን ይባርክ!!



# እኔ የምለው

## «ትርፍ» ያለው ጓደኝነት

*(ከውሂብ ጥሩነህ)*

ጴንዴት ሠነበታችሁ?› ብዬ ብጀምርስ? በየወሩ ካገር ቤት ከቤተዘመድ በሚመጣ ደብዳቤ «ኧንደአምቦ ውሃ ለምትጠማኝ፣ እንደእማዬ እንጀራ ለምትርበኝና ናፍቆትህ እንደአባዬ አለንጋ ቀጥቅጦ ቀጥቅጦ የአያታችንን ማማ ላስመሰለኝ ውድ ክቡር ...» የሚል፣ ቢመዘን ‹ኩንታል› የሚወጣው ሰላምታ የለመደ ጉብል እንደዚህ አጠር ያለ ሰላምታ ሲያይ «የቃላት ቁጠባው» አበሳጭቶት ጥርሱን እንደሚያፋጭብኝ አውቃለሁ ... ቢሆንም ግን እውነት እንዴት ከርማችኋል?

«ምነው ሰላምታ ደረደርክ? ምን ፈልገህ ይሆን?» አትበሉኝና ግን...በምድረ አሜሪካ በጣም ትሁትነት የሚበዛው «የሆነች ጥቅም ነገር» ሲፈለግ ብቻ ነው ይላሉ...በዚህ ነገር ‹ፒ.ኤች.ዲ.» ያላቸው ሽቁጥቁጤዎች!!

«አዳሚኮ ባህታዊ እየመሰለ የሚቀርበኝ አባቱ በሚመጣ ሰው እንደላኩለት ዕቃ ተጠቅሞ ሊወረውረኝ ነው! ኪስ አውላቂ ሁላ!!» እያለ በንዴት ምራቁን የሚተፋው አበሻ ቁጥሩ በርከት ያለ ነው እየተባለም ይወራል።

እውነት ግን ... በተዋወቃችሁት ማግስት ስልክ ደውሎ «አንተን የመሰለ ቅን፣ ለሰው አሳቢ፣ ደግ ሰው፣ ማዘር ቴሬሳ የሆነ ሰው አሁን የት አገኛለሁ? አስር አመት አብሬያቸው ከከረምኩት ጥርቅምቃም ጓደኞቼ ይልቅ ሁለት ቀን የማውቅህ ባልንጀራዬ አንተ ትሻለኛለህ!» እያለ ያሞጋገሳችሁ ‹አራዳ› አንድ ሳምንት ቆይቶ ሃዘን በሰበረው ድምፅ «ዶክተር ጋ ልመረመር ሄጄ ይሄ እጅህን የሚያቃጥልህ፣ ሆድህን የሚቆርጥህ፣ ምግብ አላስበላ የሚልህ፣ አልኮል አላስጠጣ የሚልህና ትንፋሽህ ቁርጥ ቁርጥ የሚልብህ ነገር «የገንዘብ እጦት» የሚሉት መጥፎ በሽታ ይዞህ ስለሆነ ነገሩ ተባብሶ የማይድንበት ደረጃ ላይ ከመድረሱ በፊት በአፋጣኝ አንድ መላ መፈለግ አለብህ ስላለኝ አይንህ እያየ ከምሞትብህ እጅህ ላይ ያለውን ብር...ጴንትትን› በለኝ!» ብሎ ‹አንጉል› አድርጓችሁ አያውቅም ወይ?

‹በእግር በፈረስ› ስታስፈልጉት ጥፍት ያለ ጓደኛችሁ ‹መልዕክትኛ ልኮ› «ሥራዬ ለምንም ነገር ጊዜ ስለማይሰጠኝ እኔን ባትፈልገኝ ጥሩ ነው! ምግብ እንኳን ቁጭ ብዬ በሥርዓት ላምጨ የምውጥበት ጊዜ ከማጣቴ የተነሣ የሚታኘክ ምግብ ትቼ ሾርባ መጠጣት ከጀመርኩ ሶስተኛ ወሬን ይዣለሁና እኔና አንተ ከአሁን በኋላ የመገናኘታችን ነገር ተስፋ ያለው አይመስልም! እግዚያብሔር ጥናቱን ይስጥህ!» የሚል ዓይነት መልዕክት በላከ በወሩ አካባቢ በድንገት ‹ጊዜ አግኝቶ› «አንገናኝም ወይ?» በሚል የናፍቆት ጥያቄ ‹መቆሚያ መቀመጫ› የሚያሳጣችሁ «የሆነች ነገር» ሲፈልግ ነው። ታዲያ እናንተም በተራችሁ ጊዜ አጥሯችሁ እንደመጥፋት ብትሉበት «በጣም ስለናፈቅከኝና ‹ለእግዜር ሰላምታ› አጥብቄ ስለምፈልግህ እንደምንም ብለህ ከሰሞኑ አንዱ ጋ እንገናኝ! አደራህን! እኔ ያልገባኝ ነገር ግን እኔ የናፈቅኩህን ያህል አንተ እኔን ለምን እንዳልናፈቅከኝ ነው! ለነገሩ ግን ምን ሆነህ ነው? የልብ ጓደኛ እንዴት እንዲህ ያደርጋል?... ለማንኛውም ግን ዓይንህን ለማየት በጣም ስለቸኮልኩ በአካል ተገናኝተን ዓይንህን እስከማይ ድረስ «ጴንገናኛለን! እኔ ተስፋ አልቆርጥም!» የሚለውን የማርታ አሻጋሪን ዘፈን መርጨልሃለሁ! ...» ይላችሁና በመልዕክቱ መዝጊያ ላይ «... ውይ ረስቼው!...ይሄውልህ...እንደው ከእኔ ጋር ለመገናኘት ጊዜ የሚያጥርህ ከሆነ ግን...እኛ አገር ቤት ያሉት ወንድ አያቴ ‹ከአሞኛቸው› ጋር ወደዚህ መምጣት ስለሚፈልጉ የዋስ ወረቀት እንድትፈርምላቸው በስልክ «አደራህን የእኔ ልጅ» ብለውሃል። ስለዚህ ፎርሞቹን ካሉበት ቦታ አምጥተህ ፈራርምና ከኔ ጋር እንኳን ባንገናኝ አንዱ ጋ ብትተውልኝ ሄጄ እወስደዋለሁ...» ቢላችሁ ሰውዬው እንዲህ አጥብቆ የናፈቃችሁ በእውነተኛው ናፍቆት አለመሆኑ ወዲያው ይገባችኋል። ጴንኳን ይህቺን የዝንብ ጥርስ ወላቃ አውቃለሁ› ይባል የለ!!

ይሄ ‹ጴንትን እንድታደርግልኝ ፈልጌ ነበር!» እየተባለ በየመንደሩ የሚመሰረት ‹የልብ ጓደኝነት› ታዲያ ያላቀያየመው አበሻ የለም ሲባል አልፎ አልፎ እንሰማለን...በሰፈራችን ሬዲዮ!

እዚህ አገር ገና የመጣ ጊዜ ኤ እና ቢን አገጣጥሞ ስሙን መፃፍ ለማይችል ሰው ‹ለክፉ ቀን ዘመድ ይሆነኛል› ብዬ ‹ሀሁ› እንዳላስተማርኩት፣ መኪና መንዳት እንዳላስለመድኩትና የአገር መውጫና መግቢያ አሳይቼ ከፈረንጅ አገር ማጅራት መቺዎች ተርፎ ራሱን ሰው እንዲያደርግ እንዳልረዳሁት ጊዜ ተለውጦ እኔን ችግር እንደኳስ እየተጫወተብኝ ነውና ‹ጎል› ከመግባቴ በፊት በፈጠረህ አንድ በለኝ ብለው ‹አንተን የምረዳበት ጊዜ ስለሌለኝ ሚካኤል የሚባለው አበሾች ያሰሩት ቤተክርስቲያን ሄደህ ስለእመብርሃን ብትል ተሳላሚዎች የሚጨክኑብህ አይመስለኝም› ብሎ ገላመጠኝ። ምነው ፈጣሪ ይሄንን ነገር በዓይኔ ከምታሳየኝ፣ በጆሮዬ ከምታሰማኝ በበሽታ እንደወሰድካቸው አያቴ ‹በአስቸኳይ› ወደቤትህ ብትጠራኝ!» እያለ አንዳንዱ ከእግዚ.ያብሔር ጋር መነጋገር የሚጀምረው ‹የልብ ጓደኛዬ› ብሎት የነበረው ሰው ጓደኛ ያደረገው ነገሮች መስመር እስኪይዙለት ብቻ እንደነበር ሲረዳ ነው። («እኔ የምለው ግን ... ይሄ «ጊዜ የለኝም» – «ጊዜ አጣሁ!» «በጣም ቢዚ ነኝ» የሚባለው ነገር በቃ አሜሪካን አገር ውስጥ ሥራ ያለውም ሥራ የሌለውም ሰው አፍ ማፍቻቻ ንግግር ሆኖ ቀረ ማለት ነው? አገር ቤት ላለ ዘመድ በስድስት ወር አንዴ ደብዳቤ ለመፃፍ «ጊዜ አጣሁ» እያለ ተቆጥቶ ሲያማርር የሰማችሁት ጉበዝ በቀን «ትንሽ» ሰዓት እየሠራ ረዘም ያለ ትርፍ ሰዓቱን የአልጋው ሽቦ እስኪላላ ድረስ በመተኛት እንደሚያሳልፍ ብትሰሙ ይቺ «የጊዜ እጥረት» የሚላት ነገር በህልሙ ከጀመራት ሁለተኛ ሥራ ጋር የተያያዘች ሳትሆን አትቀርም ማለታችሁ አይቀርም!)

እውነት ግን...የእነዚህ ‹በጥቅም› የሚዋደዱ «ጓደኛሞች» ጠስ ለሌላውም መትረፉ ‹ቆሽት አያደብንም› ወይ? የሆነ ነገር ካልፈለጉ በስተቀር ከሰው ጋር የማይቀላቀሉ ብልጣ ብልጦች በደል ያደረሱበት ጉበዝ ሰው መሸሽ የጀመረበትን ምክንያት ዝርዝር አድርጎ ቢነግራችሁ ብሶቱ ባያስለቅስ ከንፈር ማስመጠጡ የማይቀር ነው...

«መኪናዬ እንዴ ‹አንበሳ አውቶቡስ፣ እንዴ ሎንቺና፣ ቤቴ የስደተኞች መጠለያ፣ የሱሪዬ ኪስ አዳሜ በተመቸው ሰዓት ገንዘብ የሚያወጣበት ‹ንግድ ባንክ› ሆኖ እኮ የከረመው ስሜን እያቆላመጠ የሚጠራኝ ሞላጫ ሁሉ ባልንጀራዬ እየመሰለኝ ስንከረፈፍ ነው! ጅላጅል!!» ብሎ ራሱን ይሰድብና...«የመኪናዬ አራት ጐማዎችና ሞተሩ ‹በህብረት› መንገድ ላይ ፈንድተውብኝ ገበያ ሂጄ አፌ ላይ የማደርገውን ቂጣ እንኳን የምገዛበት መጓጓሣ ስላጣሁኝ ጠሜን እንዳላድር ‹እባካችሁን ተቸገሩልኝ!› ብዬ ባልንጀሮቼን ብማፀናቸው ጊዜ የለንም! እግዚያብሔር ይርዳህ!› የሚል ለኔ ለባለውለታቸው ሳይሆን ለአባት ገዳይ የሚሰጥ መልስ ሰጡኝ...ድሮምኮ አዳሜ የኔን ጓደኝነት አጥብቆ የሚፈልገው ሆዱ ሲጎልበት ብቻ ነው...የቀን ጅብ ሁላ!!» ብሎ የግምባሩን ላብ ጠረግ እያደረገ ከሰው ጋር ዳግም ውለታ ላይዋዋል እየማለ ቢያስረዳችሁ ትንሽም ብትሆን አብራችሁ ‹መቃጠላችሁ› አይቀርም!

እኔ የምለው ግን ... «ተጠቀመብኝ»፣ «ተጠቀምኩበት» ለመባባል እንደዕድር ድንኳን ቶሎ ተተክሎ ቶሎ የሚፈርሰው ጓደኝነት ቢቀርስ? ‹ብትርፍ› ላይ ብቻ የተመሰረተ ‹ጓደኝነት› መጨረሻው የአንዱን ቆሽት አሳርሮ ጠመንጃ መወልወል እንዲጀምር መገፋፋት ስለሚሆን ... አለ አይደል ... የሰው ናላ ባናዞርስ?

እስቲ ለማንኛውም በጤና እንክረም!!

---

# ስንጠረዥ ፩

በሰይፉ አዳነች ብሻው

(መ) መብቱ የተጠበቀ ፲፱፻፹፱ ዓመት

ይህን የስንጠረዥ ጨዋታ ከግራ ወደቀኝ፤ ከቀኝ ወደግራ፤ ከላይ ወደታች፤ ከታች ወደላይና በሰያፍ በመከበብ ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ቃላት ይፈልጉና ከተከበቡ ቃላት የሚተርፉትን በማጋጠም የሚያገኙትን መልስ ይላኩልን።


| | | |
|---|---|---|
| ልባም | ቃልኪዳን | ክብት |
| ልጅቷ | ትብብር | ዳባ |
| ልጅነት | ነበልባል | ጉርብትና |
| መርከብ | አልማዝ | ጉትት |
| ምግባር | አበል | ጉያ |
| ሳም | አቡ | ጉቶ |
| በር | አባ | ዐርብ |
| በትር | አቶ | ጥምዝዝ |
| ባል | አርማ | |
| ባቡር | <u>ኢትዮጵያ</u> (ለምሳሌ ያህል ተሞልቷል።) | |
| ባዶ | እያዩ | |
| ብስል | | |
| ብሶል | | |

| | | | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| መ | ዐ | ን | ዳ | ኪ | ል | ቃ | ቷ | ጅ | ል |
| በ | ር | ኢ | ል | ጅ | ነ | ት | ነ | ል | ጥ |
| ት | ብ | ከ | ሶ | ባ | ል | ት | በ | ሳ | ም |
| ር | ል | ስ | ብ | ዶ | ባ | አ | ል | ማ | ዝ |
| ዮ | ር | ብ | ብ | ት | ም | ግ | ባ | ር | ዝ |
| በ | አ | አ | ቶ | ጵ | ያ | ጉ | ል | አ | እ |
| ባ | ቡ | ር | ጉ | ር | ብ | ት | ና | ያ | ባ |
| አ | ያ | ጵ | ዮ | ት | ኢ | ት | ዩ | ዳ | ያ |


## ያለፈውን ሰንጠረዥ የመለሱ

1. ረታ መኮንን (አትላንታ) 2ኛ ጊዜ
2. አማረች አበበ (ከአትላንታ)
3. ተስፋሁን ልጃለም (ኦሃዮ)
4. ገብሬል መካሻ (ጆርጂያ) 2ኛ ጊዜ
5. ሰላማዊት መኮንን (ሳን ሆዜ)
6. ጋሻው ታፈረ (ሎስ አንጀለስ)
7. አስናቀ አሰፋ (ሂውስተን)

(ሳያቋርጡ 5 ሰንጠረዥ በትክክል ሞልተው ለሚልኩ ለስት አትም በነፃ እንሸልማለን)



# ቃላት በሰንጠረዥ




## ወደጎን

1. አለመቸኮል
5. ፃፈ (በመኪና)
8. የሳቅ ምንጭ
9. የጠረጴዛ ጨዋታ
11. አጋዥ
12. በዱላ ______
13. ውሃ ማሠራጪት
15. ሴት ልትወልድ ስትል
17. ልብስ መስፊያ
19. አገር የሚገዛ
21 መቀመቅ
24. ትልቅ እንጨት
26. ቀዳዳ አብጅ
28. ግዙፍ
30. በፋሲካ የሚታረድ
31. መምህር
33. ግጥም ያልሆነ ንባብ
35. ከአንገት በላይ
36. በፈረስ የሚጎተት መጓጓዣ
37. መከራ
39 ፍርሃት
40. ዞር ዞር ማለት

## ወደታች

1. ፊት ፊት ሄደ
2. ገብጋባ
3. ሲመሽ
4. በጋብቻ የሚመሠረት
6. ታሪክ ተናገረ
7. ውስጥ እጅ
10. ገላ ሲበላ የሚደረግ
14. በዳኛ የሚሰጥ
16. ሁለት በአንድ ላይ
18. ምኑንም ምኑንም መሰብሰብ
20. የተጠራቀመ
22. የሚበራ
23. በገጠር ውሃ መጠጫ
25 የሸቀጥ ልውውጥ
27. ኢላማ ሳይመታ ቀረ
29. ሽኩርምም
31. አብሮ የሚያያዝ
32. በልብሱ መሸፈን
34. ጠዋት
37. ተናገረ
38. ከት ብሎ ______

# የላንዳፍታ መጽሔት ማዘዣ ቅጽ

የላንዳፍታ መጽሔት እንደታተመች ወዲያውኑ ካሉበት ቦታ እንዲደርሶት ይህንን ቅጽ በመሙላት ከነክፍያው ይላኩልን።

| | 12 ISSUES | 6 ISSUES |
|---|---|---|
| U.S. | $30.00 ☐ | $16.00 ☐ |
| Canada | $40.00 ☐ | $22.00 ☐ |
| Europe | $56.00 ☐ | $30.00 ☐ |
| Asia. | $70.00 ☐ | $38.00 ☐ |
| Institutions | $80.00 ☐ | $40.00 ☐ |

*(please, mark your choice above and send your payment in U.S. Dollars)*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (    )* __________

==========================================================

*I would like to order for my friend as well. I have included both payments.*
*My friend's name and address are as follows.*

*Subscriber's Name:* ______________________________

*Address:* ______________________________

*City:* ______________________________

*St.* __________ *Zip* __________ *Phone: (    )* __________

==========================================================

*TOTAL PAYMENT ENCLOSED: $* ☐

*LANDAFTA, P.O.BOX 49301, Atlanta, GA 30359*




# ናዝሬት ምግብ ቤት

## NAZARETH RESTAURANT

*Authentic Ethiopian Cusine*

5291 Memorial Drive
Stone Mountain, GA 30083

በቅርቡ የተከፈተው
የናዝሬት የአገር ባህል ምግብ ቤት
የተሟላ የባር አገልግሎት አለው።
ዓርብና ቅዳሜና እሁድ ምሽቶች
የሙዝናኛ ፕሮግራሞች ይኖሩናል።



የአገርን ትዝታ የሚቀሰቅስ የባህል ምግብ ተመግቦ ምሽቱን
ከአገር ልጆች ጋር ለማሳለፍ የናዝሬት ምግብ ቤት አለላችሁ።

ና
ዝ
ሬ
ት

ብቅ ብላችሁ ጎብኙን!!
በመስተንግዷችን ትደሰታላችሁ!!
በምግባችን ጣዕምን ትረካላችሁ!!

Phone: (404) 294-0043

# ሀናና ብንያም ምግብ ቤት

## H & B Restaurant

## Ethiopian Cuisine & Bar



በቅርቡ ሥራውን የጀመረ
ሀናና ብንያም ምግብ ቤት የውደ
ደንበኞቹን ፍላጎት ለማርካት በል
ዝግጅትና መስተንግዶ የባህ
ምግቦችን ያቀርባል።

በተጨማሪም ዘወትር ዓርብ፤
ቅዳሜና እሁድ የተለያዩ
የምሽት የመዝናኛ
ፕሮግራሞችን
ያቀርብላችኋል።

**H & B Restaurant**

***Ethiopian Cuisine & Bar***

4600 A. E. Ponce DeLeon Ave.
Clarkston, GA 30021
Phone: (770)723-0502






በተጨማሪ በ431 N. Indian Creek, Suite
በሚገኘው ሀናና ብንያም በተሰኘው
የኢትዮጵያ ሽቀጦች መደብራችን የበለ
በማሻሻል እንጀራ፤ በርበሬና
የመሳሰሉትን፤ እንዲሁም የአገር ልብስ
ጌጣጌጦች በጥሩ ሁኔታ እናቀርባለን
ጎብኙን!!
ስልክ ቁጥር (404) 296–2766

መጥተው ይጎብኙን!!
በመስተንግዶአችን ይኮራሉ።